# የቀደመው ክብር

## የብሉይ ኪዳን ዳሰሳ



መልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)

የቅጂ መብት - © መልሳቸው መስፍን - 2003
© Melisachew Mesfin – 2011

በክፍሉ ካልተጠቀሰ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1962 ከታተመው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

የመጀመሪያ እትም - 2003 ዓ.ም.
First printing - 2011

አስተያየት ቢኖርዎት:-
ፖ. ሣ. ቁ. 31716
አዲስ አበባ

Email: onebmtm@yahoo.com

# አበርክቶ

ይህን ‹የቀደመው ክብር› የተሰኘውን
የብሉይ ኪዳን ዳሰሳ መጽሐፍ፡-
በነቢይ ‹እነሆ፤ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፤
ስሙንም አማኑኤል ይሉታል› እንደተባለው

ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ
ዓለምን ከኃጢአት የሚያድን
የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ መሆኑን ለሚያምኑ

## በምድራችን ላሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ

በትሕትናና በደስታ አበረክታለሁ።

# ማውጫ


መግቢያ ------------------------------------------------------------7

ክፍል አንድ፡- የሕግ መጻሕፍት ----------------------------12
ምዕራፍ 1፡- ኦሪት ዘፍጥረት ----------------------13
ምዕራፍ 2፡- ኦሪት ዘጸዓት -------------------------19
ምዕራፍ 3፡- ኦሪት ዘሌዋውያን --------------------30
ምዕራፍ 4፡- ኦሪት ዘኁልቁ -------------------------35
ምዕራፍ 5፡- ኦሪት ዘዳግም ------------------------39

ክፍል ሁለት፡- የታሪክ መጻሕፍት ----------------------------43
ምዕራፍ 6፡- መጽሐፈ ኢያሱ ---------------------44
ምዕራፍ 7፡- መጽሐፈ መሳፍንት------------------48
ምዕራፍ 8፡- መጽሐፈ ሩት ------------------------52
ምዕራፍ 9፡- መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ --------55
ምዕራፍ 10፡- መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ----------59
ምዕራፍ 11፡- መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ---------64
ምዕራፍ 12፡- መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ------------68
ዜና መዋዕል ---------------------------------------74
ምዕራፍ 13፡- ዜና መዋዕል ቀዳማዊ -------------75
ምዕራፍ 14፡- ዜና መዋዕል ካልዕ ----------------78
ምዕራፍ 15፡- መጽሐፈ ዕዝራ --------------------82
ምዕራፍ 16፡- መጽሐፈ ነህምያ -------------------86
ምዕራፍ 17፡- መጽሐፈ አስቴር ------------------89

ክፍል ሦስት፡- የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት ----------------92
ምዕራፍ 18፡- መጽሐፈ ኢዮብ -------------------94
ምዕራፍ 19፡- መዝሙረ ዳዊት --------------------99
ምዕራፍ 20፡- መጽሐፈ ምሳሌ -------------------104
ምዕራፍ 21፡- መጽሐፈ መክብብ ----------------109
ምዕራፍ 22፡- መኃልየ መኃልይ -----------------113

ክፍል አራት፡- የነቢያት መጻሕፍት ------------------116
ክፍል 4.1፡- ታላላቅ ነቢያት ---------------------------118
ምዕራፍ 23፡- ትንቢተ ኢሳይያስ ---------------119
ምዕራፍ 24፡- ትንቢተ ኤርምያስ --------------124
ምዕራፍ 25፡- ሰቆቃወ ኤርምያስ --------------129
ምዕራፍ 26፡- ትንቢተ ሕዝቅኤል --------------132
ምዕራፍ 27፡- ትንቢተ ዳንኤል -----------------136

ክፍል 4፡2፡- ደቂቅ ነቢያት፡፡ ---------------------------140
ምዕራፍ 28፡- ትንቢተ ሆሴዕ ---------------------141
ምዕራፍ 29፡- ትንቢተ አሞጽ --------------------144
ምዕራፍ 30፡- ትንቢተ ሚክያስ -----------------147
ምዕራፍ 31፡- ትንቢተ ኢዩኤል -----------------150
ምዕራፍ 32፡- ትንቢተ አብድዩ ------------------153
ምዕራፍ 33፡- ትንቢተ ዮናስ ----------------------155
ምዕራፍ 34፡- ትንቢተ ናሆም --------------------158
ምዕራፍ 35፡- ትንቢተ ዕንባቆም -----------------160
ምዕራፍ 36፡- ትንቢተ ሶፎንያስ -----------------162
ምዕራፍ 37፡- ትንቢተ ሐጌ -----------------------164
ምዕራፍ 38፡- ትንቢተ ዘካርያስ -----------------167
ምዕራፍ 39፡- ትንቢተ ሚልክያስ ----------------170

ማጠቃለያ ---------------------------------------------------173
ዋቢ መጻሕፍት ------------------------------------------177



# መግቢያ

ብሉይ ማለት ያረጀ፤ የነበረ፤ ጥንታዊ፤ አሮጌ ማለት ከሆነ ብሉይ ኪዳንን ማጥናት ለምን ያስፈልጋል? በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ከተጻፉ ከ2000 ዓመታት በላይ የሆናቸውን መጻሕፍት ማጥናት ከታሪካዊነቱ ያለፈ መንፈሳዊ ጠቀሜታው ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ብሉይ ኪዳንን የማጥናት ጥቅምና አስፈላጊነት አዲስ ኪዳንን እንደማጥናት ነው፡፡

## ብሉይ ኪዳንን የማጥናት አስፈላጊነት፡፡

- በዘመናት የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን ማንነት፤ ባሕርይና አሠራሩን ስለሚያሳዩና ይህም ዘላለማዊ እውነት በመሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሀሳቡን መናገር የጀመረው በብሉይ ኪዳን ነው፡፡ ‹እኔ አምላክ ነኝና፤ ሌላም የለምና፤ ...በመጀመሪያ መጨረሻውን ...እነግራለሁ፤ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ አፈጽማለሁ› (ኢሳ 46፡9-10) ብሏል፡፡
- ሁለቱም ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ከአንዱ ከሕያው እግዚአብሔር የተሰጡ የቀደመና የአሁን ኪዳኖች ስለሆኑ ነው፡፡ አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተደብቆአል፤ ብሉይ ኪዳን ደግሞ በአዲስ ኪዳን ተገልጾአል (2ቆሮ 3፡6-18)፡፡ የሁለቱም ኪዳኖች ዋና ዓላማ በኃጢአት የወደቀ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበትንና ኅብረት የሚያደርግበትን መንገድ ማሳየት ነው፡፡
- ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የተያያዙና የመገለጥ እድገት (ቀጣይነት) የሚታይባቸው የአንድ መጽሐፍ የተያያዙ ክፍሎች ስለሆኑ ነው፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድና እድገት ጋር በተያያዘ በብሉይ ኪዳን የተነገረው በአዲስ ኪዳን ተፈጽሞአል (ማቴ 2፡15፤18፡23)፡፡ በብሉይ ኪዳን መሢሕን እንደሚልክ የተናገረ እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ‹...የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን...ልጁን ላከ› (ገላ 4፡4-5)፡፡
- የቀደመው ኪዳን ለአዲሱ ጥላ፤ አዲስ ኪዳን ለቀደመው ፍጻሜ ስለሆነ ነው፡፡ አዲስ ኪዳን እስከሚመጣ ድረስ ብሉይ ኪዳን የተሸፈነ ነበር፤ መጋረጃው በክርስቶስ ተገፈፈ (2ቆሮ 3፡14)፡፡

ክርስቶስ ከሚያመለክቱ በርካታ ምሳሌዎች ጥቂቶቹ በሠንጠረዥ 8 ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 8
ስለ ክርስቶስ የሚያመለክቱ ምሳሌዎች

| ጥላ ወይም አመልካች (ታይፕ) | እውነተኛው አምሳል |
|---|---|
| ፋሲካ (ዘጸ 12:5-6፡21) | ፋሲካችን ክርስቶስ (1ቆሮ 5:7፤ ዮሐ 1:19) |
| ነጻ መውጣት (19:1) | ክርስቶስ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን (ቆላ 1:13፣ 2ቆሮ 1:10) |
| መና (16:15;35) | ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ (ዮሐ 6:31-35፤48-63) |
| ውኃ የፈለቀበት ዓለት (17:6) | ዓለቱ ክርስቶስ (1ቆሮ 10:4) |
| የማደሪያው ድንኳን 25:8 | ክርስቶስ ‹በእኛ አደረ› (ዮሐ 1:14፤ ዕብ 9:1-10:18) |
| የድንኳኑ በር (መጋረጃ) (26) | ክርስቶስ አዲስና ሕያው መንገድ (ዕብ 10:20) |
| ሊቀ ካህናት (ዘሌ 16) | ኢየሱስ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት (ዕብ 4:14-16) |
| መሥዋዕት (ዘሌ 1-6) | ከኃጢአት የሚያነጻው የክርስቶስ ደም (ዕብ 9:13-14) |
| የነሐሱ እባብ መሰቀል (ዘኁ 21:4-9) | ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን የተሰቀለ (ዮሐ 3:14) |

**ዋና ትምህርት:-**

**እግዚአብሔር ሰውን ለይቶ ያውቃል።** ‹ዮሴፍን ያላወቀ ንጉሥ› በእስራኤላውያን ላይ መከራ ቢያበዛባቸው ዮሴፍን የሚያውቅ እግዚአብሔር ሕዝቡን በተዘረጋች ክንዱ ታደገ። በአንድ አገር ውስጥ ከሚኖረው ሕዝብ መካከል እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ለይቶ ያውቃል፤ ይጠብቃል፤ ይባርካል። እስራኤላውያን ይኖሩበት የነበረው ጌሳም ከመቅሰፍት፤ የእስራኤላውያንም በኩር ልጆች ከሞት ‹በደም› እንደተጠበቁ እግዚአብሔር የእንዳንዱን ሰው ሰፈር፤ ቤትና ንብረት ያውቃል። በአንድ ቦታ ብርሃንና ጨለማ በማድረግ የእርሱ የሆኑትን ለይቶ ይጠብቃል፤ ሊቀጣው የፈለገውንም ለይቶ ይቀጣል። በእግዚአብሔር ዘንድ ‹ጅምላ ጨራሽ› የሚባል አሠራር የለም።

**የእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን በነገሥታት፤ በተፈጥሮና በእማልክትም ሁሉ ላይ ነው።** ሰግብጻውያን በሰው በንድ የማይቻለው በአማልክቶቻቸው በኩል እንደሚሆንላቸው ያስቡ



ነበር። ብዙ አማልክትም ነበሯቸው። ይሆን እንጂ አማልክቶቻቸው ባሕር መክፈል እንኳን ባይችሉ የታመነባቸውን ሕዝብ በተክፈለ ባሕር ውስጥ ማሳለፍ አልቻሉም። ለዚህም ነው የእስራኤል ልጆች ይህንን መዝሙር ለእግዚአብሔር የዘመሩት (ዘጸ 15:1-2)።

በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤
ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ።
ጉልበቴ ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፤
መድኃኒቴም ሆነልኝ፤
ይህ አምላኬ ነው አመሰግነዋለሁ፤
የአባቴ አምላክ ነው ከፍ ከፍም አደርገዋለሁ።

- ✦ ውኃ የወጣበት ዓለት (20:8-11) ‹ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ› (1ቆሮ 10:4)።
- ✦ ነፍስ ገዳይ ሰው የሚሸሸበት የመማጸኛ ከተማ (35:25-32)፤ ተስፋውን ለመያዝ ወደ እርሱ ለሸሹ መሸሸጊያ ክርስቶስን ያመለክታል (ዕብ 6:18)።

**ዋና ትምህርት፡-**
**አለማመንና አመጽ መንገድን ያረዝማል፤ በምድረ በዳም ያስቀራል፡፡** ከእስራኤላውያን አለማመንና ዓመጽ የተነሳ (ዕብ 3:16-4:2) የ11 ቀን መንገድ (ዘዳ 1:2) 38 ዓመት (ዘዳ 2:14) ወሰደባቸው። ብዙዎችም በምድረ በዳ ቀሩ (ሞቱ)። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ደስ አላለውም (1ቆሮ 10)። እግዚአብሔር የጽድቅ ባሕርይው በእርሱ አለማመንንና ማጉረምረምን እንዲቀጣ ያደርገዋል። ሙሴ እንኳን ከእግዚአብሔር ቅጣት አላመለጠም።

**እግዚአብሔር ሲመራ ምንም አያሳጣም፡፡** ወደ ግብጽ ሲገባ 70 ነፍስ የነበረው የያዕቆብ ዘር (ዘፍ 46:26-27፤ ዘጸ 1:5) ከ430 ዓመት በኋላ (ዘጸ 12:40) እግዚአብሔር እጅግ አብዝቶት (ዘጸ 1:7፤12፤20) ‹እግረኛው› ብቻ ከ600000 በላይ በመሆኑ ጠቅላላው ሕዝብ ከ2 ሚሊዮን እንደሚበልጥ ይገመታል።



እግዚአብሔር ለዚህ ሁሉ ሕዝብ በምድረ በዳ መንገድ አሳየ፤ መና፤ ውኃ፤ ሥጋ ሰጠ። ልብሳቸው አላረጀም፤ ጫማቸው አላለቀም (ዘዳ 29:5)፤ ሕዝቡ ምንም አላጡም (ዘዳ 2:7)። ይህ ማፕ[22] የእስራኤላውያን የምድረ በዳ ጉዞ ያሳያል።

[22] ምንጭ፡- ቲም ዶውሊይ (ዶ/ር) (1989)፤ የተማረው የመጽሐፍ ቅዱስ አትላስ፤ ኤስ ኣይ ኤም ኢትዮጵያ አሳታሚ፤



## ምዕራፍ 5፡-

# ኦሪት ዘዳግም

**ጸሐፊው፡-** ሙሴ ነው። ስለ ሙሴ መሞት የሚናገረውን ምዕ 34 ኢያሱ እንደጻፈው ይገመታል።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 1410 ዓ.ዓ.።

**ስያሜ፡-** ዘዳግም[23] ማለት የተደገመ (ድጋሚ) ማለት ሲሆን ተደም ሲል ከ38 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሲና[24] (በዘጸ 20ና በሌሎችም ክፍሎች) የሰጠው ሕግ ተብራርቶ የተነገረበት መጽሐፍ ነው።

**ዋና ሰዎች፡-** ሙሴ፤ ኢያሱ

**ዋና ሀሳብ፡-** የእግዚአብሔርን ቃል ልብ ስለማለት (ስለመጠበቅ) ሙሴ የመጨረሻ ትምህርትና ምክር ይሰጣል። ሙሴ የ38 ዓመቱን የምድረ በዳ ጉዞ ይቃኛል፤ የእግዚአብሔርን መልካምነት ይገልጻል፤ የተስፋይቱን ምድር ስለመውረስ ይናገራል፤ እርሱን የሚተካውን ኢያሱን ያደፋፍራል።

**ተደጋጋሚ ቃላት፡-** ‹እግዚአብሔር› የሚለው 944 ጊዜ፤ ‹ልብ በል፤ አስብ/ አትርሳ› 50 ጊዜ፤ ‹ቃል ኪዳን› 27 ጊዜ ያህል ተጽፎአል። ይህ መጽሐፍ ከዘዳግም በኋላ ባሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 356 ያህል ጊዜ እንዲሁም በአዲስ ኪዳን 80 ያህል ጊዜ ተጠቅሶአል። ጌታ ኢየሱስ በምድረ በዳ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ ‹ተጽፎአል› በማለት የመለሰለት ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ነው (ማቴ 4:4፤ ሉቃ 4:4 - ከዘዳ 8:3፤ ማቴ 4:7፤ ሉቃ 4:12 - ከዘዳ 6:16፤ ማቴ 4:10፤ ሉቃ 4:8 - ከዘዳ 6:13)።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ✦ ‹እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን

[23] Gk- Deuteronomiom <second law>
[24] ሲና ሌላ ስሙ ኮሬብ ነው (ዘጸ 3:1፤12፤ 19:1፤ ዘዳ 5:2)

ማንነት የሚገልጽ ታላቅና ዘላለማዊ እውነት ነው። ይህን እውነት ማወቅና በልብ መጠበቅ (6፡6)፤ በልብ ውስጥ የተጠበቀውን በቤት ውስጥ መግለጥ (ማስተማር/ መተግበር) ይገባል (6፡7)፤ በቤት ውስጥ ያለው ደግሞ ከቤት ውጭም መገለጽ/ መስፋፋት አለበት (6፡8-9)።

**ልጆችን ማስተማር የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።** እግዚአብሔር ያደረገውንና ያስተማረንን እንዳንረሳው ደጋግሞ ስለ መማርና ስለ ማስተማር፤ ለቀጣዩ ትውልድም ስለ ማስተላለፍ ይህ መጽሐፍ አጥብቆ ያስገነዝባል። ወላጆች ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው እግዚአብሔርን እንዲያውቁት፤ እንዲፈሩትና እንዲታዘዙት የማስተማር ኃላፊነት አለባቸው (4፡9-10፤ 6፡7፤ 11፡18-19፤ 31፡12-13)።

**ሕይወትን ምረጥ።** በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ የሚናገረው ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ስለ መኖር ነው። በመታዘዝ ስለሚመጣ በረከትና ባለመታዘዝ ደግሞ ስለሚከተል ርግማን ያብራራል። እግዚአብሔርን በመታዘዝ መኖር ሕይወትን መምረጥ ሲሆን አለመታዘዝ ደግሞ ሞትን መምረጥ ነው። እያንዳንዱ ሰው የተፈጠረው የመምረጥ ነጻነት ኖሮት በመሆኑ ማንም ሰው ሕይወት እያለ ሞትን ሊመረጥ አይገባውም።

**የሕግ መሰጠት ዓላማ ለመልካም ነው።** ሙሴ የሕግን መሰጠት ዓላማ ‹መልካም እንዲሆንልህ› (10፡13) በማለት ይገልጻል። ሕግን ለሚጠብቅ ሰው ለእርሱ መልካም ይሆንለታል፤ ወደ እግዚአብሔር ያስጠጋልና። ሕግ ስለ ክርስቶስ የሚያመለክት ነው። ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው (ማቴ 5፡17)።



# ክፍል ሁለት
# የታሪክ መጻሕፍት

የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ተብለው የሚጠሩት ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ መጽሐፈ አስቴር ያሉት 12 መጻሕፍት ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት እስራኤል የከነዓንን ምድር ከወረሱበት ጊዜ አንስቶ ባለማመንና ባለመታዘዝ ምክንያት እስከተማረኩበትና ከምድሪቱ እስከተወሰዱበት ድረስ ያለውን የ700 ዓመት ያህል ጊዜ ይሸፍናሉ።

በእነዚህ መጻሕፍት ጎልተው የሚታዩ ርዕሶች፦
- ✦ ከነዓንን መውረስ -
- ✦ በምድሪቱ ላይ የተነሱ ጠላቶችና የመሳፍንት አስተዳደር -
- ✦ የነገሥታት አስተዳደር -
- ✦ የእስራኤል ሰሜንና ደቡብ መንግሥታት
- ✦ የሰሜኑ መንግሥት በአሦር ሥር መውደቁ
- ✦ የደቡቡ መንግሥት ወደ ባቢሎን በምርኮ መወሰዱ
- ✦ የእስራኤል ቅሬታዎች ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ

እነዚህን ጉልህ ነጥቦች ከየመጻሕፍቱ ትኩረት አንጻር በ3 በመክፈል በሠንጠረዥ 12 ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 12

**በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ የተገለጸ የእስራኤል ታሪክ**

| | ዋና ሀሳብ | መጽሐፍ |
|---|---|---|
| 1. | **መለኮታዊ አገዛዝ** | |
| | ከነዓንን መውረስና መከፋፈል | ኢያሱ |
| | ምድሪቱ በጠላቶች መገዛትና የመሳፍንት መነሳት | መሳፍንት፤ ሩት |
| | | |
| 2. | **የነገሥታት አገዛዝ** | |
| | ምድሪቱ ከጠላቶች ማረፍ | 1 ሳሙኤል |
| | የእስራኤል የመንግሥቱ መጽናት፤ መስፋት | 2 ሳሙኤል |
| | የእስራኤል የከፍታ ዘመን | 1 ነገሥት 1-10 |
| | የእስራኤል መከፈል | 1 ነገሥት 11-22 |
| | የሰሜኑ መንግሥት መዳከም | 2 ነገሥት 1-17 |
| | የደቡብ መንግሥት በምርኮ መወሰድ | 2 ነገሥት 18-25 |
| | ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ዝግጅት | 1 ዜና መዋዕል |
| | የቤተ መቅደሱ መሠራትና መፍረስ | 2 ዜና መዋዕል |
| | | |
| 3. | **ከምርኮ በኋላ** | |
| | የቤተ መቅደሱ እንደገና መሠራት | ዕዝራ |
| | የኢየሩሳሌም እንደገና መሠራት | ነህምያ |
| | ሕዝቡ ከመከራ መጠበቁ | አስቴር |

# ምዕራፍ 6፡-
# መጽሐፈ ኢያሱ

**ጸሐፊው፡-** ኢያሱ ነው (8:32; 24፡26)። ከኢያሱ ሞት በኋላ ያለው ምዕ 24፡29-33 በሌላ ሰው እንደተጻፈ ይታሰባል።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 1400-1370 ዓ.ዓ.።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በመጽሐፉ ውስጥ ጎልቶ ከሚታየው ከኢያሱ ስም የተወሰደ ነው። ከኤፍሬም ነገድ የሆነው የነዌ ልጅ ኢያሱ የሙሴ አገልጋይ ነበር። የመጀመሪያ ስሙ አውሴ[26] ነበር (ዘኍ 13፡8)። ሙሴ ኢያሱ[27] ብሎ ጠራው (ዘኍ 13፡16)፤ ትርጓሜውም ‹ያህዌ (እግዚአብሔር) አዳኝ ነው› ማለት ነው።

**ዋና ሰዎች፡-** ኢያሱ፤ ካሌብ፤ ረዓብ

**ዋና ሀሳብ፡-** የተስፋይቱን ምድር መውረስ። ይህ መጽሐፍ እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ያደረጉትን ዝግጅት፤ ድል ማድረግና ምድሪቱን መከፋፈል ያስረዳል። እግዚአብሔርን ፈጽሞ በመታዘዝ ስለሚገኘው ድልና በረከት ይገልጻል።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** የእግዚአብሔር ስም 219 ጊዜ፤ ተዋጋ/መዋጋት፤ መውረስ

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ቀናልሃል፤ ይከናወንልሃልም› (1፡8)።
- ‹...የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን› (24፡15)።
- ‹እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም› (21፡45)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን በ4 በመክፈል እንደሚከተሰው ማየት ይቻላል።

[26] Hoshea

[27] *Yeshua*, a contracted form of Yehoshua, meaning, "Yahweh is salvation," is the Greek equivalent of the name Jesus.



1. ምድሪቱን ለመውረስ ዝግጅት (1-5)
2. ምድሪቱን መውረስ (6-12)
3. ምድሪቱን መከፋፈል (13-22)
4. የኢያሱ ስንበትና ማስጠንቀቂያ (23-24)

**1. ምድሪቱን ለመውረስ ዝግጅት፡-** እስራኤላውያን ምድሪቱን ለመውረስ ከመውጣታቸው በፊት ያደረጉት ዝግጅት፡-

- መሪ ተመረጠ (1)- እግዚአብሔር መመሪያ ሰጠ፤ ኢያሱን እንዲበረታና እንዳይፈራ አዘዘው።
- ምድሪቱን ሰለሉ (2)፤- እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት በቂ መረጃ እንዲሰበስቡ ሁለት ሰላዮች ተላኩ። ረዓብ የተባለች ጋለሞታ ተቀበለቻቸው፤ ደበቀቻቸውም። ረዓብ ያደረገችው የእምነት ሥራ በዕብ 11፡31 እና ያዕ 2፡25 ተገልጻአል።[28]



- በፊታቸው ያለውን የዮርዳኖስ ወንዝ ተሻግረው ቀረቡ (3-5)- ወደ ዋናው ጦርነት ከመግባታቸው በፊት እግዚአብሔር ታላቅን ነገር ያደርግ ዘንድ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መቀደስ እንደሚገባቸው አዘዛቸው (3፡5)። ያልተገረዙ ወንዶች በጌልገላ ተገረዙ። መና መውረዱ ቀረ። የእግዚአብሔርም መልአክ[29] የሰልፉ መሪ ሆኖ ተገለጠ። ኢያሱ ከሰዎች መካከል የተሾመ መሪ ቢሆንም የሰልፉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው።

**2. ምድሪቱን መውረስ።** ኢያሱ በሦስት አቅጣጫ ጦርነቶች አደረገ። (ይህ ካርታ የእስራኤል ነገዶች የወረሱትን ቦታ ያሳያል[30])።

[28] በብሉይ ኪዳን ከምናገኛቸው ሴቶች መካከል የእምነት ሴቶች ተብለው በዕብ 11 የተጠቀሱ ሣራ (11፡11)፤ የሙሴ እናት/ዮካብድ (23)፤ ረዓብ (31) ናቸው።

[29] ስለ እግዚአብሔር መልአክ ማንነት በመልሳቸው መስፍን (1996 ዓ.ም) **እግዚአብሔር መለኮት**፤ አንድነት ማተሚያ ድርጅት ገጽ 75-76 የተጻፈውን ይመልከቱ።

- **በማዕከላዊ ከነዓን፡-** ኢያሪኮ፤ አይ፤ ገባዖን። አስቀድሞ ኢያሪኮን ድል ሲያደረጉ የኢያሪኮ ግንብ በድምጽ የፈረሰበት ተአምር ይገኛል (5፡13-6፡21)። በአካን ኃጢአት ምክንት በጋይ እስራኤላውያን ተሸንፈው ነበር (7፡21)። በኂላም እርምን አስወግደው ሲዋጉ ጋይን ድል አደረጉ። ኢያሱ እግዚአብሔርን ሳይጠይቅ ከገባዖን ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን አደረገ (9)።
- **በደቡብ ከነዓን፡-** ከአምስቱ የአሞራውያን ነገሥታት ጋር በገባዖን በተደረገው ውጊያ እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ በማውረድ ፀሐይም እንዳትጠልቅ ለአንድ ሙሉ ቀን ያህል በማዘግየት ኢያሱን ረዳው፤ ድልን ሰጠው (10፡11-14)።
- **በሰሜን ከነዓን፡-** በመጨረሻም ኢያሱ በሰሜን የሚገኙትን ነገሥታት ድል አደረገ (11)።

**3. ምድሪቱን መከፋፈል።** ምድሪቱን ለ12ቱ ነገዶች ተከፋፈሉ። ከ40 ዓመታት በፊት ከኢያሱ ጋር ምድሪቱን የሰለለው የእምነት ሰው ካሌብ በጠየቀው መሠረት ኢያሱ ኬብሮንን ሰጠው።

**4. የኢያሱ ስንበትና ማስጠንቀቂያ።** ኢያሱ ከመሞቱ በፊት ሕዝቡን ለእግዚአብሔር ስለ መለየት/ መቀደስ አስገነዘባቸው (23፡8)። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን እንዲያድሱና ለእርሱ ታማኝ ሆነው እንዲኖሩ አጥብቆ በመምከር ‹…የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን› (24፡15) በማለት የራሱን ምርጫ አስታውቃቸው።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ኢያሱ።**
ነውርን የማንከባለል ምሳሌ የሆነው የሥጋን ሰውነት በመግፈፍ የሆነ መገረዝ (5፡7-9) በክርስቶስ የሆነን የልብ መገረዝ ያሳያል. (ቆላ 2፡10-12)።

**ዋና መልእክት፡-**
***መሪን ማዘጋጀትና መተካት፡-*** ኢያሱ በእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የተጀመረውን ታላቅ የሕዝብ መሪነት አገልግሎት ለመፈጸም ብቁ ሰው ነበር። ከልጅነቱ ጀምሮ የሙሴ አገልጋይ የነበረ (ዘጸ 24፡12፤ ዘኍ 11፡28)፤ ሙሴን የሚታዘዝ (ኢያ 11፡15)፤ ከመገናኛው ድንኳን የማይለይ ታማኝ (በጸ 33፡11)፤ የከነዓንን ምድር ለመሰለል የተላከ

[30] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1972 ዓ.ም.)፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።



(ዘኍ 13፡8)፤ እግዚአብሔርን ፈጽሞ የተከተለ (ዘኍ 32፡10-12)፤ በሰልፍ የተፈተነ (ዘጸ 17፡8-15)፤ መንፈስ ያለበት (ዘኍ 27፡18)፤ በሙሴ እጅ መጫን የጥበብን መንፈስ የተሞላ (ዘኍ 27፡17-19፤ ዘዳ 34፡9) ሰው ነበር። እንዲሁም መሪነቱ ከሙሴ ወደ ኢያሱ በሚተላለፍበት ጊዜ እግዚአብሔር ተተኪውን ኢያሱን አበረታታው፤ መመሪያም ሰጠው (ኢያ 1-4)። ኢያሱ ደግሞ በተራው በመሪነቱ መጨረሻ ላይ ሲደርስ ሕዝቡን መከረ፤ ከአባቶቻቸው ጀምሮ ያለውን የእግዚአብሔርን ታማኝነት አጉልቶ በማሳየት ሕዝቡ እግዚአብሔር እንዲከተሉ እርሱንም ብቻ እንዲያመልኩ አስጠነቀቀ (ምዕ 24)።

***ሁለት ጌቶች መገዛት አይቻልም፡-*** እግዚአብሔር ከማንም ጋር በደባልነት የሚመለክ ሳይሆን ሰው መርጦና ፈቅዱ የሚያመልከው ንጹህ አምላክ ነው። እስራኤላውያን በወረሱት ምድር የነበረው ባዕድ አምልኮ የሕዝቡን ልብ እየሰረቀ ስለነበረ ‹የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ› (24፡15) የሚለው የኢያሱ ምክር ለሁለት ጌቶች መገዛት እንደማይችሉ ይገልጻል። ሆኖም እስራኤላውያን የኢያሱን ምክር ባለመስማታቸው ወደ ጣዖት አምልኮ ወደቁ (መሳ 1፡1-3፡6) ብዙ ጉስቁልና ደረሰባቸው።

***ውሳኔ በፊት ጥናት ማድረግ ይጠቅማል።*** ከዮርዳኖስ ማዶ የተሠራው መሠዊያ (22፡10) ለእስራኤላውያን ኃጢአትና ዐመፅ (ጣዖት) ስለመሰላቸው በሕዝቡ መካከል የእርስ በርስ ጦርነት ሊያስነሳ ነበር። ሆኖም ጉዳዩ በጥንቃቄ ሲመረመር ለመሠዊያነት ሳይሆን ‹ምስክር› (22፡28) እንዲሆን መሠራቱ ስለታወቀ ከሕግ መተላለፍ አለመሆኑ ተረጋግጧል (22፡10-31)። ይህም ከውሳኔ በፊት ጉዳይን በጥንቃቄና በትዕግሥት መረጃ ማሰባሰብና ማጥናት በወንድማማች መካከል ሊነሣ ከሚችል ጠብና መለያየት እንደሚጠብቅ ያስተምራል።

**እግዚአብሔር የተናገረውን ይፈጽማል።** ፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ‹…ይህችን ምድር ለዘርህ ለጥቼአለሁ› (ዘፍ 15፡18) በማለት የሰጠውን ተስፋ እንዲሁም ከ480 ያህል ዓመታት በኋላ ለኢያሱ ‹…የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ ለእናንተ ለጥቼአለሁ› (1፡3) በማለት የገባውን ቃል ሁሉ ፈጸመ። ‹…ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ› 11፡23፤ ‹… እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም› (21፡43-45)።

## ሠንጠረዥ 13
## የእስራኤላውያን ክፉ ሥራ፤ ቅጣት፤ ንስሐና የእግዚአብሔር መታደግ

| ተ.ቁ | ክፉ ሥራ/ ኃጢአት | አልፎ መሰጠት | | | ንስሐ | የእግዚአብሔር መታደግ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቅጣት | ዓመት | ገዥ አገር | | መስፍን በመስጠት | የእረፍት ዘመን |
| 1. | 3:7 | 3:8 | 8 | መስጴጦምያ | | ጎቶንያል | 40 (3:9-11) |
| 2. | 3:12 | 3:12-14 | 18 | ሞአብ | 3:15 | ናዖድ | 80 (3:30) |
| 3. | | 3:31 | | ሞአብ | | ሰሜጋር | --- 3:31 |
| 4. | 4:1 | 4:2 | 20 | ከነዓን | 4:3 | ዲቦራና ባርቅ | 40 (5:31) |
| 5. | 6:1 | 6:1 | 7 | ምድያም | 6:6 | ጌዴዎን | 40 (8:28) |
| 6. | | | | ምድያም | | ቶላ | 23 (10:2) |
| 7. | | | | ምድያም | | ኢያዕር | 22 (10:3) |
| 8. | 10:6 | 10:7-9 | 18 | አሞን | 10:10-16 | ዮፍታሔ | 6 (12:7) |
| 9. | | | | አሞን | | ኢብጻን | 7 (12:9) |
| 10. | | | | አሞን | | ኤሎም | 10 (12:11) |
| 11. | | | | አሞን | | አብዶን | 8 (12:14) |
| 12. | 13:1 | 13:1 | 40 | ፍልስጥኤም | | ሶምሶን | 20 (15:20) |

እግዚአብሔር የሚያስነሳቸው መሳፍንት አስቀድመው ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው ያድናሉ፤ ከዚያም በመስፍንነት ያገለግላሉ። በዚህ ሁሉ የእስራኤል ዋናው መስፍን (ፈራጅ) የሕዝቡን ጩኸት የሚሰማ፤ የሚራራላቸው፤ መሪ የሚመርጥና በኃይል (በመንፈስ) የሚሞላ፤ የሚታደጋቸው እግዚአብሔር ነው። እርሱ ፈራጅ ነው (11:27፤ 8:23)።

እግዚአብሔር ካስነሳቸው ፈራጆች መካከል **ዲቦራ፤ ጌዲዮንና ሶምሶን** በጣም የሚታወቁት ናቸው። ነቢይቱ **ዲቦራ** (4:1-5:31) ባርቅን ያደፋፈረችና በመጨረሻም የድል ዝማሬ የዘመረች መሪ ነበረች። **ጌዲዮን** (6:1-9:57) በእግዚአብሔር የተመረጠ፤ ጣዖትን ያጠፋ፤ የቆረጠ፤ ምሪትን ከእግዚአብሔር የተቀበለ፤ ሕዝቡን ከባርነት ያዳነ፤ ‹እኔ አልገዛችሁም እግዚአብሔር ይገዛችኋል› በማለት ለሕዝቡ የተናገረ ታላቅ መስፍን ነበር። **ሶምሶን** (13:1-16:31) ከማህፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ፤ ብረቱ ተዋጊ፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል (13:25፤ 14:6፤19፤ 15:14) ድል ያደረገ ፈራጅ ነበር።



**ክርስቶስ በመጽሐፈ መሳፍንት፡፡**
ከጌድዮን ጋር የተነጋገረው ‹የእግዚአብሔር መልአክ› 6:12፤20፤21፤22)፤ እግዚአብሔር ነው (6:14፤ 23)። ይህም ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የተገለጸበት መንገድ (ክሪስቶፋኒ) ነው።

**ዋና ትምህርት፡-**
**እግዚአብሔርን ፈጽሞ መታዘዝ እረፍትንና በረከትን ያመጣል፤ አለመታዘዝ ደግሞ ቅጣትንና ጉስቁልናን ያስከትላል።** እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በከፊል ለመታዘዝ የሞከሩባቸው ዓመታት ነበሩ። እግዚአብሔርን አመልካለሁ እያሉ መጥፋት ያለበትን ጨርሶ አለማጥፋት ቅይጥ ሕይወት ነው፤ ወጥመድን ያስከትላል። ለምሳሌ ከማያምን ጋር በጋብቻ መጠመድ (3:5-6)፤ ለጣዖት እየሰገዱ እግዚአብሔርንም አመልካለሁ ማለት ወጥመድ ነው።

**እያንዳንዱ በፊቱ መልካም የመሰለውን ሲያደርግ ውድቀት ይከተላል፡፡** የመሳፍንት ዘመን የሚገለጸው እግዚአብሔርን መፍራት ያልነበረበትና ሰው ሁሉ የራሱ መለኪያ የነበረው ጊዜ መሆኑ ነው (21:25)። ‹ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው› (መዝ 119:105) እንደሚል ሰው ሁሉ ሊመራበት የሚገባው ትክክለኛው መለኪያና መንገድ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

**እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ነው፡፡** ‹የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔርን፡- እኛ ኃጢአትን ሠርተናል ... ዛሬ ግን እባክህ አድነን አሉት። ...ነፍሱም ስለ እስራኤል ቁስቁልና አዘነች› (10:15-16) እንደሚል እስራኤላውያን በንስሐ ሲመለሱ እግዚአብሔር ይራራላቸው ነበር። የእግዚአብሔር ምሕረቱ አያልቅምና፤ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው (ሰቆ 3:22)።

# ምዕራፍ 8፡-
# መጽሐፈ ሩት

**ጸሐፊው፡-** አይታወቅም። አብዛኛው ክፍል በነቢዩ ሳሙኤል እንደተጻፈ ይገመታል።

**ጊዜው፡-** 1000 ዓ.ዓ.። የሩት ታሪክ የተፈጸመው በመሳፍንት ዘመን ነበር (1፡1)።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** መጽሐፉ ስያሜውን ያገኘው በመጽሐፉ ውስጥ ብዙ ጊዜ ስሟ ከተጠቀሰው ከሞዓባዊቷ ሩት ነው። ሩት የቦዔዝ እናት የንጉሥ ዳዊት ቅድመ አያት ነች። ሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በስማቸው ከተሰየመባቸው ሁለት ሴቶች አንዷ ስትሆን ሴላዋ ንግሥት አስቴር ነች።

**ዋና ሰዎች፡-** ኑኃሚን፤ ሩት፤ ቦዔዝ

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** መቤገርት (ተቤዥ) የሚለው ቃል 23 ጊዜ ያህል ይገኛል (2፡20፤ 3፡9፤12፤13፤ 4፡1፤3፤4፤6፤7፤8፤14)።

**የመጽሐፉ ሀሳብ፡-** መጽሐፉ የሚያተኩረው እንዲት በትውልዷ እስራኤላዊት ያልሆነች ሴት በመቤገርት ሕግ መሠረት በንጉሥ ዳዊት እንዲሁም በጌታ ኢየሱስ የዘር ሐረግ (ማቴ 1፡5-6፤16፤ ሉቃ 3፡23-32) ውስጥ እንዴት እንደገባች ማሳየት ነው። ሞዓባዊቷ ሩት ከሎጥ ዘር ነች (ዘፍ 19፡37)።

**ቁልፍ ጥቅስ፡-**

- ‹…እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጎበኘ እንጀራም እንደ ሰጣቸው …› (1፡6)።
- ‹…ሕዝብሽ ሕዝቤ፤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል› (1፡16)።
- ‹…ዛሬ ዋርሳ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ስሙም በእስራኤል ይጠራ› (4፡14)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** የሩትን ድርጊቶች ተከትሎ መጽሐፉን በአራት መክፈል ይቻላል።



1. የሩት ውሳኔ (1፡1-22)
2. የሩት መቃረም (2፡1-23)
3. የሩት ቦዔዝን ማግኘት (3፡1-18)
4. የሩት ብድራት (4፡1-22)

1. **የሩት ውሳኔ፡-** በይሁዳ ራብ በሆነበት ዘመን አቤሜሌክ ሚስቱን ኑኃሚንንና ሁለት ወንድ ልጆቹን ይዞ ወደ ሞዓብ አገር ሄደ። መሐሎን የተባለው ልጅ ሩትን አገባ። መሐሎን ሲሞትና ራቡም ከምድር እንዳለፈ ኑኃሚን ባወቀች ጊዜ ወደ ቤተ ልሔም ለመመለስ ፈለገች። ሩትም ከኑኃሚን ጋር መሄድን መረጠች። ሞዓባዊቷ ሩትም እንደስሟ[32] ወዳጅነትን አጥብቃ ያዘች።

2. **የሩት መቃረም፡-** ኑኃሚንና ሩት ቤተልሔም ከደረሱ በኋላ ለመኖሪያ የሚሆናቸውን ቃርሚያ ይቃርሙ ነበር። ሩትም በቦዔዝ እርሻ ትቃርም ነበር። ቦዔዝ የኑኃሚን ባል የነበረው የአቤሜሌክ ዘመድ ነበር።

3. **የሩት ቦዔዝን ማግኘት፡-** ሩት በኑኃሚን ምክር መሠረት ቦዔዝን በእህል አውድማው አገኘችው። ቦዔዝም በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት ሩትን ከመውሰዱ በፊት ከእርሱ ይልቅ ለአቤሜሌክ የቅርብ ዘመድ መኖሩን ለማጣራት ወሰነ።

4. **የሩት ብድራት፡-** በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት (ዘሌ 25፡25-32፤47-55፤ ዘዳ 25፡5-10) ባሏ የሞተባትን ሴት የባሏ የቅርብ ዘመድ (2፡20፤ 3፡12) እንዲያገባት ይፈቅዳል። የሚቤዥ የቅርብ ዘመድ የሆነ፤ መቤገርት የሚችል (ሀብት ያለው)ና ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው። ይህም ‹የቅርብ ዘመድ ታዳጊ›[33] እንደ ማለት ነው። ቦዔዝም የቅርብ ዘመድ ሆኖ ስለተገኘ ሩትን አገባት። ሩት ከቦዔዝ ኢዮቤድን ወለደች (4፡17)። ኢዮቤድ የዳዊት አባት የሆነው የእሴይ አባት ነው።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ሩት።**
እንደ ሕጉ (ሌዋ 25፡47-49) ሩትን የተቤዠ የቅርብ ዘመድ (ሩት 4፡4-8) ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ የሰውን ዘር በደሙ ከኃጢአት ዋጀ (ገላ 3፡13፤ ራእ 5፡9)። እርሱ ለሰው የቅርብ ዘመድ ነው

[32] ሩት ማለት ጓደኝነት/ ወዳጅነት ማለት ነው። Hb. rooth- friend.
[33] the Kinsman-Redeemer *orgoc*. "close relative."

(ሥጋ የለበሰ)፤ መቤዠት የሚችል (ሁሉ የእርሱ የሆነ)ና ፈቃደኛ የሆነ (ራሱን አሳልፎ የሰጠ) ነው።

**ዋና ትምህርት፡-**

**ምርጫቸው እግዚአብሔር ለሆነ እርሱ መልካምነቱን ያጠግባቸዋል፡፡** ኑኃሚን ባሏና ሁለቱ ልጆቿ ከሞቱ በኋላ ወደ ቤተ ልሔም ስትመለስ ሁለቱን ምራቶቿን ለእነርሱ የሚሆን ተስፋ በቤተ ልሔም የለምና (1፡9-14) በሞዓብ እንዲቀሩ ግድ ስትላቸው ዖርፋ ‹…ወደ ሕዝብዋና ወደ አማልክትዋ› ተመለሰች (1፡15)። ከአማቷ (ከባሏ እናት) ከኑኃሚን መለየት ያልወደደችው ሩት ‹ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል› (1፡16) በማለት ኑኃሚንን ተከትላ ከሀገሯ ወደ እስራኤል ለመሄድ ቆረጠች። እግዚአብሔርም መልካም አደረገላት፤ ባልና ልጅን ሰጣት፤ በመሲሁ በክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥም ገባች። አስቀድሞ የእግዚአብሔር የሆነውን የሚፈልግ በሌላው ሁሉ ይባረካል (ማቴ 6፡33)።
እንዲሁም ‹ሁሉን የሚችል አምላክ አስመርሮኛልና ማራ[34] በሉኝ እንጂ ኑኃሚን አትበሉኝ› (1፡20) ያለችውን ኑኃሚን ከዓመታት በኋላ በእርሷ ላይ የእግዚአብሔርን መልካምነትን ያዩ ሊያመሰግኑ ‹…እግዚአብሔር ይባረክ ስሙም በእስራኤል ይጠራ› (4፡14) አሉ። እግዚአብሔር በስተእርጅናዋ የሚመግባት ልጅ ሰጥቷታልና (4፡15)። ካለፈችበት ሁኔታ የተነሣ ኑኃሚን[35] ደስታ የሚል ትርጉም ያለውን ስሟን ‹እግዚአብሔር አስመርሮኛል› (1፡20) ስትል ማራ ብላ ለወጠች። ሆኖም በስተርጅናዋ ከምትወዳት ምራት ከሩት ልጅ ሲወለድላትና ስታቅፈው (4፡15-16) ለኑኃሚን መታደስ ሆነላት። ይህም የእግዚአብሔር መልካምነት ነው።

**እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጎበኛል፡፡** በቤተ ልሔም ራብ በሆነ ጊዜ አቤሜሌክ ቤተሰቡን ይዞ ወደ ሞአብ ሄደ። የተፈጥሮ አዛዥ ሕያው እግዚአብሔር በጊዜው ሕዝቡን ጎበኘ፤ እንጀራንም ሰጠ። እግዚአብሔር ርኅራኄው ብዙ ነው።

[34] ማራ ማለት መራራ ማለት ነው።
[35] ኑኃሚን ማለት ደስታ ማለት ነው



## ምዕራፍ 9፡-

# መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ

በዕብራስጡ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ አንድ መጽሐፍ ናቸው።

**ጸሐፊው፡-** ሳሙኤልና ሌሎች። በ10፡25 መሠረት ሳሙኤል እንደጻፈው ሲታሰብ የእርሱ ሞት ከተነገረበት ከምዕራፍ 25 በኋላ ያለውን የጻፈው ሌላ ሰው መሆን ስለሚኖርበት ናታንና ጋድ ሊሆኑ ይችላሉ (1ዜና 29፡29) ተብሎ ይገመታል።

**ጊዜው፡-** 930 ዓ.ዓ.

**ስያሜ፡-** በመጽሐፉ በተገለጸው በነቢዩ ሳሙኤል ነው። ሳሙኤል ከመሳፍንት ዘመን የመጨረሻው መስፍን ፈራጅ (7፡6)ና ነቢይ (3፡20) ነበር።

**ዋና ሰዎች፡-** ኤሊ፤ ሳሙኤል፤ ሳኦል፤ ዳዊት

**ዋና ሀሳብ፡-** እግዚአብሔር ያከበሩትን እንደሚያከብር መታዘዝም ከመሥዋዕት እንደሚበልጥ ያስተምራል። እግዚአብሔር እንደ ሳሙኤልና ዳዊት ያሉ ታናናሾችን የእርሱ ሀሳብ አገልጋይ አድርጎ ሲያሳድግና ሲቀባ ያሳያል። በካህኑ ኤሊና በሳኦል የነበረው አለመታዘዝ ያስከተለውን ቅጣት ያመለክታል።

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ፡-** ቅባት (ቀባው) የሚለው 7 ጊዜ፤ መኻር (መናቅ) 7 ጊዜ።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹… ያከበሩኝን አከብራለሁና፤ የናቁኝም ይናቃሉና ይህ አይሆንልኝም› (2፡30)።
- ‹ …ሰው ፊትን ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል› (16፡7)።
- ‹ … እነሆ፤ መታዘዝ ከመሥዋዕት፤ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል› (15፡22-23)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱ 3 ዋና ሰዎችን ተከትሎ እንደሚከተለው መክፈል ይቻላል።

1. ሳሙኤል (1-8)
2. ሳኦል (9-15)
3. ዳዊት (16-31)

1. **ሳሙኤል፡-** እናቱ ሐና በጸሎት ያገኘችውን ልጇን ለእግዚአብሔር ከሰጠችበት ቀን አንስቶ (1፡27-28) በቤተ መቅደስ አደገ። እስራኤልን በካህንነት፤ በነቢይነትና በፈራጅነት አገለገለ። የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት የጀመረው በልጅነት ዕድሜው ነበር (3)። የካህኑ ኤሊ ልጆች እግዚአብሔርን የማይፈሩ የመሥዋዕትን ሥርዓት የማያከብሩ ነበሩ። ይህም ፍርድ አስከትሎባቸዋል። ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተደረገ ጦርነት ታቦቱ ተማረከ፤ ክብር ከእስራኤል ለቀቀ (ኢካቦድ ሆነ)። ታቦቱ በተማረከበት ቦታ እረፍት ስላልሰጣቸው ወደ እስራኤል መለሱት (4-6)። ከዚህም በኋላ በምጽጳ መንፈሳዊ መነቃቃት (7) ሆነ።

በሳሙኤል ዘመን በእግዚአብሔር መለኮታዊ አገዛዝ (ቀጥተኛ አስተዳደር) ሥር የነበሩት እስራኤላውያን እንደሌላው አሕዛብ መሆንን ፈልገው ንጉሥ እንዲሾምላቸው ጠየቁ። ይህም በእግዚአብሔር ዓይን እርሱን መናቅ ነበር (1ሳሙ 8፡7)። እግዚአብሔር ንጉሥ የሚሰጣቸው ጊዜ እንደሚኖር ተናግሮ ነበር (ዘፍ 49፤10፤ ዘዳ 17፡14-15፤ 28፡36)[36]። የሕዝቡ ከመለኮታዊ አገዛዝ ወደ ንጉሣዊ አገዛዝ[37] ሽግግር ጥያቄ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ጊዜ ያልጠበቀ በራሳቸው ጊዜ እንዲሆንላቸው ግድ ያሉበት ነው። እግዚአብሔርም የተመኙትን እንዲያደርግላቸው ፈቀደ (1ሳሙ 8፡7፤ 10፡19፤ 12፤17-19)። በዚህም መሠረት ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ተሾመ።

[36] አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እርሱ የሚወደው (የሚመርጠው) ነገር እንኳን ሳይሆን ሰዎች ግድ ብለው የጠየቁትን እንዲያገኙ ይፈቅዳል (ዘኁ 14፡2፤26-27፤ 22፡20፤ መዝ 106፡15)። አጥብቀን እንድንጸልይ የሚገባ ሲሆን (ሉቃ 11፡5-13፤ 18፡1-8፤ 2ቆሮ 12፡7-10) የእግዚአብሔርን ፈቃድና ጊዜ በመጠየቅ ሳይሆን እኛ የምንፈልገውን ብቻ እንዲሆንልን ግድ ማለት እግዚአብሔርን እንደ መናቅ ይሆናል።
[37] Theocracy to the Monarchy



2. **ሳኦል፡-** ሳኦል በሳሙኤል የተቀባ ከእስራኤል ነገሥታት የመጀመሪያው ንጉሥ ነበር። ሳኦል በእግዚአብሔር የተናቀና ከንጉሥነቱ የተሻረም ንጉሥ ነው። ሳኦል የተናቀውና የተሻረው እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ ነበር (1ሳሙ 13፡13-14፤ 15፡11፤22-23፤26-29)። ፍልስጥኤማዊው ጎልያድ እስራኤልን ለመውጋት በመጣ ጊዜ እርሱን እንዲገጥም የሚጠበቅ ሰው በጊዜው መሪ የሆነውና እንደ ጎልያድ ረጅሙ ሳኦል (1ሳሙ 9፡2) በሆነ ነበር። ሴቶች ‹ሳኦል ሺህ፤ ዳዊትም እልፍ ገደለ› (18፡7) ካሉበት ጊዜ ጀምሮ ሳኦል፡-

- ዳዊትን ተመቅኝቶ ተመለከተው (18፡9)።
- በዳዊት ጦሩን ወረወረበት (11)
- ዳዊትን ፈራው (12)
- ዳዊትን ከእርሱ አራቀው (13)
- ዳዊትን እጅግ ፈራው (15)
- ዳዊት በፍልስጥኤማውያን እንዲገደል በመመኘት የሺህ አለቃ አደረገው (13፤17)
- ለዳዊት ወጥመድ ትሆነው ዘንድ ልጁን ሜልኮልን ዳረለት (20-21፤ 27)
- ዕድሜውን ሁሉ ለዳዊት ጠላት ሆነ (29)

3. **ዳዊት፡-** ዳዊት በሳኦል ምትክ እግዚአብሔር የቀባውና የሾመው ንጉሥ ነው። ዳዊት ለንጉሥነት በሳሙኤል በተቀባበት ጊዜ በግ ጠባቂ ነበር። ዳዊት በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው ነበር። ጎልያድን በጦርነት የገጠመው ‹…በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ› (1ሳሙ 17፡45) በማለት ነው። ነገር ግን ዳዊት ጎልያድን ድል ባደረገ ጊዜ ሳኦል በዳዊት ቀንቶ አሳደደው። ከዚህ ሁኔታ በኋላ 1ኛ ሳሙኤል መጽሐፍ ስለ ዳዊት የሚናገረው ከሳኦል በመሸሽ ስላሳለፈው የስደት ኑሮ ነው።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፡፡**
ቀንዱ ከፍ ከፍ የሚለው መሲሕ /የተቀባው (2፡10) እርሱ ክርስቶስ ነው (ሐዋ 4፡27፤ 10፡38)

**ዋና ትምህርት**

***ያከበሩኝን አከብራለሁ፡-*** የካህኑ ኤሊ ልጆች የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ማርከሳቸውና የመሥዋዕቱን ሥርዓት አለመጠበቃቸው እግዚአብሔርን መናቃቸው ነበር። እግዚአብሔርም ጥበቃውን ከእነርሱ ላይ አነሣ፤ በእርሱ ተንቀዋልና። እግዚአብሔር እርሱን ለሚፈሩት ጋሻ ነው፤ ከበጎም ነገር አያጎልባቸውም።

**የሐና ዝማሬ፡-** ምድር በጣዖት አምልኮ በረከሰችበትና የካህናት ልጆች እግዚአብሔርን በማይፈሩበት ዘመን የነበረችው ሐና እግዚአብሔርን የምታውቅ የጸሎት ሰው ነበረች። የጸለየችውንም ስትቀበል ለእግዚአብሔር ምስጋናን ማቅረብ አልረሳችም። ልጅን በሰጣት በእግዚአብሔር መልካምነት ደስ ተሰኝታ እንዲህ ዘመረች (1ሳሙ 2)፡-

> አትታበዩ፤ በኩራትም አትናገሩ፤
> እግዚአብሔር አዋቂ ነውና፤
> እግዚአብሔርም ሥራውን የሚመዝን ነውና
> ከአፋችሁ የኩራት ነገር አይውጣ።



# ምዕራፍ 10፡-
# መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ

**ጸሐፊው፡-** አይታወቅም።

**ጊዜው፡-** 930 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-**

**ዋና ሰዎች፡-** ዳዊት፤ ቤርሳቤህ፤ ናታን፤ አቤሴሎም

**ዋና ሀሳብ፡-** መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ከሳኦል ሞት በኋላ ስለ ዳዊት መንገሥ፤ ስለግዛቱ መስፋትና በኃጢአት ምክንያት በሕይወቱ ስለመጣው ውድቀት ያሳያል። የዳዊትን መልካም ነገር፤ ስህተትና ውድቀት ይገልጻል።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** የዳዊት ስም 267 ጊዜ ተጽፎአል። በአዲስ ኪዳንም የዳዊት ስም 58 ጊዜ ተጠቅሷል።

**ቁልፍ ጥቅስ፡-**

- ‹ዳዊትም ናታንን፤ እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን፤እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤ አትሞትም። ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል አለው› (12፡13-14)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን ከንጉሡ ዳዊት ሕይወት ጋር በተያያዘ በ3 መክፈል ይቻላል።

1. የዳዊት መንገሥና የመንግሥቱ መጽናት (1-10)
2. የዳዊት በኃጢአት መውደቅና ውጤቱ (11-21)
3. የመጨረሻው ሁኔታ (22-24)

1. **የዳዊት መንገሥና የመንግሥቱ መጽናት፡-** ዳዊት በሙሉው እስራኤል ላይ የነገሠ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው። ዳዊት በኬብሮን ለ7 ዓመት ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በኢየሩሳሌም ለ33 ዓመት በድምሩ ለ40 ዓመታት ነገሠ (5፡4-5፤ 2ዜና 29፡27)። ኢየሩሳሌምን የእስራኤል ዋና ከተማ አደረገ። የእስራኤል መንግሥት የተመሠረተው በሳኦል ዘመን ሲሆን የጸናውና የሰፋው በዳዊት ዘመን ነበር። በዳዊት ንጉሥነት ላይ

- **በቤተሰቡ ላይ፦** ከቤትህ ሰይፍ፣ አይርቅም (12:10) እንደተባለው በልጆቹ አምኖንና አቤሴሎም ምክንያት በቤተሰቡ ላይ ታላቅ ችግር መጣ፤ ከኢየሩሳሌም እስከ.ሸሽም ድረስ (ምዕ 14-18) ሆነ።
- **በመንግሥቱ ላይ፦** በሕዝቡ መካከል የነበረው ሰላም እየደፈረሰ መጣ (19:9-10)፤ በተቃውሞም ተነሱበት።

ዳዊት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲያልፍ፣ ስሜቱን በመዝሙር ገልጾ ነበር። ጥቂቶቹ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ 15 ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 15

በሳሙኤል መጽሐፍ፣ የተገለጸ ዳዊት በመዝሙሩ.[39]

| በሳሙኤል መጽሐፍ፣ | ሁኔታው | በመዝሙር |
|---|---|---|
| 1ሳሙ 19:11 | የዳዊት ቤት በተከበበ ጊዜ | 59 |
| 21:10-11 | ዳዊት በአኪሽ በተያዘ ጊዜ | 56 |
| 21:12-22:1 | ከአኪሽ ባመለጠ ጊዜ | 34 |
| 22:1 | ዳዊት በዋሻ ውስጥ | 57፤ 142 |
| 22:9-19 | ኤዶማዊው ዶይቅ ባወራበት ጊዜ | 52 |
| 23:14-15 | በኤዶምያስ ምድረ በዳ | 63 |
| 23:19 | ሰዎች ዳዊትን በከዱት ጊዜ | 54 |
| 2ሳሙ 8:1-14 | ድል ከዮርዳኖስ ማዶ | 60 |
| 11-12 | ስለ ያሪያ ቤት ወደ ቤርሳቤህ በገባ ጊዜ | 51 |
| 15-17 | አቤሴሎም ባመጸ ጊዜ | 3፤ 7 |
| 15-17 | በይሁዳ ምድረ በዳ | 63 |
| 22 | በጠላቶች ላይ ድል ሲያገኝ | 18 |

3. ***የመጨረሻው ሁኔታ፦*** በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች በእስራኤል ስለመጣው ራብና ዳዊት ሕዝቡን በመቁጠሩ ምክንያት ስለመጣበት ቅጣት እንመለከታለን። ሕዝብን መቁጠር በራሱ ኃጢአት አይደለም። ሙሴ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እስራኤላውያንን ሁለት ጊዜ ቆጥሯልና (ዘኁ 1 እና 26)። በዳዊት ላይ በደል የሆነበት ሕዝቡን ስለቆጠረበት ዓላማ ነው። ይህም ምናልባት ዳዊት ‹አቅሙን› ለመለካት ፈልጎ ይሆናል፤ ሆኖም ምን እንደነበረ እግዚአብሔር ያውቀዋል። መልካም ነገር በክፉ ዓላማ ሲደረግ በእግዚአብሔር ፊት በደል ይሆናል።

[39] ESV Study Bible. p.488. Life Application Bible. P.953



**ክርስቶስ በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ።**
ከኃጢአቱ በስተቀር ዳዊት በብሉይ ኪዳን የክርስቶስ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ‹የንጉሥነት የዘላለም ቃል ኪዳን› የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ሮሜ 1:3)።

**ዋና ትምህርት፦**
**የኃጢአት ውጤት ጉስቁልና ነው።** ሰው እግዚአብሔርን ይፈራል እንጂ እግዚአብሔር ማንንም ሰው አይፈራም። ዳዊት የእስራኤል ታላቅ ንጉሥና ቃል ኪዳን የተገባለት ሰው ቢሆንም እንኳን ከእግዚአብሔር የጽድቅ ሚዛንና ፍርድ አላመለጠም። በአንድ ወቅት ‹ዳዊት ያደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆነ› (11:27) እንደሚል እግዚአብሔር በኃጢአት ያዝናል፤ የሚወዳቸውን ይቀጣቸዋል። ኃጢአት ደስታን ወደ ሀዘን፤ ድል አድራጊነትን ወደ ውድቀት ይለውጣል።

**የተዋረደ መንፈስ ያለውን ሰው እግዚአብሔር ይወዳል።** ዳዊት የእግዚአብሔርን ቅባት የሚያከብርና የይቅርታ ልብ ያለው ሰው ነበር። በነቢዩ ናታን ኃጢአት ማድረጉ ከነገረው በኋላ ዳዊት ከመንግሥቱ መቀመጫ ወረደ፤ በአመድም ላይ ተቀመጠ፤ እግዚአብሔርንም በንስሐ ለመነ። እንዲህም አለ ‹እግዚአብሔርን በድያለሁ› (12:13)። ምድራዊ ሥልጣኑንና ክብሩን ኃጢአቱን ለመሸፈኛነት፤ ነቢዩንም ለማስፈራሪያነት አልተጠቀመበትም። ንጉሥ ቢሆንም ለነገሥታት ንጉሥ ለእግዚአብሔር ተንበረከከ። ዳዊትን ‹እንደ ልቤ› ያሰኘውም ይህ የተዋረደ መንፈሱ ነው። እግዚአብሔርም ምሕረት አደረገለት።

**የመዝራትና የማጨድ ሕግ።** ‹ኃጢአት ብንሠራም ንስሐ እስከገባን ድረስ እግዚአብሔር ይቀር ይለናል› ብሎ ራስን አለመግዛት እግዚአብሔርን መዳፈር ነው። ኃጢአትን መናዘዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ወይም ምሕረትን ቢያስገኝም በዳዊት እንደታየው ስለ ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር የሚያመጣውን ቅጣት ግን ላያስቀረው ይችላል። እግዚአብሔር ንስሐ የተገባበትን ኃጢአት እንደ ቸርነቱ ብዛት ይቅር ይላል፤ የተፈጸመውን ኃጢአት ግን ያልተፈጸመ ድርጊት አያደርገውም። ዳዊት ኃጢአትን ዘራ ኃጢአትን በቤተሰቡ አጨደ። ‹ሰው ሁሉ የዘራውን ያንኑ ያጭዳል› (ገላ 6:7)። የተሳሳቱ ምርጫዎችና ድርጊቶች ከፍተኛ ዋጋ (ቅጣት) ስለሚያስከትሉ (2ሳሙ 6:6፤ 11:4፤15፤ 13:14፤28-29፤ 14:24፤ 16:7፤ 21:1፡ 24:10) በእግዚአብሔር ጸጋ እርሱን እየፈሩ መኖር ከቅጣት ይጠብቃል።

# ምዕራፍ 11:-

# መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ

በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በአንድነት ‹መጽሐፈ ነገሥት› ተብለው ይጠራሉ።

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ ኤርምያስ ነው። በ2ነገ 24-25 ያለው ሀሳብ በኤር 39-42፣ 52 ስለሚገኝ የኤርምያስን ጸሐፊነት ያጠናክረዋል። የጻፈውም የታሪክ መጻሕፍትን በማገናዘብ ነው (11:41፣ 14:19፣29)። ከኤርምያስ ሌላ የእስራኤልን ታሪክ የሚያውቁ ዕዝራ ወይም ሕዝቅኤል ድርሻ ይኖራቸው ይሆናል። 1ኛ ነገሥትን የጻፈው 2ኛ ነገሥትንም እንደጻፈ ይታሰባል።

**ጊዜው:-** 550 ዓ.ዓ.። ታሪኩ የ400 ዓመታት (970-586 ዓ.ዓ) ያህል ጊዜ ይሸፍናል።

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በአብዛኛው ከነገሥታት ጋር በተያያዘ የሰሜኑንና የደቡቡን እስራኤል ታሪክ ስለሚናገር ነገሥት ተብሏል።

**ዋና ሰዎች:-** ሰሎሞን፣ ኤልያስ፣ አክዓብ፣ ኤልዛቤል

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ:-** ንጉሥ 250 ጊዜ፣ ነቢይ 43 ጊዜ

**ዋና ሀሳብ:-** የነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ነው። ንጉሥ ዳዊት ከሞተበትና ልጁ ሰሎሞን ከነገሠበት ጊዜ አንስቶ ይሁዳ ተብሎ የሚታወቀው ደቡብ የእስራኤል ክፍል በባቢሎን እስከተማረከበት ያለውን የከፍታና የዝቅታ ዓመታትን ታሪክ ይዟል። የእነዚህ መንታ መንግሥታት አብዛኛዎቹ ነገሥታት እግዚአብሔርን ባስመታዘዛቸው ሁሉቱም ለምርኮ አልፈው ተሰጥተዋል።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች:-**

- ‹በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፣ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፣ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ!› (8:27)።



- ‹እናንተም የአምላካችሁን ስም ጥሩ፥ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ፣ ስምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ፥ እርሱ አምላክ ይሁን› 18:24)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** መጽሐፉን እንደሚከተለው በ 3 መክፈል ይቻላል።

1. የንጉሥ ሰሎሞን ሕይወትና አገዛዝ:- (1-11)
2. የጸናው መንግሥት መከፈል:- (12-16)
3. ኤልያስና አክዓብ (17-22)

**1. የንጉሥ ሰሎሞን ሕይወትና አገዛዝ:-** ይህ ዘመን የእስራኤል የከፍታ ዘመን ነበር። አንድ የጸና የእስራኤል መንግሥት የነበረበት፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም የታነጸበት፣ ሰሎሞንም ቤተ መንግሥት የሠራበት ዘመን ነበር። ሰሎሞን ሳለው ኃላፊነት የእግዚአብሔርን ጥበብ በመለመኑ በጥያቄው እግዚአብሔር ደስ ተሰኝቶ ጥበብን፣ ማስተዋልን እንዲሁም ያልጠየቀውን ‹ክብር› ሁሉ ሰጥቶት ነበር። እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ የሰሎሞን ዝና በዓለም ሁሉ ስለወጣ የሳባ ንግሥተ ልትጎበኘው ሄዳ ነበር (10:1-13)። ይሁን እንጂ ሰሎሞን በኋለኛው የእድሜ ዘመኑ ሚስቶችን አባዛ ልቡንም ወደ ጣዖት እምስኮ ሳቡበት (11:1-6)። ‹የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ...በአምላኩም ዘንድ የተወደደ ነበር፤ ...እርሱንም እንኳ እንግዶች ሴቶች አሳቱት› (ነህ 13:26)። ከዚህ የተነሳ በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን አልተከተለም፤ ልቡ ተከፈለበት። የተከፈለ ልብ ወደ ተከፈለ መንግሥት አመራ።

**2. የጸናው መንግሥት መከፈል:-** ከሰሎሞን ቀጥሎ የነገሠው ሮብዓም ነበር። ሕዝቡ ግብር እንዲቀንስላቸው ሲጠይቁት በመዛቱ አሥሩ የእስራኤል ነገድ ዐምጾ ከእጁ ወጣ። ይህም ሰሜን እስራኤል (ሰማርያ) ተብሏል። የይሁዳንና የብንያም ነገዶችን የያዘው ደቡቡ ክፍል ደግሞ ‹ይሁዳ› በመባል ይታወቃል። የሰሜኑ ክፍል (እስራኤል) 20፤ የደቡቡ ክፍል (ይሁዳ) ደግሞ 20 ነገሥታት ነበሯቸው (ሠንጠረዥ 17)። የሰሜኑ ክፍል በአሦራውያን

የእስራኤል መንግሥት ከመከፈሉ በፊትና በኋላ



ከተማረከ በኋላ ይሁዳ ለ140 ዓመታት ሳይማረክ ቆይቶ በመጨረሻ በባቢሎን እጅ ወድቋል። የሰሜኑ ክፍል ንጉሥ የነበረው ኢዮርብዓም በቤቴልና በዳን የአምልኮ ቦታዎችን በማዘጋጀት እስራኤልን ወደ ኃጢአት የመራ ንጉሥ ነበር። እግዚአብሔር ነቢያትን በመላክ ቢያስጠነቅቀውም ለመስማት አልወደደም።

**3. ኤልያስና አክዓብ፡-** በመጽሐፉ የመጨረሻ 6 ምዕራፎች የአመጸኛውን የይሁዳ ንጉሥ የአክዓብን መንገድና የእስራኤልን ኃጢአት የተቃወመውን የነቢዩ ኤልያስን አገልግሎት እንመለከታለን። ኤልያስ እስራኤል በኣልን በመከተል በታላቅ መንፈሳዊ ውድቀት በገባችበት ጊዜ ለዘመኑ የሚሆን እግዚአብሔር ያስነሳው ታላቅ ነቢይ ነው። የሰማዩ መንግሥት አገልጋይ ኤልያስ የምድራዊውን መንግሥት ንጉሥ አክዓብን ስለ ኃጢአቱ ወቅሷል። አክዓብና ሚስቱ ኤልዛቤል በታጠቁት ሰይፍ ኤልያስን ያስፈራራሉ፤ ኤልያስ በጸሎት የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ሕያው እግዚአብሔር እንደሆነ እውነተኛው የእስራኤል ንጉሥ ሕያው እግዚአብሔር እንደሆነ ያሳያል። ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ያቀረበውን መሥዋዕት ከሰማይ እሳት ወድቃ ስተበላው በእውነት እርሱ የእግዚአብሔር ባሪያ እንደሆነ ታወቀ፤ በእስራኤል የነበሩትንም 450 የበኣል ነቢያት አሳረዳቸው (18:20-40)።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ።**
ክርስቶስ ጥበበኛውና ዝናው የወጣለት ሰሎሞን (1ነገ 10:1-13)፤ ክርስቶስ ከሰሎሞን የሚበልጥ (ማቴ 12:42፤ ሉቃ 11:31፤ 1ቆሮ 1:30)

**ዋና ትምህርት፡-**
**የመንፈሳዊ መሪ ዋና መለኪያ እግዚአብሔርን መታዘዙ ነው።** እግዚአብሔር መሪዎችን (ሰዎችን) በሀብታቸው፤ በእውቀታቸው፤ በአስተዳደር ችሎታቸው አይለካም። የመሪ ዋናው መለኪያ ለእግዚአብሔር ቃል ያለው ታዛዥነት ነው። ይህ መለኪያ የመሪን ከፍታና ውድቀት ይወስናል። ይህን አጥብቆ የተረዳው ዳዊት ልጁን ሰሎሞንን ‹በርታ ሰውም ሁን፤ ...የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ› (2:3) በማለት አስጠንቅቆት ነበር። የአባቱን ምክር ያልሰማው ሰሎሞን መጨረሻው እንደ ጅማሬው ያላመረለት ንጉሥ ሆነ።



**እግዚአብሔርን አለመታዘዝ የጸና መንግሥትንም ይጥላል።** የእስራኤል ደህንነት የተመሠረተው ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታማኝ በመሆኗ ላይ ነው። እግዚአብሔር በየዘመናቱ ነቢያቱን እየላከ ቢመክራትም በአምቢታ መንገድ የቀጠለች እስራኤል የአምላኳ ጥበቃ ተነሣባት፤ ወደ ውድቀት አመራች፤ ለማራኪዎችም አልፋ ተሰጠች። ቃሉ ‹ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፤ ኃጢአት ግን ሕዝብን ታስነውራለች› (ምሳ 14:34) እንደሚል ነው። እግዚአብሔር በኃጢአት ሲቆጣ ለስሙ ክብር የተሠራው ቤተ መቅደስ እንኳ እንዲፈረስ ይፈቅዳል።

**የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከተል በሁኔታዎች ምቹነት ላይ የተመሠረተ አይደለም።** ኢዮርብዓም በቤቴልና በዳን የአምልኮ ቦታዎችን ያዘጋጀው ሕዝቡ እስከ ኢየሩሳሌም ሩቅ መሄድ ስለሚበዛባቸው (12:28) በቅርቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ በሚል ሰበብ ነበር። ይህን በማድረጉ እስራኤል ሁሉ እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወጣ የሚያዘውን ሕግ ጣሰ (ዘዳ 12:5-14፤ 16:2-6)። እንዲሁም ለአምልኮ ጥጃዎች በማሰራቱና ካህናትን በመሾሙ ጣዖት አምልኮን ተከተለ (12:31-32)። እግዘአብሔር የላከውን ነቢይ ስላልሰማ እግዚአብሔር ቀጣው (14:13-14)። የሰው ምቾት እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ በማይከበርበት ታላቅ ውድቀት ይከተላል።

# ምዕራፍ 12:-
# መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ

**ጸሐፊው፡-** ነቢዩ ኤርምያስ። 1ኛ ነገሥትን የጻፈው 2ኛ ነገሥትንም እንደጻፈው ይታሰባል።

**ጊዜው፡-** 550 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** እንደ 1ኛ ነገሥት ሁሉ በአብዛኛው ከነገሥታት ጋር በተያያዘ የሰሜኑንና የደቡቡን እስራኤል ታሪክ ስለሚናገር ነገሥት ተብሏል።

**ዋና ሰዎች፡-** ኤልያስ፤ ኤልሳዕ፤ ሕዝቅያስ፤ ኢዮስያስ

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ‹ንጉሥ› 400 ጊዜ፤ ‹...በእግዚአብሔር ፊት› ወይም ‹በእግዚአብሔር ዓይን› የሚለው 28 ጊዜ መጠቀሱ (ለምሳሌ 3:2፤18፤ 8:18) የሰው ሀሳቡም ሆነ የሠራው ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚታወቅና በትክክል የሚመዘነው በእግዚአብሔር ዓይን መሆኑን ያስተምረናል።

**ዋና ሀሳብ፡-** የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት እስከተማረኩበት ጊዜ የነበረውን ሕይወትና ታሪክ መግለጽ። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ የተጀመረውን የነቢዩን ኤልያስና የኤልሳዕን ታሪክ በመቀጠል በአብዛኛው ስለ መንታዎቹ የእስራኤል መንግሥታት ሁኔታና ሁለቱም መንግሥታት እስከተማረኩበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ታሪክ ያስረዳል። የሰሜኑ ክፍል በ722 ዓ.ዓ. በአሦር ((ነነዌ) እጅ ሲወድቅ ይሁዳ ደግሞ ከ140 ዓመታት በኋላ በ586 ዓ.ዓ. በባቢሎን ተማረከ። በሁለቱም በታዎች/ አገሮች እግዚአብሔር ነቢያቱን በየጊዜው እየላከ ከኃጢአታቸው በንስሐ ካልተመለሱ እንደሚቀጣቸው ሕዝቡን ያስጠነቅቅ ነበር።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹እግዚአብሔርንም ሲፈሩ ከመካከላቸው እንደ ፈለሱት እንደ እሕዛብ ልማድ አምላካቸውን ያመልኩ ነበር›[40] (17:33)።

[40] አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ‹በአንድ በኩል እግዚአብሔርን ሲያመልኩ፤ በሌላ በኩል ግን እንደየአገራቸው ልማድ የየራሳቸውን አምልኮት ያመልኩ ነበር› ይላል።



**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን እንደሚከተለው በ3 መክፈል ይቻላል።

1. የኤልያስ ወደ ሰማይ መወሰድና የኤልሳዕ አገልግሎት (1-8)
2. ከዮአስ እስከ ሰሜኑ ክፍል መማረክ (12-17)
3. ከሕዝቅያስ እስከ ይሁዳ መማረክ (18-25)

**1. የኤልያስ ወደ ሰማይ መወሰድና የኤልሳዕ አገልግሎት፡-** ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ ኤልሳዕ አገልግሎቱን በመቀጠል በእጁ ብዙ ተአምራት ተደርጎአል። ኤልሳዕ ስነቢይነት ከተጠራ ጀምሮ (1ነገ 19:19-21) ከኤልያስ ጋር ብዙ ጊዜ ቆይቶአል፤ ኤልያስ መወሰጃው ሲደረስም ሲለየው አልወደድም፤ ናፍቆቱ ኤልያስ ከነበረው መንፈስ ‹በእጥፍ ...› (2ነገ 2:9) እግዚአብሔርን ማገልገል ነው። ይህ ልመናው እንደተመለሰለት እገልግሎቱ ያመለክታል። በኤልያስና በኤልሳ በኩል እግዚአብሔር ያደረገው ተአምራት በሠንጠረዥ 16 ቀርቦአል።

ሠንጠረዥ16

**በኤልያስና በኤልሳ በኩል እግዚአብሔር ያደረገው ተአምራት[41]**

| ነቢዩና የተደረገው ተአምር | ክፍሉ |
|---|---|
| **ኤልያስ** | |
| *1. በቁራዎች ምግብ ቀረበለት* | *1ነገ 17:5-6* |
| *2. የመበለቲቱ ምግብ በዛ* | *1ነገ 17:12-16* |
| *3. የመበለቲቱ ልጅ ከሞት ተነሣ* | *1ነገ 17:17-24* |
| *4. መሠዊያውና መሥዋዕቱ በእሳት ተበላ* | *1ነገ 18:16-46* |
| *5. የአካዝያስ ወታደሮች በእሳት ተበሉ* | *2ነገ 1:9-14* |
| *6. የዮርዳኖስ ወንዝ ተከፈለ* | *2ነገ 2:6-8* |
| *7. በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ተወሰደ* | *2ነገ 2:11-12* |
| **ኤልሳዕ** | |
| *1. ዮርዳኖስ ወንዝ ተከፈለ* | *2ነገ 2:13-14* |
| *2. መራረው ምንጭ የሚጠጣ ሆነ* | *2ነገ 2:19-22* |
| *3. የመበለቲቱ ማድጋዎች ሁሉ በዘይት ሞሉ* | *2ነገ 4:1-7* |
| *4. የሱናመዊቱ መካን ሴት ልጅ መታቀፍ* | *2ነገ 4:8-17* |
| *5. ብላቴናው ከሞት ተነሣ* | *2ነገ 4:18-37* |

[41] ለተጨማሪ ማብራሪያ Life Application Bible, King James Version p.659

| | |
|---|---|
| *6. መርዛሙ ወጥ ጣፈጠ* | *2ነገ 4:38-41* |
| *7. የነቢያት ምግብ በዛ* | *2ነገ 4:42-44* |
| *8. ንዕማን ከለምጽ ነጻ* | *2ነገ 5:1-14* |
| *9. ግያዝ ለምጻም ሆነ* | *2ነገ 5:15-27* |
| *10. መጥረቢያው ተንሳፈፈ* | *2ነገ 6:1-7* |
| *11. የአገልጋዩ ዐይኖች ተከፍተው የእሳት ፈረሶችንና ሰረገሎች አየ* | *2ነገ 6:16-17* |
| *12. የሶርያ ሠራዊት ታወረ* | *2ነገ 6:8-23* |

እነዚህ ተአምራት በኤልያስና በኤልሳ በኩል የተፈጸሙት ጉልበታቸውን ካላንበረከኩ ከጥቂቶች በስተቀር በኣል የተባለው ጣዖት በምድረ እስራኤል በስፋት በሚመለክበት ዘመን ነበር። በኣል የእሳት፣ የዝናብ እና የምርት አምላክ ነው ይሉታል፤ የህፃናትንም መሥዕትነት ይፈልግ ነበር። የተደረጉት ተአምራት አብዛኛዎቹ አምላካቸው ‹በአል› በሰው እጅ የተሠራ ጣዖት መሆኑንና የእግዚአብሔርን ደግሞ ሕያው አምላክነት የሚገልጹና እግዚአብሔር ለህፃናት እንደሚያስብም የሚያስረዱ ናቸው።

**2. ከዮአስ እስከ ሰሜኑ ክፍል *መማረክ*:-** የሰማርያን በአሦራውያን እጅ መውደቅ በምዕ 17 እናነባለን። በሰሜኑ ክፍል የነበሩ ነገሥታት በእግዚአብሔር ተመዝነው ሁሉም ወድቀው (ቀለው) ተገኙ።

**3. ከሕዝቅያስ እስከ ይሁዳ *መማረክ*:-** የሰማርያ[42] ከተማ ለ3 ዓመት በአሦራውን ከተከበበች በኋላ በ722 ዓ.ዓ ተማረከች። የሰማርያን በአሦር ሥር መውደቅ በፖለቲካ ተንታኞች ከነገሥታት የኃይል ሚዛን መበላለጥ አንጻር ይተነተናል። ከእግዚአብሔር አንጻር ግን የቃል ኪዳኑ ሕዝብ ቃል ኪዳናቸውን ባለማክበራቸውና እግዚአብሔርን ባለመፍራታቸው የእርሱ መለኮታዊ ጥበቃ ከላያቸው (ከዙሪያቸው) እንደተነሳ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን ከፈሩ የይሁዳ ነገሥታት መካከል ሕዝቅያስና ኢዮስያስ ይገኛሉ።

**ሕዝቅያስ** አባቱ አካዝ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰው ነበር። ሕዝቅያስ ግን በእርሱ ዘመን ከነበሩት ነገሥታት በተለዬ ሁኔታ

[42] አሦር አብዛኛውን የእስራኤል ሕዝብ በምርኮ በመውሰድ በምትኩ ሌላ ሕዝብ አምጥቶ አሰፈረበት። ያህም ሕዝብ በሰሜን ከቀሩት እስራኤላውያን ጋር በመጋባት የተወለዱት ሳምራውያን ተባሉ።



እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር። ከአሦር ንጉሥ የመጣበትን የማስፈራሪያ ደብዳቤ በእግዚአብሔር ፊት በመዘርጋት ጸለየ (19:14) እግዚአብሔርም በኢሳይያስ በኩል መልስ ሰጠው፤ የሚረዳውንም መልአክ ላከለት (19:35)።

ኢዮስያስ ንጉሥ የሆነው በ8 ዓመቱ ነበር። እንደ ሕዝቅያስ ሁሉ ለእግዚአብሔር ቅንዓት ነበረው። ከእርሱ በፊት ለ55 ዓመት የነገሠው አባቱ በይሁዳ ምድር ያስጀመረውን ጣዖት አምልኮና ርኩሰት በማጽዳት ታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶ አመጣ። ይህ ተሐድሶ አስቀድሞ የጀመረው በራሱ ሕይወት እግዚአብሔርን በመፈለግ ነበር። ኢዮስያስ በ31 ዓመታት የንጉሥነት ዘመኑ እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ ተከተለ። ከኢዮስያስ ቀጥሎ የነገሠው ልጁ ኢዮአቂም እግዚአብሔርን የማይሰማ በነቢዩ ኤርሚያስ በኩል የመጣውን መልእክት የሚቃወም ሰው ነበር። 3 ወራት ከነገሠ በኋላ በባቢሎን ተማረከ። በ586 ዓ.ዓ ባቢሎን ይሁዳን ማረከች፤ የቤተ መቅደስ እቃዎችንም ወሰዱ።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ።**
ክርስቶስ የሚጠበቀው አዳኝ ስለሆነ ነቢዩ ኤልያስ የጌታን መምጣት በሚያውጀውና መንገዱን አዘጋጁ ብሎ ከኃጢአት ንስሐ ስለ መግባት በሚሰብከው በመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌነት ሲነገር (ማቴ 11:14፤ 17:10-12፤ ሉቃ 1:17፤ ሚክ 4:5) የሚጠበቀው ጌታ ክርስቶስ ነው።

**ዋና ትምህርት:-**
**እግዚአብሔር የሚምር የሚቆጣም አምላክ ነው።** የእግዚአብሔርን ነቢያት የሚንቅና ከኃጢአቱ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ለማይመለስ ሕዝብ (ሰው) መጨረሻው እጅግ አሳዛኝ እንደሚሆን ይህ መጽሐፍ ያስተምረናል። እግዚአብሔር ባለ ብዙ ምሕረት የሆነ አምላክ ነው። ለሰው ሁሉ የሚራራና ኃጢአተኞች ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ጊዜ የሚሰጥ ታጋሽ አምላክ ነው። ምክሩን በናቁና በኃጢአታቸው ለሚቀጥሉ ደግሞ ለእስራኤል እንዳደረገው ቁጣውን ይገልጻል። የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚገልጽ በተደጋጋሚ የተገለጸው ቃል (ሐረግ) እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እጅግ ተቆጣ ‹…ከፊቱም

ጣላቸው›[43] የሚለው ነው (17:18)፤ እንዲሁም 17:20፤22፤ 23:27)።

**እግዚአብሔርን እንደ አሕዛብ ልማድ ማመለክ ቅይጥነት ነው፡፡** በዚህ ዘመን በሕዝቡ ዘንድ ቅይጥ እምልኮ ተንሰራፍቶ ነበር (17:33)፡፡ ይህ ከፊል መታዘዝ ነው፡፡ እውነተኛውን ከሀሰተኛው ጋር ስመቀላቀል መሞከር ብርሃን ከጨለማ ጋር እንዲኖር መፈለግ ነው፡፡ ብርሃንና ጨለማ ደግሞ ይቀዋወማሉ፤ መጋጠም የላቸውም፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው (ወይም ንጉሥ) ለብቻው ይመዝናል፡፡ አብዛኛው ሕዝብ በአመጽ በሚሄድበት ዘመን እንኳ በፊቱ በትሕትና የሚሄደውን ያያል፤ ያውቃል፡፡ ከይሁዳ ነገሥታት በእግዚአብሔር መመዘኛ ‹መልካም አደረጉ› የተባሉም ነበሩ፡፡ ዳዊት መልካም ላደረጉት ነገሥታት መለኪያ እንደሆነ ሁሉ (1ነገ 15:5) ኢዮርብዓም ደግሞ ክፉ ነገር ያደረጉ መለኪያ ነው (2ነገ 15:9)፡፡ አንድ ሰው አባቶቹ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ቢሆኑ እርሱ ግን እንደ ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን በመከተል ምሕረትን ሊያገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ምርጫ ነው፡፡

[43] አዲሱ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ ‹...ከፊቱ አራቀ› ይላል፡፡



## ሠንጠረዥ 17
## የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት ዝርዝር

| ይሁዳ | | | | | እስራኤል | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ. | ንጉሥ | የነገሠበት ዓመት | ክፍሉ | በዘመኑ የነበረው ነቢይ[44] | ተ.ቁ. | ንጉሥ | ዓመት | ክፍሉ | በዘመኑ የነበረው ነቢይ[45] |
| 1. | ሮብአም | 17 | 1ነገ 14:21-31 | | 1. | ኢዮርብዓም | 22 | 1ነገ 11:26-40 | |
| 2. | አቢያም | 3 | 1ነገ 15:1-8 | | 2. | ናዳብ | 2 | 15:25-32 | |
| 3. | አሳ* | 41 | 15:9-24 | | 3. | ባኦስ | 24 | 15:27-16:7 | |
| 4. | ኢዮሳፍጥ** | 23 | 22:41-50 | | 4. | ኤላ | 2 | 16:8-14 | |
| 5. | ኢዮራም | 8 | 2ነገ 8:16-24 | አብድዩ | 5. | ዘምሪ | 7 ቀን | 16:9-20 | |
| 6. | አካዝያስ | 1 | 8:25-29 | | 6. | ታምኒ | 6 | | |
| 7. | ጎቶልያ | 6 | 11:1-20 | | 7. | ዘንበሪ | 12 | 16:16-17 | |
| 8. | ኢዮአብ* | 40 | 12:1-21 | ኢዩኤል | 8. | አክዓብ | 22 | 16:29-17:1 | ኤልያስ |
| 9. | አሜስያስ* | 29 | 14:1-21 | | 9. | አካዝያስ | 2 | 22:51-53 | ኤልያስ |
| 10. | ያዝያን (አዛርያ)* | 52 | 15:1-7 | | 10. | ኢዮራም | 12 | 2ነገ 3:1-27 | ኤልያስ |
| 11. | ኢዮአታም** | 16 | 15:32-38 | ኢሳይይስ/ ሚኪያስ | 11. | ኢዩ* | 28 | 9:1-10:36 | ኤልሳዕ |
| 12. | አካዝ | 16 | 16:1-20 | ›› | 12. | ኢዮአካዝ | 17 | 13:1-9 | ኤልሳዕ |
| 13. | ሕዝቅያስ** | 29 | 18:1-20:21 | ›› | 13. | ዮአስ | 16 | 13:10-25 | ኤልሳዕ |
| 14. | ምናሴ | 55 | 21:1-18 | ኢሳይይስ/ ናሆም | 14. | ኢዮርብዓም 2ኛ | 41 | 14:23-29 | ዮናስ/ አሞፅ |
| 15. | አሞጽ | 2 | 21:1926 | | 15. | ዘካሪያ | 1/2 | 15:8-12 | ሆሴዕ |
| 16. | ኢዮስያስ** | 31 | 22:1-23:30 | ሶፎንያስ/ ኤርሚያስ | 16. | ሰሎም | 1/12 | 15:10-18 | ሆሴዕ |
| 17. | ኢዮአክስ | 1/4 | 23:31-34 | ኤርሚያስ | 17. | ምንሔም | 10 | 15:14-22 | ሆሴዕ |
| 18. | ኢዮአቄም | 11 | 23:35-24:7 | ዕንባቆም/ ኤርሚያስ | 18. | ፋቁስያስ | 2 | 15:23-28 | ሆሴዕ |
| 19. | ዮአኪን | 1/4 | 24:8-17 | ኤርሚያስ | 19. | ፋቁሔ | 20 | 15:25-31 | ሆሴዕ |
| 20. | ሴዴቅያስ | 11 | 24:18-20 | ኤርሚያስ | 20. | ሆሴዕ | 9 | 17:1-6 | ሆሴዕ |

* በከፊል መልካም ያደረጉ ነገሥታት፤ ** መልካም ያደረጉ

[44] John F. Walvoord and Roy B. Zuck, p.513
[45] Ibid.

# ዜና መዋዕል

ዜና መዋዕል ቀዳማዊና ዜና መዋዕል ካልዕ ተብለው የሚታወቁት መጻሕፍት በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹ዜና መዋዕል› ተብለው አንድ መጽሐፍ ናቸው። በሁለቱ መጻሕፍት ያሉት ስዎችና ድርጊቶች በሳሙኤልና በነገሥት መጻሕፍት ካሉት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ለምሳሌ የሳሙኤልና ነገሥት መጻሕፍት ንጉሥ ዳዊት ስላሳለፈው የስደት ሕይወትና ስላደረጋቸው ጦርነቶች ይበልጥ ሲናገሩ ዜና መዋዕል ደግሞ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት በተደረገው ዝግጅት ላይ ያተኩራሉ። በተጨማሪም የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ስላለው ታሪክ በዜና መዋዕል መጻሕፍት ስማቸው የተጠቀሰው ነገሥታት የደቡቡ እስራኤል (ይሁዳ) ነገሥታት ብቻ ናቸው። ሠንጠረዥ 18 በመጽሐፈ ሳሙኤል፤ ነገሥትና ዜና መዋዕል መካከል ያለውን ተወራራሽነት በአጠቃላይ ሁኔታ ያሳያል።

ሠንጠረዥ 18

የሳሙኤል፤ ነገሥትና ዜና መዋዕል መጻሕፍት ተወራራሽነት

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 ሳሙኤል | 2 ሳሙኤል | 1 ነገሥት | 2 ነገሥት |
| - | 1 ዜና መዋዕል | 2 ዜና መዋዕል | |

ሁለቱ የዜና መዋዕል መጻሕፍት ከአዳም ጀምሮ እስራኤል በባቢሎን እስከተማረከችበትና ምርኮኞች መመለስ እስከጀመሩበት ጊዜ ድረስ ያለውን ታሪክ ባጭሩ ይገልጻሉ። ዜና መዋዕል ቀዳማዊ ከአዳም እስከ ንጉሥ ዳዊት የነበረውን ጊዜ ሲሸፍን ቀሪው ታሪክ በዜና መዋዕል በካልዕ ይገኛል።

የዜና መዋዕል መጻሕፍት ከምርኮ ለተመለሱ እስራኤላውያን የቀደመውን ታሪክ ባጭሩ ለማሳወቅ፤ ስለደረሰባቸውም መከራና ምርኮ ለማጽናናትና የእግዚአብሔርን አሠራር ለማስተማር የተጻፉ ናቸው። ከአዳም ጀምሮ (1ዜና 1፡1) ምርኮው እስካበቃበት ጊዜ ድረስ (2ዜና 36፡22-23) ያለውን የብዙ ዓመታት ታሪክ ባጭሩ በማቅረብ በዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ገዥነት እንዲሁም ለእስራኤል ሕዝብ ያለውን ዓላማ ያስረዳሉ። የዜና መዋዕል ቀዳማዊ ዳሰሳ ቀጥሎ ቀርቦአል።



## ምዕራፍ 13፡-

# ዜና መዋዕል ቀዳማዊ

**ጸሐፊ፡-** ካህኑ ዕዝራ። ይህ ጸሐፊ በሳሙኤል (1ዜና 29፡29)፤ በኢሳይያስ (2ዜና 32፡32) እና በሌሎች (2ዜና 9፡29፤ 12፡15፤ 16፡11፤ 20፡34፤ 25፡26፤ 33፡19) የተጻፉ ምንጮችን ተጠቅሞአል።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 450-425 ዓ.ዓ.፤ (ታሪኩ ከ1010-530 ዓ.ዓ. ያለውን ጊዜ ይሸፍናል)።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** ዜና ማለት ዘገባ፤ ወሬ፤ መረጃ፤ ታሪክ ሲሆን መዋዕል ደግሞ ዘመን፤ ዕድሜ ማለት ነው። ስለዚህ ዜና መዋዕል ማለት የዘመናት ታሪክ ወይም የዕለታት ዘገባ ነው።

**ዋና ስዎች፡-** ዳዊት፤ ናታን፤ ቤርሳቤህ።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** የዳዊት ስም 183 ጊዜ ተጽፎአል።

**ዋና ሀሳብ፡-** በዚህ ዘመን የነበረውን ሁኔታ መተረክ። የዜና መዋዕል መጻሕፍት በቤተ መቅደሱ መሠራት፤ የአምልኮ ሥርዓትና የካህናት አገልግሎት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹አቤቱ፥ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል፤ ክብርም፤ ድልና ግርማ ለአንተ ነው፤ አቤቱ፤ መንግሥት የአንተ ነው፤ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ። ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው፤ አንተም ሁሉን ትገዛለህ፤ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው፤ ታላቅ ለማድረግ፤ ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት በእጅህ ነው። አሁንም አንግዲህ፤ አምላካችን ሆይ፤ እንገዛልሃለን፤ ለክቡር ስምህም ምስጋና እናቀርባለ› (29፡11-12)።

**አከፋፈሉ፡-** መጽሐፉን በታሪኩ ቅደም ተከተል በ3 በመክፈል እንመለከታለን።

1. የትውልድ ሐረግ ከአዳም እስከ ዳዊት (1-9)
2. የዳዊት መቀባትና የንጉሥነት ዘመን (10-28)
3. ቤተ መቅደስ የመሥራት ዝግጅት (22-29)

**1. የትውልድ ሐረግ ከአዳም እስከ ዳዊት፡፡** ይህን የትውልድ ሐረግ ተከትለን ስንሄድ መሢሐ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን መስመር እናገኛለን፡፡

ከአዳም እስከ ዳዊት የዘር ሐረግ

| **አዳም** (1) | **አብርሃም** (21 |
|---|---|
| ሤት (2) | ይስሐቅ (22) |
| ሄኖስ (3) | ያዕቆብ (23) |
| ቃየን (4) | ይሁዳ (24) |
| መላልኤል (5) | ፋሬስ (25) |
| ያሬድ (6 | አስሮም (26) |
| ሄኖክ (7) | አርኒ (27) |
| ማቱሳላ (8) | አሚናዳብ (28) |
| ላሜህ (9) | ነአሶን (29) |
| ኖኅ (10) | ስልሞን (30) |
| ሴም (11) | ቦዔዝ (31) |
| አርፋክስድ (12) | እሴይ (33) |
| ቃየን (13) | **ዳዊት** (34) |
| ሳላ (14) | |
| አቤር (15) | |
| ፋሌቅ (16) | |
| ራጋው (17) | |
| ሴሮህ (18) | |
| ናኮር (19) | |
| ታራ (20) | |
| **አብርሃም** (21) | |

2. ***የዳዊት መቀባትና የንጉሥነት ዘመን፡፡*** ዳዊት ንጉሥ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ያደረገው አንድ ታላቅ ተግባር የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ማምጣቱ ነበር (13-17)፡፡ የዖዛ መቀሰፍ አስደንጋጭ ታሪክ ነው፡፡ ዳዊት ከዚህ በመማር እንደ ሕጉ እንዲፈጸም አደረገ (15፡2፤13-15)፡፡ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመሥራት መልካምን ነገር አሰበ፡፡ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤትን እንደማይሠራ ተነገረው (17፡4)፡፡ እግዚአብሔር ግን ለዳዊት ቤት እንደሚሠራለት ቃል ኪዳን ገባለት (17፡10-12)፡፡ ይህ እግዚአብሔር የሚሠራው ቤት ከትውልዱ ለዘላለም ንጉሥ የሚሆን ዘር የመምጣቱ ተስፋ ነው፡፡ ይህ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ የዘላለም ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

3. ***ቤተ መቅደስ የመሥራት ዝግጅት፡፡*** ዳዊት ቤተ መቅደስ ለሚሠራበት መሬት ገዛ፤ ዕቃ አከማቸ፤ ሕዝቡንም አነሣሳ፤



ሠራተኞችንም መደበ (22)፡፡ በመቅደሱ የሚያገለግሉትንም ሌዋውያን፤ ዘማሪዎች፤ የተለያዩ አገልጋዮች ሾመ (23-27)፡፡

**ክርስቶስ በዜና መዋዕል ቀዳማዊ መጽሐፍ፡፡**
ዙፋኑ ለዘላለም የሚጸና የዳዊት ልጅ (17፡13-14)፤ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን የሚወርስ ለዘለላም የሚነግሠው፤ ለመንግሥቱ መጨረሻ የሌለው ክርስቶስ ነው (ሉቃ 1፡32-33)፡፡

**ዋና ትምህርት፡-**
***የእግዚአብሔርን ሥራ እግዚአብሔር በሚመርጠው መንገድ መሥራት፡፡*** በእግዚአብሔር አገልግሎት ምን እንደምንሠራ ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደምንሠራውም መጠንቀቅ ይገባል፡፡ እግዚአብሔርን ሊያገለግል የተነሣ ዖዛ ዓይነት ሰው ለምን ይቀሰፋል; ዖዛ ሊወድቅ ያለውን ታቦት እንዳይወድቅ እጁን ዘርግቶ ለመደገፍ መሞከሩ ሰው የሚያደርገው ‹ቅን› ተግባር ይመስላል፡፡ ስህተቱ የተጀመረው በእጅ በመንካቱ ላይ ሳይሆን ገና ከጅማሬው የእግዚአብሔርን ታቦት በእንስሳት ለመውሰድ ማሰቡ ላይ ነው፡፡ ስለ ታቦቱ መጓጓዝ ሕጉ የሚያዘው በመሎጊያ ውስጥ ገብቶ በካህናት ትከሻ እንዲሆንና ማንም በእጁ እንዳይነካው ነው (ዘጸ 25፡13-14፤ ዘኍ 4፡15፤ 1ዜና 15፡2፤13፤15)፡፡ ስለሆነም መልካሙን ነገር ስህተት በሆነ መንገድ ማድረግ አለመታዘዝ ነው፡፡ አለመታዘዝ ደግሞ ቢዘገይም ቅጣት ሳይኖረው አይቀርም፡፡ የእግዚአብሔር አገልግሎት መከናወን ያለበት እግዚአብሔር በሚወደው መንገድ ነው፡፡

**እግዚአብሔር ለውን ስለ መልካም *ሥራው* ብቻ ሳይሆን ለእርሱ መልካም ስለማሰቡም ብድራት ይከፍለዋል፡፡** ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ማሰቡ መልካም ነው ተብሏል፡፡ ቤቱን የሠራው ግን ሰሎሞን ነበር፡፡ ስለ መልካም ሀሳቡ ግን እግዚአብሔር ለዳዊት ‹ቤት› እንደሚሠራለት ቃል ኪዳን ገባለት፡፡

**እግዚአብሔርን ማወቅ፤ ማምለክ፤ *መፈለግና* ማገልገል፡፡** ዳዊት ለልጁ ለሰሎሞን የመከረው (1ዜና 28፡9-10) በዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን ስለ፡-

- ማወቅ፡- እግዚአብሔርን እወቅ
- ማምለክ፡- በፍጹም ልብና በልብ ፈቃድ ማምለክ
- መፈለግ፡- ፈልገው ይገኝልሃል
- በትጋት ማገልገል፡- ለሥራው መመረጠህን በሥራ ብርታት ግለጽ በማለት ነበር፡፡ ይህ ምክር ለዛሬም ጽኑ ነው፡፡

## ምዕራፍ 14፡-

# ዜና መዋዕል ካልዕ

**ጸሐፊው፡-** ካህኑ ዕዝራ።

**ጊዜው፡-** 450-425 ዓ.ዓ.

**ስያሜው፡-** በዜና መዋዕል ቀዳማዊ የተጀመረው ‹ዘገባ› ተከታይ ታሪክ ስለሆነ።

**ዋና ሰዎች፡-** ሰሎሞን፤ የይሁዳ ነገሥታት

**ዋና ሀሳብ፡-** ዜና መዋእል ካልዕ ስለ መጀመሪያው ቤተ መቅደስ ስለተሠራበት ሁኔታ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ በይሁዳ ስለነበረው የመንፈሳዊ ሕይወት መዳከምና ቅይጥነት በመጨረሻም ሕዝቡ እንዴት በባቢሎን እንደተማረከና ቤተ መቅደሱም እንደ ፈረሰ ያስረዳል።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ‹…የእግዚአብሔር ቤት› የሚለው ሐረግ 69 ጊዜ

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፤ ፊቴንም ቢፈልጉ፤ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፤ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ› (7፡14)።
- ‹የአባቶቻቸውም አምላክ እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለማደሪያው ስላዘነ ማለዳ ተነሥቶ በመልእክተኞቹ እጅ ወደ እነርሱ ይልክ ነበር። እነርሱ ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ ላይ እስኪወጣ ድረስ፤ ፈውስም እስከማይገኝላቸው ድረስ፤ በእግዚአብሔር መልእክተኞች ይሳለቁ፤ ቃሉንም ያቃልሉ፤ በነቢያቱም ላይ ያፌዙ ነበር› (36፡15-17)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን በ3 በመክፈል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

1. ሰሎሞን ከንግሥናው እስከ ሞቱ (1-9)
2. የይሁዳ ነገሥታት (10-36፡21)
3. የይሁዳ መማረክና የቂሮስ አዋጅ (36፡22-23)



**1. ሰሎሞን ከንግሥናው እስከ ሞቱ፡-** ሰሎሞን በተሰጠው ታላቅ ጥበብ ቤተ መቅደሱን ሠራ (2-6)። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱ ሲመረቅ በዚያ ቦታ የሚደረገውን ጸሎት እግዚአብሔር እንዲሰማ ጸለየ እግዚአብሔርም ለሰሎሞን ተገልጦ ‹‹በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፤ ፊቴንም ቢፈልጉ፤ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፤ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ› (7፡14) በማለት ተስፋ ሰጠ። የሰሎሞንን ዝና የሰማች የሳባ ንግሥት ሰሎሞንን ጎበኘች (9)።

**2. የይሁዳ ነገሥታት፡-** ከሮብዓም እስከ አካዝ 20 ነገሥታት ተጠቅሰዋል። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ መልካም ጅማሬ ነበራቸው። ንጉሡ **አሳ** ሲጀምር በእግዚአብሔር የታመነ ሰው ነበር (14-16)። የጣዖት መሠዊያዎችን ከይሁዳ አስወገደ፤ መንፈሳዊ መነቃቃትን አመጣ። ሆኖም አሳ በመጨረሻው ዘመኑ በእግዚአብሔር መታመኑን ትቶ በሶሪያ ንጉሥ ተደገፈ (16፡7)። ድርጊቱ በእግዚአብሔር ፊት መልካም አለመሆኑን የነገረውን ነቢዩን አናኒን ወደ ወኅኒ ላከ፤ በታመም ጊዜ ለፈውሱ በባለ መድኃኒተኞች ታመነ እግዚአብሔርንም አልፈለገም (16፡12-13)። አሳ መጨረሻው እንደ ጅማሬው ያላማረለት ንጉሥ ነው።

**ኢዮሳፍጥ፡-** (17-20) ሲጀምር እግዚአብሔርን በመታዘዝ ነበር። መንፈሱን ወደ እግዚአብሔር አነሳ (17፤6)። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማር አደረገ (17፡7-9)። ሆኖም ጠላት በተነሣበት ጊዜ አካዝን በጦርነት በመርዳት ወዳጅ ሲያደርገው ፈለገ፤ በእግዚአብሔርም አልታመነም (18-19)። እግዚአብሔር በነቢዩ ኢዩ በኩል ገሰጸው (19፡2)። ኢዮሳፍጥ ተግሳጹን ተቀብሎ ቀሪውን ዘመኑን በእግዚአብሔር ታመነ። ጠላት ሲመጣበትም ወደ እግዚአብሔር በመጮህ ‹ሀይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው አለ› (20፡5-12)። እግዚአብሔርም ታደገው።

**በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ** ሰዎች በብዙ ቁጥር ንስሐ በመግባት፤ የኃጢአት መንገዳቸውን በመተውና በመመለስ እግዚአብሔርን ያመለኩበት ዘመን ነበር። ሠንጠረዥ 19 የተጠቀሱት የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና መንፈሳዊ መነቃቃቶችና ተሐድሶዎች ናቸው።

## ሠንጠረዥ 19

### መንፈሳዊ መነቃቃቶችና ተሐድሶዎች በብሉይ ኪዳን

| ለተሀድሶው መሪ | የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | ሕዝቡ የነበሩበት ውድቀት | የመጣው ተሐድሶ |
|---|---|---|---|
| ሳሙኤል | 1ሳሙ 7፡1-13 | ጣዖትን ማምለክ፤ | ጣዖቶቻቸውን አፈረሱ፤ እግዚአብሔርን ለመከተል ወሰኑ |
| ዳዊት | 2ሳሙ 6 | --- | የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም አመጣ፤ እግዚአብሔርን አመሰገነ |
| ኢዮሳፍጥ | 2ዜና 20 | --- | በእግዚአብሔር ታመነ፤ እርሱም ታላቅ ማዳን አደረገላቸው |
| ሕዝቅያስ | 2ዜና 29-31 | ----- | ቤተ መቅደሱን አጸዳ፤ ጣዖታትን አስወገደ፤ |
| ኢዮስያስ | 2ዜና 34-35 | --- | እግዚአብሔርን ፈለገ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዘ |
| ዕዝራ | ዕዝ 9-10 | ----- | በእምነታቸው ቅይጡን ሁሉ አስወገዱ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አደሱ |
| ነህምያ | ነህ 8-10 | --- | የእግዚአብሔርን ቃል ሰሙ፤ ንስሐ ገቡ፤ በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን ለመከተል ቃል ኪዳን አደሱ |

**3. የይሁዳ መማረክና የቂሮስ አዋጅ፡-** የይሁዳ ሰዎች እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ባለመስማታቸው ተማርከው ከምድራቸው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። ናቡከደነፆር ይሁዳን ሲማርክ ‹የእግዚአብሔርንም ቤት ዕቃ ሁሉ ታላቁንና ታናሹን፥ የእግዚአብሔርንም ቤት መዝገብ፤ የንጉሡንና የአለቆቹን መዝገብ፥ እነዚህን ሁሉ ወደ ባቢሎን ወሰደ› (36፡18)።

**ክርስቶስ በዜና መዋዕል ካልዕ መጽሐፍ፡፡**
ሰሎሞን ያሠራው ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ማደሪያ; በአማኙ ልብ በእምነት የሚኖረው ክርስቶስ (ኤፌ 3፡16-17፤ 2ቆሮ 6፡16)::

**ዋና ትምህርት፡-**
**አምልኮ ሥርዓት ብቻ ሲሆን ውድቀትን ያስከትላል።** በይሁዳ ቤተ መቅደስ ተሠርቷል፤ የአምልኮ ሥርዓቱም አልተቋረጠም፤ የሕዝቡ ልብ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከእግዚአብሔር የራቀ ነበር። የእግዚአብሔር ጥበቃ ከላያቸው ተነሣ። ስለዚህ ለምርኮ አሳልፎ ሰጣቸው።



**መጨረሻን ማሳመር።** ከዚህ በፊት አጀማመራቸው መልካም ሆኖ **ፍጻሜያቸው ያላማረላቸውን መሪዎች** ጌዴዎንን፤ ሶምሶንንና ሰሎሞንን በኃጢአታቸውም ፈጥነው ንስሐ ከመግባት ይልቅ በክፋት ሲቀጥሉ ተመልክተናል። ሰዎች በእግዚአብሔር ስም ያገኙት መከናወን፤ ትልቅነት፤ ሀብት፤ ድል ወደ ትዕቢት ሲለወጥ አይተናል። በዚህም መጽሐፍ እስከ መጨረሻው እግዚአብሔርን በመፍራት ያልኖሩ ሰዎች ኢዩንና ዖዝያን እናገኛለን። **ኢዩ** (2ዜና 10፡1-36) የበኣል አምልኮ እንዲጠፋ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት የበኣል አምልኮን ከእስራኤል ምድር ያጠፋ ንጉሥ ነው። ስለታዘዘም ተባረከ (10፡30)። ነገር ግን በሙሉ ልቡ እግዚአብሔርን አልተከተለም (10፡31)። እንዲሁም **ዖዝያን** (26) ጅማሬው እጅግ ያማረ ንጉሥ ነበር። ለረጅም ዓመታት ገዛ፤ ሀብትም በዝቶለት ነበር። በመጨረሻው ዘመኑ ግን ታላቅ ስህተት አደረገ። ንጉሥ ሆኖ ሳለ እንደ ካህን ዕጣን ሲያጥን ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፤ የካህናትን ምክር አልሰማም። ባስመታዘዙም በለምጽ ተመታ።

**ራስን አዋርዶ እግዚአብሔርን መፈለግ።** በ2ዜና 7፡14 የተጠቀሰው እጅግ ታላቅ ተስፋ የያዘ ጥቅስ ነው። ንስሐ የእግዚአብሔርን ምሕረት ይቀድማል። የምድር ፈውስ በእግዚአብሔር ሕዝብ በኩል ይገኛል።

# ምዕራፍ 15:-

# መጽሐፈ ዕዝራ

**ጸሐፊው:-** ካህኑ ዕዝራ ነው። በአንደኛ መደብ ራሱን ይጠራል (7:28-9:15)። ከተለያዩ የታሪክ መዛግብት መረጃዎችን ተጠቅሞአል (2:1-70፤ 4:7-16፤ 7:27-9:15)።

**ተጻፈበት ጊዜ:-** ከ450-444 ዓ.ዓ.። መጽሐፉ 538-457 ዓ.ዓ. ያለውን ታሪክ ይሸፍናል። በምዕ 1- 6 እና በምዕ 7-10 መካከል የ58 ዓመት ያህል ልዩነት አለ።

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በመጽሐፉ ውስጥ ጎልቶ ስሙ በተጠቀሰው ዕዝራ ነው።

**ዋና ሰዎች:-** ዕዝራ፤ ቂሮስ፤ ኢያሱ (ሊቀ ካህኑ)፤ ዘሩባቤል

**ተደጋጋሚ ቃል:-** እንደ ዜና መዋዕል መጻሕፍት ሁሉ በዕዝራ መጽሐፍም ‹የእግዚአብሔር ቤት› የሚለው ሐረግ 53 ጊዜ ያህል ተገልጾአል።

**ዋና ሀሳብ:-** መጽሐፈ ዕዝራ ከምርኮ በኋላ በቤተ መቅደሱ እንደገና መሠራትና የሕዝቡ ሕይወት በንስሐ መታደስ ላይ ያተኩራል። ይህ መጽሐፍ የአይሁድን የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ከምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ይገልጻል። ቅሬታዎች ከምርኮ መመለስ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ መፈጸሙን ያሳያል።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች:-**

- ‹በኤርምያስም አፍ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በመጀመሪያው ዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ አስነሣ፤ እርሱም በመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ (1:1)።
- ‹በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ያሳምር ዘንድ እንደዚህ ያለውን ነገር በንጉሡ ልብ ያኖረ፤ በንጉሡም በአማካሪዎቹም በንጉሡም ኃያላን አለቆች ሁሉ ፊት ምሕረቱን ወደ እኔ የሳበ የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ። እኔም በላዬ ባለችው በአምላኬ በእግዚአብሔር እጅ በረታሁ፤ ከእኔም ጋር እንዲወጡ ከእስራኤል ዘንድ አለቆችን ሰበሰብሁ (7:27-28)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** ከምርኮ መመለስ ጋር በተያያዘ በ2 መክፈል ይቻላል።



1. የመጀመሪያው መመለስ (1-6)
2. ሁለተኛው መመለስ (7-10)

**1 የመጀመሪያው መመለስ:-** የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ እግዚአብሔር የሕዝቡን መንፈስ አስነሳ (1:5)፤ ንጉሥ ቂሮስም አዋጅ አወጣ (2ዜና 36-22-23፤ ዕዝ 1-14)።

በ537 ዓ.ዓ. በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ትእዛዝ የተመለሱ 50000 ያህል ብቻ ነበሩ። ይህ ቁጥር በዚያን ዘመን በባቢሎን ይኖሩ ከነበሩት 2 ሚሊዮን የሚገመቱ[46] አይሁድ አንጻር ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት ጥቂት መሆናቸውን ያሳያል። በዘሩባቤል መሪነት የተመለሱት መሠዊያውን በመሥራት ጀመሩ። ከዚያም የቤተ መቅደሱን መሠረት ጣሉ፤ ታላቅም ደስታ ሆነ። የመጀመሪያው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በነበረበት ሥፍራ ላይ ሠሩ። የቀደመውን ቤተ መቅደስ የሚያውቁ የቀደሙት ሽማግሌዎች አለቀሱ (ሕዝ 3:8-13)፤ ሰማርያውያን በሥራው እንዲካፈሉ ጠይቀው ስላልተፈቀደላቸው ሥራው እስኪቆም ድረስ ተቃወሟቸው። በሐጌና ዘካርያስ ትንቢት በ520 ዓ.ዓ. ሥራው እንደገና ተጀመረ፤ ሥራው በ516 ዓ.ዓ. አለቀ (6:14-15) ።

ምርኮው የሆነው በ605 ዓ.ዓ.፤ 597 እና 586 በ3 ደረጃ ነበር። መመለሳቸውም በ536፤ 458 እና 445 ዓ.ዓ. በ3 ደረጃ ነው። ሠንጠረዥ 20 እስራኤላውያን ከምርኮ የተመለሱባቸውን ጊዜያትና ሁኔታ ያሳያል።

ሠንጠረዥ 20

**የእስራኤላውያን ከምርኮ መመለስ**

| ዘመን (ዓ.ዓ.) | የፋርስ ንጉሥ | የተመለሱት ብዛት | የተመለሱት መሪ | ጥቅስ | ያከናወኑት |
|---|---|---|---|---|---|
| 537 | ቂሮስ | 50000 | ዘሩባቤል | ------ | ቤተ መቅደሱን ሠሩ፤ ተቃዋሚዎች ለ20 ዓመት ያህል ሥራውን አስቁመው ነበር |
| 458 | አርጤክሴስ | 2000 ወንዶችና ቤተሰቦቻቸው | ዕዝራ | ------ | የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ታደሰ፤ አምልኮ በቤተ መቅደስ ተጀመረ |
| 445 | አርጤክሴስ | ጥቂቶች | ነህምያ | ------ | የኢየሩሳሌም ቅጥር ታደሰ፤ መንፈሳዊ ተሐድሶም ተከተለ |

[46] Nelson's Student Bible Handbook (2007), Thomas Nelson Inc., Nashville, p.55.

2. ሁለተኛው መመለስ፡- ቤተ መቅደሱ ከተጠናቀቀ ከ58 ዓመታት ያህል በኋላ ዕዝራ ሁለተኛውን ተመላሽ ሕዝብ መርቶ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ። ዕዝራ ከአሮን ወገን የሆነ ካህን (7፡1-5) እና ጸሐፊ ነበር (7፡6፤21)። ዕዝራ ልቡን አዘጋጀ፤ እግዚአብሔርን ፈለገ፤ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ቃል እንዲመለሱና ቃሉን እንዲታዘዝ አጥብቆ አስተማረ (7፡6፤10)። ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የሚያዝንና ሕዝቡን በንስሐ የመራ ሰው ነው (9-10)። የመዝሙር 119 ጸሐፊ ነው። እንዲህ ዓይነት ታላቅ ሥራ የተሠራው የአምላኩ እጅ በእርሱ ላይ ስለ ነበረች ነው (7፡6፤9)። ሠንጠረዥ 21 በዕዝራና ነህምያ ላይ በነበረችው የእግዚአብሔር እጅ የተነሣ የተከናወነውን ሥራ ያሳያል።

ሠንጠረዥ 21
መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ በዕዝራና ነህምያ ላይ

| | |
|---|---|
| ዕዝ 7፡6 - | ዕዝራ የጠየቀውን ሁሉ ንጉሡ ሰጠው |
| ዕዝ 7፡9 - | ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም በ4 ወር ደረሰ |
| ዕዝ 7፡28 - | ዕዝራ በንጉሡና በአማካሪዎቹ ፊት ሞገስ አገኘ፤ ከእስራኤልም አብረውት የሚሄዱትን ሰበሰበ፤ በረታ |
| ዕዝ 8፡18 - | ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱ ሌዋውያንና አገልጋዮችን አገኘ |
| ዕዝ 8፡22 - | እንደ ጸለየው በመንገድ ሁሉ የእግዚአብሔር እጅ ለመልካም ሆነ |
| ዕዝ 8፡31 - | በመንገድ ከጠላትና ከሚያሸምቅ ሰው እጅ ዳነ |
| ነህ 2፡8 - | ነህምያ ለመንገድ ሁሉ የጠየቀውን ንጉሥ አርጤክስስ ሰጠው |

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ዕዝራ።**
እስራኤል ሁሉ እንዳይጠፋ ቅሬታን ያስቀረ አምላክ (9፡8)፤ ቅሬታዎች የተመረጡት በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ነው (ኤፌ 1፡5፤ ሮሜ 11፡5-6)።

**ዋና ትምህርት፡-**
**እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ያለመክልከል በሥልጣን ይፈጽማል።** ከ70 የምርኮ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምድራቸው መልሷል (ኤር 29፡10-14)። ይህን ለመፈጸም በየትኛውም አገር፤ በምንም ዓይነት የሥልጣን ደረጃ ላይ ያለን ማንኛውንም ሰው፤ በእርሱ የሚያምኑትንም ሆነ የማያምኑትን ይጠቀማል፤ ያዛል። እግዚአብሔር ሀሳቡን ለመፈጸም ዘሩባቤልንና ዕዝራን እንደተጠቀመ ሁሉ ቂሮስንና አርጤክሴስን ተጠቅሟል።



እግዚአብሔር የቂሮስን መንፈስ አነሣሳ (1፡1)። ከናቡከደነፆር ወደ ቂሮስ (ከባቢሎን ወደ ፋርስ) መንግሥት ሲቀየር ቂሮስ እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ መፍቀዱ ከመንግሥቱ አሠራር አንጻር የፖሊሲ ለውጥ ማድረጉ ይሆናል። እግዚአብሔር ግን መንግሥታት የፖሊሲ ለውጥ ቢሉትም በእነርሱ አማካይነት የዘላለም ሀሳቡን ያለ ምንም መከልከል በሥልጣን ሲፈጽም ኖሯል።[47] መጽሐፍ ‹የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል› (ምሳ 21፡1) ይላልና።

**እግዚአብሔር አፍርሶ መሥራት የሚችል አምላክ ነው።** በኤርምያስ 18፡14 በሸክላ ሠሪው ምሳሌ እንደተነገረው ይሁዳ ከነበረበት ምድር ፈረሰ፤ ተበተነ። የተሰፋው ዘመን ሲደረስ እግዚአብሔር እንደገና ሰበሰው፤ የፈረሰውም ተሠራ። ፍጥረትን ከምንም የፈጠረ አምላክ የፈረሰውንም እንደገና ይሠራል።

[47] Nelson's Student Bible Handbook (2007), p.51. "The Babylonians had held the Jewish people captive for more than 50 years, but the Persians had a different foreign policy. They believed in letting their subject nations live in their own native regions under the authority of a ruling governor. They allowed the Jewish people to return to Jerusalem in several different stages".

## ምዕራፍ 16፡-

# መጽሐፈ ነህምያ

**ጸሐፊው፡-** ነህምያ ነው። በ1፡1 ‹የነህምያ ቃል› ስለሚልና ብዙ ቦታ በአንደኛ መደብ እኔ እያለ ስለሚናገር ነህምያ እንደጻፈው ይታሰባል።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 445-425 ዓ.ዓ.። መጽሐፉ በኢየሩሳሌም የተፈጸመውን የ25 ዓመት ታሪክ ይገልጻል።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በጸሐፊው በነህምያ

**ዋና ሰዎች፡-** ነህምያ፣ ዕዝራ፣ ሰንበላጥ፣ ጦቢያ

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ፡-** ‹ቅጥር› 33 ጊዜ ያህል፣ መሥራት /እንሠራለን 20 ጊዜ ያህል፤

**ዋና ሀሳብ፡-** የፈረሰን ቅጥር ማደስ ነው። እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል አስቦ የተማረከውን ሕዝብ እንደመለሰና በእርሱ ምሪትና ኃይል የፈረሰው የኢየሩሳሌም ቅጥር፣ የሕዝቡም መንፈሳዊ ሕይወት ታደሰ።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹…እግዚአብሔርም ለኢየሩሳሌም አደርገው ዘንድ በልቤ ያኖረውን …› (2፡12)።
- ‹…ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ› (2፡17)

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** ከሁለቱ ዓይነት አድሳቶች አንጻር በ2 መክፈል ይቻላል።

1. ቅጥሩን ለማደስ መዘጋጀትና መሥራት (1-7)
2. መንፈሳዊ ሕይወትን ማደስ (8-)

**1. ቅጥሩን ለማደስ መዘጋጀትና መሥራት፡-** ነህምያ ከወንድሙ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ በሮቿም ስለመቃጠላቸው፣ ሕዝቡም በታላቅ ቁስቁልና ስለመኖራቸው ከሰማ በኋላ መጸለይ ጀመረ (1፡4-11)። ነህምያ በሱሳ የንጉሥ ጠጅ አሳላፊ ነበር። የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት እግዚአብሔር በንጉሡ ፊት ሞገስ ሰጠው (2፡1-8)። ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ዕዝራ ከመጣ ከ12 ዓመታት ያህል በኋላ ነበር (ዕዝ 7፡8 እና ነህ 2፡1)። እንደመጣም መረጃ ሰበሰበ



(2፡12-17)፣ ሕዝቡን ለሥራ አነሣሳ (2፡9-3፡)። በሥራው ላይ ከውጭ (4፡1-9፣ 6፡1-19) እና ከውስጥ (4፡10-5፡1) ተቃውሞ ቢነሣም ጨክነው ሠሩ፣ በ52 ቀን ውስጥ ጨረሱ (6፡15)። ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር ኃይል እንደተሠራ ታወቀ። ነህምያ ያገለገለው እንደ ሕዝብ መሪ፣ ወታደር፣ ሠራተኛ (ግንበኛ)፣ የጸሎት ሰው ሆኖ ነበር።

ነህምያ የእቅድና የተግባር ሰው ነበር። ጥቂት በዕቅድ የሠሩ ሰዎች ምሳሌ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ 22 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 22

በዕቅድ ስለ መሥራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

| ሠራተኛው | ሥራው |
|---|---|
| ነህምያ | ቅጥሩን ለማደስ ጸለየ፣ ዝግጅት አደረገ፣ የፈረሰው ጎበኘ፣ ሕዝቡን ለሥራ አነሣሳ፣ አስማራ፣ ሥራው በ52 ቀን አለቀ። |
| ኖህ | ከእግዚአብሔር መርከብ እንዲሠራ ትዕዛዝ ተቀበሎ ለ120 ዓመታት ሠርቶ ጨረሰ |
| ዳዊት | ለእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት በልቡ ባሰበው መሠረት ለሥራው የሚያስፈልገውን ሁሉ አከማቸ፣ ለሰሎሞን ሰጠው |
| ዮሴፍ | ለሚመጣው 7 ዓመት ራብ አስቀድሞ እህል በየከተማው እንዲከማች አደረገ፣ ሕዝቡን ከራብ አዳነ |

**2. መንፈሳዊ ሕይወትን ማደስ፡-** ዕዝራና ነህምያ በተመሳሳይ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩበት ወቅት ነበር (8፡2፤9)። ዕዝራ ሕዝቡን በመንፈሳዊ መታደስ አገልግሎት ነህምያን ረዳው (ነህ 8፡9)። የመንፈሳዊ ሕይወት መታደስ የጀመረው የእግዚአብሔርን ቃል ከማንበብ (ፈቃዱን ከማወቅ) (8፡3፤7-8) እና ለቃሉ ከመታዘዝ ጋር ነው። ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃሉ ሕዝቡ ስው ኃጢአታቸውን አስተዋሉ (9፡1-4)፣ ቃል ኪዳኑንም አደሱ (9፡37-38)። ቃል ኪዳን ማደሱ በሰንበት አለመሸጥና አለመግዛት፣ ልጆቻቸው ከአሕዛብ ጋር እንዳይጋቡ መከልከልና ለቤተ መቅደሱ እንዲጠነቀቁና አገልጋዮችን ቸል እንዳይሉ የሚል 3 ክፍል ነበረው። ነህምያ 12 ዓመት በኢየሩሳሌም ከቆየ በኋላ ወደ ሱሳ ተመለሰ። ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ (13፡6) 3ቱም የቃል ኪዳኑ ክፍሎች ተጥሰው አገኛቸው (13፡4-8)። የእስራኤል ጠላት የነበረው ጦቢያም በሊቀ ካህኑ ኤልያሴብ ትብብር መኖሪያውን በቤተ መቅደስ አንደኛው ክፍል ውስጥ አድርጎ ነበር፣ ሰንበት የንግድ ቀን ሆኗል (13፡15-22)፣ ሕዝቡም ከአሕዛብ ጋር ተጋብቷል (13፡23-31)። ይህም ሁሉ የእግዚአብሔር ሥራ የማያቋርጥ ጥበቃ (ክትትል) እንደሚያስፈልገው ያስገነዝባል።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ነህምያ።**
በታላቁ ጓዳ የነበረውን የጦብያን የቤቱን ዕቃ ሁሉ ነህምያ ከጓዳ ወደ ውጪ እንደጣለ (13:4-8)፤ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፤ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠ (ማቴ 21:12-13)።

**ዋና ትምህርት፡-**
**ጸሎትና ተግባር የተያያዙ ናቸው።** ነህምያ ውጤታማ መሪ የሆነው ጸሎትንና ተግባርን በአንድነት አጣምሮ በመያዙ ነበር። በጸሎት ያልተጀመረና በጸሎት ያልተደገፈ ተግባር የእግዚአብሔር ምክር የሌለበት ‹ሰው ሰራሽ› ተግባርን ያስገኛል። ግልጽ የሆነ የእግዚአብሔር ሀሳብ መረዳት (ተልእኮን ማወቅ) ለመንፈሳዊ መሪነት ቀዳሚ ሥራ ሲሆን በየደረጃውም በእግዚአብሔር መደገፍና ምሪትን መጠየቅ የሥራው ባለቤት ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን አስመዘንጋት ነው። በተጨማሪም በጸሎት የመትጋትን ያህል በተግባር ትጉህ ሠራተኛ ሆኖ መገኘት እግዚአብሔር አገልጋይ የሚጠበቅ ዓይነተኛ ባሕርይ መሆኑን ከነህምያ ኑሮ እናስተውላለን። ነህምያ በሥራ ይበረታል፤ በጸሎት ይተጋል (ለምሳሌ 1:4-11፤ 2:4፤ 1314፤22፤29፤31)። የተገኘው የሥራ ውጤትና ድል በራሉ ጾምና ጸሎት፤ በመሪነት ችሎታቸው ወይም በንጉሡ መልካም ፈቃድ እንደሆነ ሳያስብ ‹መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ› ነች በማለት ክብርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

**የፈረስ መኖሩን እያወቀ ዝም የማይል ሰው።** ከምርኮ የተመለሱት የ3ቱም መሪዎች የተልእኮ ትኩረት የፈረሰውን በማደስ ላይ ነበር።

- ✦ ዘሩባቤል- የቤተ መቅደሱ መታደስ፤
- ✦ ዕዝራ፡- የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት መታደስ፤
- ✦ ነህምያ፡- የኢየሩሳሌም ቅጥር መታደስ።

ፍርስራሽ በበዛበት ዘመን በቸልተኝነት የሚኖር የእግዚአብሔር ሰው የእምነቱን ባሕርይ በውል ያልተገነዘበ መሆን አለበት። ከመጽሐፈ ነህም የተወሰደው **‹እንነሣና እንሥራ›** (2:18) የሚለው ቃል በሀገራችንም ሆነ በሌሎች አገራት በዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በተለይም ሕንጻን (ቤትን) ለመገንባት የሚነገር የማነሳሻና የመበረታቻ ቃል ነው።



## ምዕራፍ 17፡-

# መጽሐፈ አስቴር

**ጸሐፊው፡-** አይታወቅም። ዕዝራ ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል።

**ጊዜው፡-** 465 ዓ.ዓ.። የአስቴር ታሪክ የተፈጸመው በመጀመሪያው የዘሩባቤል መመለስና በሁለተኛው በዕዝራ መመለስ መካከል በነበረው 483-473 ዓ.ዓ. ጊዜ ነው።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በመጽሐፈ ውስጥ በተጠቀሰችው በአስቴር ስም የተሰየመ ነው።

**ዋና ሰዎች፡-** አስቴር፤ አርጤክስስ፤ መርዶኪዮስ፤ ሐማ፤

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ፡-** ግብዣ 17 ጊዜ፤ ትእዛዝ 16 ጊዜ፤

**ዋና ሀሳብ፡-** እግዚአብሔር ሕዝቡን ከታላቅ እልቂት ስለ መታደጉ። መጽሐፉ አንዲት አይሁዳዊት ሴት ልጅ እንዴት የፋርስ ንግሥት እንደሆነችና በእርሷም በኩል እግዚአብሔር አይሁድን ከታሰበባቸው ታላቅ እልቂት እንዴት እንደታደጋቸው ይናገራል። በዚህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ስም በቀጥታ ባይጠቀስም እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ሕዝብ ታዳጊና የነገሥታት ንጉሥ መሆኑ በድርጊቱ ጎልቶ ይታያል።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ✦ ‹በዚህ ጊዜ ቸል ብትዪ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆንላቸዋል፥ አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ፤ ደግሞስ ወደ መንግሥት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደ ሆነ ማን ያውቃል?› (4:14)።

- ✦ ‹…ምንም እንኳ ያለ ሕግ ቢሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ፤ ብጠፋም እጠፋለሁ› (4:16)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** በሁለት በመክፈል እንደሚከተለው እናያለን።

1. አይሁድ በአደጋ ላይ (1-5)
2. አይሁድ ከጥፋት መዳን (6-10)

**1. አይሁድ በአደጋ ላይ፡-** አስቴር በሱሳ ትኖር የነበረች አይሁዳዊት ናት። ያሳደጋት አጎቷ መርዶክዮስ በንጉሡ ቤተ መንግሥት ይሠራ ነበር (2፡5-7)። የመጀመሪያ የዕብራይስጥ ስሟ ሀደሳ (2፡7) ሲሆን በኋላ አስቴር[48] ተባለች። ሐማ በፋርስ ግዛት በሚገኙ 127 አገሮች የነበሩትን አይሁድ በሙሉ ለማስገደል አሰበ፤ አዋጁም ተነገረ። መርዶክዮስ አስቴርን ስለ ሁለት ዋና ምክንያቶች ይመክራታል። 1. እግዚአብሔር እንዲህ ላለ ጊዜ ወደ ቤተ መንግሥት አምጥቷት እንደሆነ እንድታስብ፤ 2. እርሷ ይህን ሁኔታ በቸልታ ብታልፈው እግዚአብሔር ግን አይሁድን የሚታደግበት ሌላ መንገድ እንደሚኖረው (4፡13-14) ያስገነዝባታል።

**2. የአይሁድ ከጥፋት መዳን፡-** አስቴር ከጾመችና ከጸለየች በኋላ ወደ ንጉሡ ቀረበች፤ እግዚአብሔርም ሞገስ ሰጣት፤ በመጨረሻም በንጉሡ ትእዛዝ ሐማ ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው መስቀያ ላይ ተሰቀለ። አይሁድን ለማጥፋት የወጣው አዋጅ በሌላ አዋጅ ተሻረ። መርዶክዮስ ከነበረበት ዝቅተኛ ስፍራ ከንጉሡ ቀጥሎ ወደነበረው ከፍተኛ ስፍራ (ሹም) ከፍ አለ። የአይሁድን ከታላቅ ጥፋት መትረፍ የሚያስታውሰው ፑሪም የተሰኘው የአይሁድ በዓል የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነበር (9፡17-)። እግዚአብሔር ካደረገው የተነሣ ለአይሁድ ሞገስና መከበር ሆነ።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ አስቴር።**

የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ሕዝብ ለማጥፋት ያሰበው ሐማ ለሌላ ባዘጋጀው መስቀያ እንደ ተሰቀለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል እንዲሞት ያደረገውን የዲያብሎስን ሥልጣን ገፎ ድል ነሣው (ቆላ 2፡14-15፤ ዕብ 2፡14-15)።

**ዋና ትምህርት**

**የእግዚአብሔርን አሠራር ማንም አያውቅም።** እግዚአብሔር በየዘመናቱ ሀሳቡን የሚያከናውንበት መንገድ አስደናቂ ነው። መርዶክዮስ አስቴርን ‹እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል› (4፡14) እንዳላት የእግዚአብሔርን አሠራር ማንም አያውቅም። **በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚ የለም።** አይሁድ እንዲጠፉ በሚወሰንበት ዘመን አስቴር እንዲህ ወዳለ ስፍራ መምጣቷ፤ ሐማ ለመርዶክዮስ መስቀያ ግንድ አዘጋጅቶ ከንጉሡ

[48] በፋርስ ቋንቋ አስቴር ማለት ኮከብ እንደ ማለት ነው።



ፈቃድ በሚጠይቅበት በዚያች ሌሊት እንቅልፍ ከንጉሡ መሸሹ (6፡1)፤ ከታሪክ መጽሐፉ ውስጥ መርዶክዮስ ለንጉሡ ስላደረገው ውለታ የሚናገረው ክፍል በዚያች ሌሊት መነበቡ (6፡2-3)፤ ‹ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው ምን ይደረግለታል?› ለሚለው የንጉሥ ጥያቄ መልስ ይሰጥ ዘንድ በዚያን ሰዓት ሐማ በአዳራሹ ውስጥ መገኘቱ (6፡4-9) ሁሉ አጋጣሚ አይደለም፤ የእግዚአብሔር ድንቅ አሠራር እንጂ።

**ነገሩ ተገለበጠ፤ ትእዛዝ በፈጣን ፈረሶች ተላከ።** ሐማ ለመርዶክዮስ ያዘጋጀው መስቀያ ለራሱ ሆነ፤ አዋጅ በአዋጅ ተሻረ፤ ከንጉሡ ቀጥሎ ያለው የሐማ ሥልጣን ለመርዶክዮስ ተሰጠ፤ ደስታው ወደ ሀዘንና ራሱን ወደ መከናነብ (6፡12) ወረደ፤ የሐዘን ቀን ወደ ደስታ በዓል ተለወጠ፤ ‹ነገሩ ተገለበጠ› (9፡1)። እግዚአብሔር በአብርሃም ‹የሚባርኩህንም አባርካለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማለሁ› (ዘፍ 12፡3) በማለት የገባውን ተስፋ ፈጸመ። ጠላት ለጊዜው ያሸነፈና ድል ያገኘ ቢመስለውም እግዚአብሔር በተነሳበት ሰዓት ሁሉንም ይገለብጣል። ትእዛዙንም ‹በፈጣን ፈረሶች› (8፡10) ይልካል። ይህ የእግዚአብሔር ልዕልና ነው።

# ክፍል ሦስት
# የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት

በክፍል ሁለት የተመለከትናቸው የታሪክ መጻሕፍት እንደ መጠሪያቸው በአብዛኛው ታሪክን ይናገራሉ። ስለ ሕዝብና ስለ አገሮች በተለይም ስለ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያስረዳሉ። ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት የተሰኙት ደግሞ የሕይወት ልምምድን ይገልጻሉ። ተከታታይ የሆነ የታሪክ ቅደም ተከተል አይታይባቸውም። በአንድ ሰው ወይም በጥቂት ሰዎች ሕይወት ስለሆኑ ሁኔታዎች ይገልጻሉ።

የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት በአብዛኛው የሚያተኩሩት ስለ ሰው ልብ ነው። ሰው በልቡ የሚያስበውን፣ ከኑሮው ጋር የሚያደርገውን ትግልና የሚያልፈበትን ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው። ‹ከሰማይ በታች› ያለውን ኑሮ ያሳያሉ። ስለሆነም ዘመን የማይሽረው፣ በጊዜና በቦታ የማይወሰን መልእክት ይዘዋል።

መጻሕፍቱ የቅኔ የተሰኙበት ምክንያት የአቀራረባቸው ሁኔታ ግጥም መሰል ስለሆነ ነው። ይህ ማለት ግን ልብ ወለድ ናቸው ማለት አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሁሉ በሰው እጅ ቢጻፍም እግዚአብሔር እንዲጻፍ የፈለገው ብቻ ስለተጻፈ እነዚህም መጻሕፍት ከአጻጻፍ ዘይቤአቸው በስተቀር እንደ ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለባቸው መጻሕፍት ናቸው።

በአማርኛ ስነ ጽሑፍ የቅኔ ወይም የግጥም መጨረሻው የሚመታ ስንኝ ያለውና ሲነበብም ዜማዊ ተመሳሳይነት የሚሰጥ ነው። ብሉይ ኪዳን በተጻፈበት የዕብራይስጥ ቋንቋ የቅኔና የግጥም አጻጻፍ ፓራራሊዝም[49] (የስንኝ ድግግሞሽ)ና ሌሎችም የአጻጻፍ

[49] ፓራላሊዝም ማለት እቻ ዘይቤ ወይም እኩያ አባባል እንደማለት ነው። Parallelism refers "to the practice of balancing one thought or phrase by



ስልቶች አሉት። አንዳንድ ጊዜም የእግዚአብሔርን ማንነት ሲገልጽ እጅ፣ ዐይን፣ እንዳለው በሚመስል የሰውነት ክፍሎች የሚገልጽበት ጊዜ አለ። በስነ መለኮት ይህ አገላለጽ አንትሮፖሞርፊዝም[50] ይባላል።

የአምስቱ የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት ትኩረት የሚከተለው ነው።
- መጽሐፈ ኢዮብ፡- መልካም ሰዎች ስምን በመከራ ያልፋሉ?
- መዝሙረ ዳዊት፡- በጸሎት ውዳሴ ማቅረብ፣
- መጽሐፈ ምሳሌ፡- በሕግ ውስጥ ያለ ጥበብ፣
- መጽሐፈ መክብብ፡- በከንቱነት ውስጥ ያለ እውነት፣
- መኃልየ መኃልይ፡- በኅብረት/ጋብቻ ውስጥ ያለ ደስታ፣

a corresponding thought or phrase containing approximately the same number of words, or at least a correspondence in ideas.

[50] Anthropomorphism: The assigning of some part of the human anatomy to God's Person to convey some aspect of God's being like the eyes or ears (cf. Ps. 10:11, 14; 11:4; 18:15; 31:2).

# ምዕራፍ 18፡-
# መጽሐፈ ኢዮብ

**ጸሐፊው፡-** አይታወቅም።
**የተጻፈበት ጊዜ፡-** በ900 ዓ.ዓ. አካባቢ እንደተጻፈ ይገመታል። የኖረበት ዘመን በሚመለክት ኢዮብ ለቤተሰቡ የክህነት አገልግሎት መፈጸሙ (1፡5) የአሮን ክህነት ከመጀመሩ በፊት እንደኖረ ስለሚያመለክት፤ በመጽሐፉ የእስራኤል ስም አለመጠቀሱና ስለ ሙሴ ሕግ አለመነገሩ ወደ በ2000 ዓ.ዓ አካባቢ እንደሆነ ይገመታል።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በመጽሐፉ ውስጥ ዋና ሰው በሆነው በኢዮብ የተሰየመ። ስለ ኢዮብ በሕዝ 14፡14፤20፤ 1ቆሮ 3፡19 እና ያዕ 5፡11 እናነባለን።

**ዋና ሰዎች፡-** ኢዮብ፤ ኤልፋዝ፤ ብልዳዶስ፤ ሶፋር፤ ኤሊሁ።

**ዋና ሀሳብ፡-** የእግዚአብሔር መልካምነትና ልዕልና ነው። ጻድቅ ኢዮብ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ስቃይ ውስጥ ማለፉ ‹ለምን› የሚለን ጥያቄ ሊያስነሳ ቢችልም መልሱ እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ፤ በሁሉም ሁኔታ ላይ ባለሙሉ ሥልጣን የሆነና በልጆቹ (እርሱን በሚያምኑ) ላይ የሚመጣው መከራ ሁሉ በእርሱ የታወቀና ‹የተፈቀደ› መሆኑንና በትዕግሥት ለሚጠብቁ መጨረሻው መልካም እንደሚሆንላቸው ያሳያል።

**ቁልፍ ቃል/ሐረግ፡-** ‹ፍጹምና ቅን› 3 ጊዜ፤

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፤ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፤ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም፤ በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ፤ እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል። ሰይጣንም መልሶ እግዚአብሔርን። ቁርበት ስለ ቁርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል። ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሥጋውን ዳብስ፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል አለው። እግዚአብሔም ሰይጣንን። ሕይወቱን ተወው እንጂ እነሆ፤ እርሱ በእጅህ ነው አለው› (2፡3-6)።



- ‹ኢዮብም መለሰ እግዚአብሔርንም እንዲህ አለው። ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ። ...መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ› (42፡1-6)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን እንደሚከተለው በ3 በመክፈል ማየት ይቻላል።

1. የኢዮብ የመጀመሪያ ሁኔታ 1-2
2. የባልንጀሮቹ ምክር 3-37
3. የእግዚአብሔር ንግግር 38-42

1\. **የኢዮብ የመጀመሪያ ሁኔታ።** ኢዮብ ዖፅ በሚባል አገር (ከዛሬዋ እስራኤል በስተ ምሥራቅ አካባቢ) የሚኖር ሀብታም ሰው ነበር። ኢዮብ ‹ጻድቅ› ሰው እንደ ነበረ እግዚአብሔር ተናግሯል። እግዚአብሔርን የሚያመልከው ስላለው ንበረትና ጤንነት ነው በማለት ሰይጣን ኢዮብን ከሰሰው። ኢዮብን በተወሰነ ደረጃ እንዲፈትነው እግዚአብሔር ለሰይጣን ፈቀደለት። ሰይጣንም በኢዮብ ላይ በተከታታይ አለኝ በሚለውና በአካሉ (በስብዕናው) ላይ ሁሉ ታላቅ መከራ አመጣበት። የኢዮብ ሚስት አስተሳሰብ እግዚአብሔርን መከተልና ማምለክ የሚገባ ችግር እስካልደረሰብን ድረስ ነው የሚል ነበር። ኢዮብ በደረሰበት ሁኔታ ‹እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን› (1፡21) በማለት እግዚአብሔርን አልበደለም። ሆኖም ከመከራው ብርታት የተነሣ ‹ለምን ተወለድሁ›፤ ‹ለምንስ አልሞትም (3፡20-) እያለ ይጠይቅ ነበር። ኢዮብ እግዚአብሔርን አልካደም ግን ተጠራጠረው፤ መሞትንም ፈለገ (3፡11፤ 7፡19)፤ የእግዚአብሔርንም የጽድቅ ባሕርይ ጠየቀ (40፡8)።

2\. **የባልንጀሮቹ ምክር።** ሦስቱ ባልንጀሮቹ ኤልፋዝ፤ በልዳዶስና ሶፋር ከእርሱ ጋር አንድ ላምንት ከቆዩ በኋላ በሦስተ ዙር ኢዮብን ለመምከር ጀመሩ። ምክራቸውም የመጀመሪያው ከ3-14፤ ሁለተኛው ከ15-21፤ ሦስተኛው ከ22-31 ይገኛል። ሦስቱም ባልንጀሮቹ ለኢዮብ የሰጡት ምክር በአጠቃላይ ሲታይ መከራ ሁሉ የሚመጣው በኃጢአት ምክንያት ነው የሚል ነበር። የሦስቱ ምክር የእውነትና የስህተት ድብልቅ አለበት። ለምሳሌ ኤልፋዝ ጻድቁን አይጥልም ማለቱ ልክ ነው (8፡20)። በ5፡11-13

የተናገረውም በ1ቆሮ 3፡19 ተጠቅሶአል። ሆኖም ኢዮብ መከራ የተቀበለው በኃጢአቱ ምክንያት ነው ማለታቸው በ2፡3 ስለ ኢዮብ ከተነገረው ጋር ይቃረናል። ኢዮብም እነዚህን ‹የምታስጨንቁ አጽናኞች (16፡2) አላቸው። ሦስቱን ባልጀሮች እግዚአብሔር ገለጻቸው (42፡7)። በመጨረሻ የተናገረው ከሁሉም ታናሽ የሚሆን የኤሊሁ ምክር (32-37) ከሦስቱ የተሻለ ነበር። እግዚአብሔር ሰውን በመከራ ውስጥ ያስተምረዋል፤ እግዚአብሔር መልካም ነው (33፡24)፤ እግዚአብሔር አይሳሳትም (34፡12)፤ እግዚአብሔር ታላቅ ነው (36፡26) የሚል ነበር።

3. **የእግዚአብሔር ንግግር።** እግዚአብሔር ለኢዮብ ሲመልስለት ሲጀምር ሁሉን አዋቂነቱን በተፈጥሮ ምሳሌነት ይነግረዋል። እንዲሁም የእርሱን ታላቅነትና የሰውን ትንሽነት ያሳየዋል። ኢዮብ ለምን በመከራ ውስጥ እያለፈ እንደሆነ አላብራረለትም፤ ከእርሱ ጋር መከራከሩንም አልወደደለትም (40፡2)። እግዚአብሔር በኃይሉ ታላቅ፤ በመፍጠር ሥራ ጥበበኛ እንደሆነ (40) ሲገልጽለት ኢዮብ መልስ ያጣል። መከራውም የእግዚአብሔርን ታላቅነት የበለጠ እንዲያውቅ ምክንያት ሆነው። እጅግ ብዙ የማያውቀው ነገር እንዳለ ኢዮብ ተገነዘበ።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር፤ ወይም እግዚአብሔርን ‹ለምን› ብሎ መጠየቅ እንደማይገባው አስተዋለ። እግዚአብሔርንም ‹እነሆ፤ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ፤ የምመልስልህ ምንድር ነው? እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ (40፡3-4) አለ። ሦስቱ ባልንጀሮች ኢዮብን መልካም ምክር ባለመምከራቸው እግዚአብሔር ገለጻቸው፤ ኢዮብም እንዲጸልይላቸው አደረገ። በመጨረሻም ኢዮብን በብዙ በረከትና በረጅም ዕድሜ ባረከው።

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ኢዮብ፡-**
ኢዮብ በመከራ ውስጥ ቢያልፍም የሚዋጀው (የሚታደገው) እንደሚመጣ ‹እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፥ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፤ ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፤ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ። እኔ ራሴ አየዋለሁ፥ ዓይኖቼም ይመለከቱታል፤ ከእኔም ሌላ አይደለም። ልቤ በመናፈቅ ዝሎአል (19፡25-27) በማለት ተናገረ። ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ተረድቷል። ሕይወት ክርስቶስ ነው (ዮሐ 11፡25)። ከትንሣኤ በኩር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1ቆሮ 15፡20)።



**ዋና ትምህርት፡-**
**የእግዚአብሔር ልዕልና ታማኝነቱና ክፉን ወደ መልካም መቀየሩ።** ሰይጣን አቅሙ የተገደበ በመሆኑ በቅዱሳን ላይ ለሚያመጣው መከራ አስቀድሞ እግዚአብሔርን እንደሚያስፈቅድ ከሉቃ 22፡31-32 እንገነዘባለን። ከገደቡም ማለፍ አይችልም። እግዚአብሔርም ደግሞ ነገሮችን ከዘላለም አንጻር ይመለከታል። ስለዚህ በሰው ላይ የሚመጣው መከራ (ሕመም) በሰይጣንም ሥራ ሲሆን ስለሚችል ለሁሉ ሳይንሳዊ ምክንያት መስጠት አይቻልም ማለት ነው። እግዚአብሔር ከወደደ በሰው ሕይወት ላይ የሚሆኑ ነገሮች ለምን እንደሚሆኑ ሲገልጽልን ይችላል። ባይገልጽልንም ልዑል እግዚአብሔርን ‹ለምን› ብለን ልንጠይቀው አንችልም። እግዚአብሔር ታላቅነቱን ለኢዮብ ሲያሳውቀው ሲጀምር የጠየቀው ‹ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ?› (38፡4) በማለት ነው። ኢዮብ ለዚህ ምንም መልስ አልነበረውም። እግዚአብሔር ለሰይጣን ሲፈቅድም ለአርሉ ክብር የሚያመጣለትን መንገድ ስለሚያውቅ ነው። መጽሐፍ ‹ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፤ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና› (ያዕ 5፡11) እንደሚል ልዑል እግዚአብሔር ለኢዮብ በመጨረሻው በብዙ እጥፍ መልካም አደረገለት። በደረሰብህ መከራ የእግዚአብሔርን መልካምነት ሳታይ ለመሞት አትመኝ (6፡9)።

**ጽኑ እምነት እግዚአብሔር ሁልጊዜም መልካም መሆኑን መገንዘብ ነው።** እግዚአብሔርን በመፍራት በሚኖር ሰው ላይ እግዚአብሔር ሳያውቀውና ሳይፈቅደው የሚመጣ ነገር የለም። ሲፈቅድም በገደብ ስለሚሆንና ሁሉም በቁጥጥሩ ሥር ስለሆነ ልጆቹ ፍጹም እንዲታመኑበት ይፈልጋል። እግዚአብሔር ስለሚያደርግልን ነገር ሳይሆን ስለ እርሱነቱ ልንታመንበት ይገባል። ሰው ለሚደረስበት ነገር ሁሉ ወዲያውኑ ማብራሪያ ላያገኝ ይችላል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አይገልጽምና በእምነት ካልሆነ በቀር ሕይወት ከሰው መረዳት በላይ የሆነ እንቆቅልሽ ይኖረዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር በሚያደርግልን ነገር ብቻ የምንለካው ከሆነ ባልተደረገልን ጊዜ እንደ ኢዮብ ሚስት ‹ስደብና ሙት› የሚሉን በዙሪያችን ቅርብ ነው። እምነት የሚታወቀው በፈተና ውስጥ ሲታለፍ ነው (ሮሜ 16፡10)።

ሰይጣን ዛሬም በመክሰሱ ቀጥሏል፤ አስተዋይ ሰው ከወጥመዱ ያመልጣል። ከአዳም ዘመን ጀምሮ ሰይጣን አሳችና ዛሬም የወንደሞች ከሳሽ ነው (ዘፍ 3:1-7፤ ራእ 12:9)። በመንፈሳዊው ዓለም ሁልጊዜ ያለ እረፍት ቀንና ሌሊት ይሠራል። በምድር ዙሪያ ይዞራል። እነማን በእግዚአብሔር አጥር ውስጥ እንደሚኖሩም ያውቃል (1:10)። በዚህ ሥራው እስከ መጨረሻው ዘመን ይቀጥልበታል (ራእ 12:10፤ 1ጴጥ 5:8)። አምላካችን ግን ‹እግዚአብሔር ይገሥጽህ› እያለውና ነጭ ልብስም እያለበሰን (ዘካ 3:2) ያኖረናል። እኛም ‹ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወቱ ይሰጣል። ...ይሰድብሃል› (ኢዮ 2:4-5) በሚለው የሰይጣን ማጥመጃ ስልት እንዳንገባና ዋናውን ነገር ረስተን እግዚአብሔርን የምንከተለው በሥጋ ስለሚገኝ ‹በረከት› ብቻ እንዳይሆን በእጅጉ ማተዋል ይገባናል።

**ለሁሉም ‹ሕመም› መድኃኒቱ አንድ አይሆንም።** የኢዮብ ሦስቱ ባልንጀሮች ወደ እርሱ መምጣታቸውና ለማጽናናት ለባት ቀን አብረውት መቆየታቸው ጥሩ ነገር ሆኖ ሳለ ምክራቸው ግን ለኢዮብ መከራ መነሻውን ከሚያውቀው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘ አልነበረም። ኢዮብን ‹በመከራ ውስጥ የምታልፈው ከኃጢአትህ የተነሣ ነው› የሚለው አስተሳሳብ በከፊል እውነት ላይ የተመሠረተ ነው። በእርግጥ ሰው የዘራውን ያጭዳል (ገላ 6:7፤ መዝ 37:25)፤ ሆኖም የኢዮብ መከራ ግን የኃጢአት ፍሬ አልነበረም። በቅዱሳን ላይ የሚመጣ መከራ ሁልጊዜ በኃጢአት ምክንያት የመጣ ቅጣት ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔርን የሚፈሩም እንደ ኢዮብ በመከራ ውስጥ ሊያልፉ ይችላሉ። ለዚህም ኢዮብ ‹እኔ ደግሞ አንደ እናንተ እናገር ዘንድ ይቻለኝ ነበር፤ ነፍሳችሁ በነፍሴ ፋንታ ቢሆን ኖሮ፥ እኔ በእናንተ ላይ ቃል ማሳከት፤ ራሴንም በእናንተ ላይ መነቅነቅ በተቻለኝ ነበር› (16:4) አላቸው።

ሰውን ለመምከርና ለማጽናናት የሚያስብ ሰው ‹የችግርህን መነሻ እኔ አውቃለሁ› ብሎ ከመጀመሩ በፊት ለሰው ችግር ሁሉ በቂ መልስ እንደሌለው በመገንዘብ እግዚአብሔር ስለዚያ በችግር ላይ ስላለ ሰው የሚናገረውን በጸሎት ማድመጥ ይጠቅማል። ያለዚያ ከመናገር ይልቅ ዝምታ የበለጠ ያጽናናል (13:5)። አኛ ‹ምክር አዳዮች› አይደለንም። ድንቅ መካር ክርስቶስ ብቻ ነው (ኢሳ 9:6)። ሌላውን ሰው ስንወቅስ ‹እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው› (ሐዋ 10:15) እንደተባለው ዓይነት እንዳይሆንብን መጠንቀቅ ይገባናል።



# ምዕራፍ 19:- መዝሙረ ዳዊት

**ጸሐፊው:-** ዳዊትና ሌሎች ናቸው። የ100 መዝሙሮች ጸሐፊ በየመዝሙሩ መጀመሪያ ላይ ተመልክቶአል። ዳዊት 73፤ አሳፍ 12፤ ቆሬያውያን 11፤ ሰሎሞን 2፤ ሙሴ 1፤ ኢታን 1 መዝሙሮች ሲጽፉ የተቀሩት 50 መዝሙሮች በማን እንደተጻፉ አልተገለጸም። ሆኖም ለምሳሌ በሐዋ 4:25 እና ዕብ 4:7 መሠረት መዝ 2 እና 95 በዳዊት እንደተጻፉ ስለተገለጸ ቀሪዎቹም በዳዊት የተጻፉ ሊሆኑ ይቻላሉ።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** ከ1400-500 ዓ.ዓ.። መዝሙሮቹ በተለያዩ ጸሐፊዎች የተጻፉ ስለሆኑ ጊዜው ይለያያል። ከሁሉም የሚቀድመው በሙሴ የተጻፈው መዝ 90 በ1400 ዓ.ዓ. እንደሚሆን ሲገመት የዳዊት መዝሙሮች ደግሞ ከ1020-975 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ እንደሆነ ይታሰባል። እንዲሁም ከምርኮ ስለመመለስ የሚናገሩት መዝ 126ና 137 ከ500 ዓ.ዓ. በፊት እንደተጻፉ ይገመታል።

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** መጽሐፉ ‹በእስራኤል ዘንድ መልካም ባለቅኔ በሆነው በእሴይ ልጅ ዳዊት› (2ሳሙ 23:1) የተለየመ ነው። በዕብራይስጥ ተሂሊም[51] ወይም ውዳሴ ይባላል። የመዝሙረ ዳዊት አጻጻፍ ‹ፓራራሊዝም›[52] የተሰኘ የአጻጻፍ ስልት ይጠቀማል። ፓራላሊዝም ማለት አቻ ዘይቤ ወይም እኩያ አባባል እንደ ማለት ነው።

**ዋና ሰዎች:-** ዳዊት፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ።

---

[51] *Sepher Tehillim* (book of praises). Gk: *Psalmoi.* - "songs to the accompaniment of a stringed instrument,"

[52] መዝሙረ ዳዊት የተለያዩ የፓራራሊዝም (ድግግሞሽ ወይም ንጽጽር) የአጻጻፍ ስልቶችን ይጠቀማል። እነዚህ Parallelism ዓይነቶቸች Synonymous/repeat (ተመሳሳይ), antithetical/contrast (ተቃራኒ) synthetical/ progressive (ተደጋጋፊ/የሚያድግ ሀሳብ) ይባላሉ።

**ዋና ሀሳብ፡-** ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን ማመስገንና ማወደስ ነው። መዝሙረ ዳዊት ብዙ ጸሎቶችን በመዝሙር ስለሚገልጽ የመዝሙር-ጸሎት ሊባልም ይችላል። የእግዚአብሔር ስም በሁሉም መዝሙሮችና በአጠቃላይ 1200 ጊዜ ተጠቅሶአል። ይህም በሀዘንም ጊዜ ቢሆን (መዝ 74) ወይም በሃሌ ሉያ (መዝ 150) የዝማሬ ትኩረቱ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል። እግዚአብሔር ካልተመሰገነ መንፈሳዊ መዝሙር የለምና። መዝሙረ ዳዊት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰፊው መጽሐፍ ሲሆን ረጅሙ ምዕራፍ ምዕ 119 ነው። ሰው ላለበት የተለያየ ሁኔታ ሁሉ ለውስጥ ልቡ የሚናገር መጽሐፍ ስለሆነ ሰዎች በብዛት የሚያነቡት መጽሐፍ ነው። መዝሙረ ዳዊት በአዲስ ኪዳን 81 ጊዜ ተጠቅሶአል።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ውዳሴ (ምስጋና) 166 ጊዜ፤ በረከት፤ ይባረክ፤ ባርኩ 100 ጊዜ ያህል፤ ጽድቅ (ጻድቅ) 130 ጊዜ።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፤ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፤ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል› (1:1-2)።
- ‹አቤቱ ጌታችን፤ ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመስገነ› (8:9)።
- ‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፤ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፤ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፤ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ (23:1-6)።
- ‹አሕዛብ ሁላችሁ፤ እግዚአብሔርን አመስግኑት፤ ወገኖችም ሁሉ ያመስግኑት፤ ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና፤ የእግዚአብሔርም እውነት ለዘላለም ትኖራለች› (117:1-2)።



- ‹ጕልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው። በፍጹም ልቤ ፈለግሁህ፤ ከትእዛዝህ አታርቀኝ። አንተ እንዳልበድል፤ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ› (119:9-11)።
- ‹እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። ሃሌ ሉያ (150:6)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** ብዙዎች 150 መዝሙሮች የያዘውን መጽሐፍ በ5 የመጽሐፍ ክፍሎች ይከፍሉታል። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ክፍል የሚጨርሰው በምስጋናና ውዳሴ ነው። መጽሐፉን ከፔንታቱክ መጻሕፍት ጋርም በማዛመድ የሚከፍሉት አሉ።

1. መጽሐፍ 1፡ ስለ ሰውና ተፈጥሮ (1-41) - ዘፍጥረት
2. መጽሐፍ 2፡ ስለ እስራኤልና ነጻ ስለ መውጣት (42-72) - ዘጸዓት
3. መጽሐፍ 3፡ ስለ አምልኮና ቤተ መቅደስ (73-89) - ዘሌዋውያን
4. መጽሐፍ 4፡ በምድር ላይ ጉዞ (90-106) - ዘኍልቁ
5. መጽሐፍ 5፡ የእግዚአብሔር ቃልና ውዳሴ (107-150) - ዘዳግም

እንዲሁም በመዝሙሮቹ ይዘት ለምሳሌ ያህል በሚከተለው መንገድ ይሰባሰባሉ።

- **መሲሐዊ መዝሙሮች-** 2፤ 8፤ 16፤ 22፤ 31፤ 34፤ 35፤ 40፤ 41፤ 45፤ 68፤ 69፤ 72፤ 102፤ 110፤ 118። ስለ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶችን ይዘዋል።
- **ስለ ፍጥረትና ተፈጥሮ መዝሙሮች፡-** 8፤ 19፤ 104
- **የእስራኤል ከባርነት ነጻ ስለ መውጣት መዝሙሮች፡-** 78፤
- **የሃሌሉያ ውዳሴ መዝሙሮች፤** 8፤ 97፤ 100፤ 106፤ 113፤ 115፤ 117፤ 135፤ 136፤ 146፤ 150
- **የጸሎት፡-** 3፤ 55፤ 79፤ 80፤ 86፤ 123
- **የንስሐ፡-** 32፤ 51፤ 103
- **ስለ ፍትህ-** 2፤ 7፤ 14፤ 26፤ 37፤ 49፤ 58፤ 82፤ 94፤ 145
- **ስለ ጥበቃ-** 3፤ 4፤ 7፤ 16፤ 17፤ 18፤ 23፤ 27፤ 31፤ 91፤ 121፤ 125
- **ስለ ብቸኝነት፤-** 9፤ 10፤ 12፤ 13፤ 27፤ 40፤ 43
- **ስለ ምሪት፡-** 1፤ 5፤ 15፤ 19፤ 25፤ 32፤ 48

**ክርስቶስ በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ:-**
መዝሙረ ዳዊት ስለ ክርስቶስ የተነገሩ በርካታ ትንቢቶችና ምሳሌዎችን ይዟል። ሠንጠረዥ 23 ስለ ክርስቶስ የተነገሩና በአዲስ ኪዳን የተፈጸሙ ትንቢቶችን ያሳያል።

ሠንጠረዥ 23
ስለ ክርስቶስ በመዝሙር የተነገሩና በአዲስ ኪዳን የተፈጸሙ ትንቢቶች

| ስለ ክርስቶስ የተነገረው | መዝሙር | አዲስ ኪዳን |
|---|---|---|
| 1. መወለዱ | 104:4 | ዕብ 1:7 |
| 2. ዳዊት ልጅ መሆኑ | 89:3-4፤ 35-36 | ማቴ 20:30፤ 22:41 |
| 3. የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ | 2:7 | ዕብ 1:5፤6 |
| 4. መከራ መቀበሉ | 8:4 | ዕብ 2:6፤ 1ቆሮ 15:27 |
| 5. መለኮትነቱ | 45:6 | ዕብ 1:8 |
| 6. አገልግሎቱ | 69:9 | ዮሐ 2:17 |
| 7.የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ መጣ | 40:6-8 | ዕብ 10:5-7 |
| 8. መጠላቱ/ መገፋቱ | 118:22 | ማቴ 21:42 |
| 9. አልፎ መሰጠቱ | 41:9 | ዮሐ 13:18 |
| 10. መሰቀሉ | 22 | ማቴ 27:39፤43፤46፤ ሉቃ 23:35፤ ዮሐ 19፤ ዕብ 2:12 |
| 11. አጥንቱ አይሰበርም | 34:20 | ዮሐ 19:36-37 |
| 12. ትንሣኤው | 16:8-10 | ሉቃ 24:5-7፤ ሐዋ 2: 25-32 |
| 13. ዕርገቱ | 68:18 | ኤፌ 4:8 |
| 14. መግዛቱ | 102:26 | ዕብ 1:11 |
| 15.አሳልፎ መስጠት | 41:9 | ሉቃ 22:48፤ ዮሐ 13:18 |
| 16. ለመፍረድ ይመለሳል | 96:13 | 1ተሰ 1:10 |
| 17. የዘላለም ካህን-ንጉሥ ነው | 110:4 | ዕብ 6:20፤ 5:6 |

**ዋና ትምህርት:-**
**የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ የሚጠቀመው ጠባቂው ነው።** ፍጹም፤ የታመነ፤ ቅን፤ ብሩህ (19:7-8) የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ለነፍስ መመለስ፤ ለጥበብ፤ ለልብ ደስታ፤ ለዓይን ብርሃን ፍቱን መድኃኒት ነው። እጅግ ክቡርና ጣፋጭም ነው። ይህን ተረድቶ የሚጠብቀው (የሚኖርበት) ጥቅሙን የተረዳ ሰው ነው።



**የእግዚአብሔር እረኝነት ሙሉ ነው።** የእረፍት፤ የመመለስና የምሪት ፍላጎታችንን የሚሞላ፤ ሞትን ሳይቀር የሚያስፈራንን ዝም የሚያስኘልን፤ በዕድሜ ዘመናችን ሁሉ በበጎ ነገር የሚያጠግበን መልካም እረኛ እግዚአብሔር ነው (መዝ 23)። ለእርሱ ሃሌሉያ ይሁን።

**ሃሌሉያ- ምስጋና ለሚገባው ጌታ።** ዳዊት የመዘምራንን አገልግሎት በእግዚአብሔር ቤት አስጀመረ (1ዜና 6:31፤ 15:16)። ዳዊት ራሱ በእግዚአብሔር ፊት ይዘምራል (2ሳሙ 6:14)። በተቸገረም ጊዜ የውስጥ ስሜቱን በዝማሬ ለእግዚአብሔር ይገልጻል። ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ ከጠላቶቼም እድናለሁ› (መዝ 18:3)። መላእክትም በበጉ ፊት ወድቀው ‹ለተገባው› ...እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ (ራእ 5:8-11)። እኛም ለዚህ ጌታ ዘወትር ምስጋና ልናቀርብለት ይገባናል።

# ምዕራፍ 20:-
# መጽሐፈ ምሳሌ

**ጸሐፊው:-** የንጉሥ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነው (1:1፤ 10:1፤ 25:1)። እንዲሁም አጉር (30)ንና ልሙኤል (31)ን ሁለቱን ምሳሌዎች ጽፈዋል። ሰሎሞን ‹ሦስት ሺህ ምሳሌዎች ተናገረ፤ መኃልዩም ሺህ አምስት ነበረ› (1ነገ 4:32)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 950-700 ዓ.ዓ.። የንጉሡ ሕዝቅያስ ሰዎች ስላሰባሰቧቸው ምሳሌዎች በ25:1 ስለሚናገር መጽሐፉ በ950 ዓ.ዓ አካባቢ በሰሎሞን ተጽፎ 700 ዓ.ዓ አካባቢ ባለው ጊዜ እንደተጠናቀረ ይታሰባል።

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** ምሳሌ የሚለው ከመጽሐፉ ይዘት የተወሰደ ነው (1:1)። ‹ምሳሌ› በዕብራይስጥ ማሻል[53] ማለትም መሳይ፤ አምሳያ፤ መምሰል፤ የሚል ሀሳብ ኖሮት በምሳሌ የተነገረ የጥበብ ንግግር ነው። (‹ቅጥር እንደሌላት እንደ ፈረሰች ከተማ፤ መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው› (25:28) ሲል ራሱን የማይቆጣጠር ሰው ቅጥሯ በፈረሰ ከተማ ተመስሏል ለማለት ነው)።

**ዋና ሰዎች:-** ሰሎሞን፤

**ዋና ሀሳብ:-** ከጥበብ ሁሉ በላጩ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። ሰዎች በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት መኖዝ እንደሚገባቸው ተግባራዊ ምክር ይሰጣል። መጽሐፉ ስለ ኃጢአት፤ ፍቅር፤ ገንዘብ፤ ፍርድ፤ ልጆች፤ ሀብት፤ ድህነት፤ ትዕቢት፤ ምላስ፤ ቅጣት፤ ስንፍና፤ ጓደኛ፤ ሞት፤ ወዘተ በሚሉ በርካታ የሕይወት ርዕሶች ሰው እንዴት በጥበብ መኖር እንዳለበት ጠቃሚ ምክርና ትምህርት ይሰጣል። በኑሮ ውጥረት ውስጥ

[53] Hb: mashal, comes from a root meaning "to be like." or "to represent." fromma - "to be like, represent"- means "parallel," "similar," or "a comparison." . mashal. comes from a root meaning "to be like," or "to represent." ምሳሌ- ለማነዛቤ በሚያመች አነጋገር ማለት ነው።



ለሚኖር ሰው ኑሮን ለማሸነፍና በስልት ለመኖር የጥበብ ማኅደር ነው። መጽሐፉ በአዲስ ኪዳን 60 ያህል ጊዜ ተጠቅሶአል።

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ:-** ጥበብ ወይም ጥበበኛ 85 ጊዜ ሲገኝ 70 ጊዜ ከተጻፈው ጻድቅ ወይም ጽድቅ ከሚለው ጋር የተያያዘ ነው። በአንጻሩ ጥፋት የሚለው 85 ጊዜ ሲገኝ ከእርሱ ጋር የተገናኘው ሰነፍ ወይም ስንፍና 71 ጊዜ ይገኛል።

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች:-**

- ‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው (1:7)።
- ‹በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፤ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል። በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን፤ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፋትም ራቅ (3:5-7)።
- ‹የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል› (18:10)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** መጽሐፉን እንደሚከተሰው በ4 ክፍሉ ማየት ይቻላል።

1. የጥበብ ምንነትና ክቡርነት - በአባትን ልጅ መካከል የተደረገ ንግግር (1-9)
2. የሰሎሞን ምሳሌዎች (10-24)
3. በሕዝቅያስ ሰዎች የተቀዱ የሰሎሞን ምሳሌዎች (25-29)
4. የአጉርና ልሙኤል ምሳሌዎች (30-31)

የመጽሐፉን መልእክት ባጭሩ ለመረዳት ጥቂት ርዕሶች እንደሚከተሰው ቀርበዋል።

**ጥበበኛ** ሰው። በእግዚአብሔር የሚታመን እንጂ በራሱ ማስተዋል የማይደገፍ፤ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው (3:5-6፤ 11:14፤ 15፤22፤ 16:9)። ጥበበኛ ሰው መለኮታዊ ምሪትን ይጠይቃል። እግዚአብሔር ምሪትን እርሱን በሚፈሩ ባልጆሮች በኩልም ይሰጣል። ጥበበኛ ሰው ትሑት የሆነ (15:25፤ 16:18-19፤ 21:4)፤ ከኃጢአት የራቀ (6:16)፤ በሚዛን ታማኝ የሆነ (11:1፤ 16:11)፤ በሥራው ትጉህ የሆነ ነው (20:13፤ 24:33-34)።

**የሀገር አመራር ጥበብ፡፡** እግዚአብሔር በሀገር መሪዎች ላይ ልዑል ነው (8፡15-16፤ 21፡1-2)፡፡ ስለዚህ በፍትህ ማስተዳደር ይገባቸዋል (31፡1-9)፡፡ እግዚአብሔር ጽድቅን እንደሚወድና ኃጢአትን እንደሚቀጣ ሁሉም ሰው ሊያውቅ ያስፈልጋል (11፡11፤ 14፡34)፡፡ ጥሩ አመራር ባለበት ሰላም አለ (11፡14)፤ ሕዝብን ሁሉ የሚጠቅም ነገር ይሠራል (24፡3)፤ ለሕዝቡም ደስታ ይሆናል (29፡2)፡፡

**የቤተሰብ አስተዳደር ጥበብ፡፡** ልባም ሚስት ከእግዚአብሔር የምትሰጥ በረከት ናት (18፡22፤ 19፡14)፡፡ ወላጆች ለልጆቻቸው መልካሙን መንገድ ማሳየት አለባቸው (22፡6)፤ በሥርዓትም ማሳደግ ይገባቸዋል (13፡24፤ 22፡15፤ 23፡13)፡፡ ‹ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው ባደገ ጊዜ ከእርሷ ፈቀቅ አይልም› (22፡6)፡፡ ልጆችም ወላጆቻቸውን ሊያከብሩና ሊሰሙአቸው ይገባል (1፡18-19)፡፡

**ልባም ሴት፡፡** መልካም ሚስት ናት (31፡11-12፤ 23-24)፤ ቤቷን ትሠራለች (14፡1) ለልጆቿ መልካም እናት ናት (31፡14-15፤ 18፤ 21፤27)፡፡ ለሌላው ሰው ግድ ይላታል (31፡11-12፤ 23-24)፤ በንግግሯ ጥበበኛ ነች (31፡26)፤ ባሏ እንዲከናወንለት ትረዳዋለች (31፡23)፡፡ ይህ ሁሉ መልካምነት እግዚአብሔርን ከመፍራቷ የሚገኝ ነው (30)፡፡ ተላላ ሴት ግን ተጨቃጫቂ ነች፤ እረፍት አትሰጥም (21፡19፤ 25፡24፤ 27፡15-16)፡፡

**ከጓደኛ ጋር የመኖር ጥበብ፡፡** የወዳጆችን ቁጥር መመጠን ከቅርቦችም ጋር መጠጋጋት መልካም ነው (18፡24)፡፡ መልካም ወዳጅ ራስን ለማስተካከል ይጠቅማል (27፡14)፤ እውነተኛ ወዳጅ ቢያቆስልም ለመርዳት ነው (27፡6)፡፡ ወደ ክፋት ከሚመሩ ወዳጆች ራቅ (1፡10-19)፡፡ የሀብት ብዛትን በማየት የሚመጣ ወዳጅነት ጎጂ ነው (19፡4)፡፡ ወዳጅነትም ቢሆን ልክ አለው (16፡28፤ 17፡9)፡፡

**የገንዘብ አያያዝ ጥበብ፡፡** ገንዘብን ለጽድቅ አውለው፤ በከንቱ አታባክን (10፡16)፤ ለጋስ ሁን (11፡24፤25፤ 22፡9) ከራስህ ጥቅም ይልቅ የሌሎችን አስቀድም (11፡26)፤ ብልጣ ብልጥ አትሁን (17፡18፤ 22፡26-27)፤ ጉቦ አትቀበል (17፡23)፤ ችግረኞችን እርዳ (19፡17፤ 21፡13፤ 22፡9)፤ ለወደፊቱ ብለህም ቆጥብ (21፡20)፤ ለመበደር አትቻኮል (22፡7)፡፡



**የምላስ (አንደበት) ዓይነቶች፡፡** አራት ዓይነት አንደበቶች አሉ፡፡

1. አንደበታቸውን የሚገቱ፤- ከመናገራቸው በፊት የሚያስቡ፤ ራሳቸውን የሚገዙ (10፡19፤ 11፡12-13፡ 12፡16፡13፡3) ጥበበኞች ናቸው፡፡
2. ተገቢውን ቃል የሚናገሩ፤- ቃላቸው ደስ የሚያሰኝ፤ ለፈውስ የሚሆን (10፡32፤ 12፡18፤25፤ 15፡23፤26) ጥበበኞች ናቸው፡፡
3. ጠማማ ንግግር የሚናገሩ፡- ነውረኛና ሐሜተኛ አንደበት ያላቸው ናቸው (6፡12-14፤ 8፡13፤ 16፡28፤ 18፡8 25፡18)፡፡ ይህ የጥበብ መጉደል ነው፡፡
4. ሐሰተኛ አንደበት ያላቸው፡- ተሳዳቢ ምላስ ያላቸው፤ በግደየለሽነት የሚናገሩ (10፡18፤32፤ 11፡9፡12፡16፤18፤ 15፡4)፡፡ እነዚህ ሰነፎች ናቸው፡፡ ከመናገር ይልቅ ማድመጥን ወደድ (15፡1-2፤ 20፡19፤ 26፡20) ጥበብ ነው፡፡

**ክርስቶስ በመጽሐፈ ምሳሌ፡፡**
‹ወደ ሰማይ የወጣ የወረደስ ማን ነው? ነፋስንስ በእጁ የጨበጠ ማን ነው? ውኃንስ በልብሱ የቋጠረ ማን ነው? የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማን ነው? ይህን ታውቅ እንደ ሆንህ፤ ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?› (ምሳ 30፡4)፡፡ ይህ የመሰከት መግለጫ ነው፡፡ ስሙ እግዚአብሔር የልጁ ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እንዲሁም ምዕ 8 ጥበብ ‹እኔነት› ባለው ሰው ምሳሌ ተገልጻለች፡፡ መለኮታዊ ነች (22-31)፤ ሕይወትን የምትሰጥ ናት (35-36)፤ ጻድቅ (8-9)፤ ለሚፈልጓት የምትገኝ (1-6፤ 32-35)፡፡ ይህ ጥበብ ሁሉ በእርሱ ስላለው (ቆላ 2፡3)፤ በሥጋ ስለተገለጠው ክርስቶስ ያመለክታል፡፡ እርሱ ጥበባችን ነው (1ቆሮ 1፡24፤30)፡፡

**ዋና ትምህርት፡-**
**ጥበብ በጽድቅ በመኖር ይገኛል፡፡** ጽድቅ እግዚአብሔርን በመፍራት መኖር ነው፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት ለእርሱ የሚገባውን አክብሮት መስጠት ነው (10፡27፤ 14፡26-27፤ 15፡16፤ 16፡6፤ 19፡23፡ 28፡14)፤ ከክፉ መራቅ ነው (8፡13፤ 16፡6)፡፡ ይህን የዕድሜ ክልል አይወስነውም፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው (1፡7፤ 2፡5፤ 9፡10፤ 15፡33)፤

ወደ ሕይወት ይመራል (14:27)፤ የጸሎት መልስ ያስገኛል (1:29)፤ ዕድሜን ያረዝማል (10:27)፤ ተስፋን ያድሳል (23:17-1815:16) ከሀብት ይልቅ ይሻላል (22:4)።
የጥበብን ምንነት ለመገንዘብ የሚከተለው ቀመር ሊያግዝ ይችላል።

ጥበብ = እውቀት+ ስልት

ለማያዊ ጥበብ = እውቀት+ ስልት+ ጽድቅ

እውቀትን በተገቢው ሁኔታ ማዋል ስልት ነው እንበል። እውቀትና ስልት በአንድ ላይ ጥበብ ይሆናሉ። ይህ ጥበብ እግዚአብሔርን በመፍራት (ማለትም በጽድቅ) ሲሆን ለማያዊ ጥበብ ነው። እውነተኛ ጥበብ እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ይመራል (2:1-5)። እግዚአብሔር የጥበብ ለጋስ ስለሆነ ለሚለምነው ይሰጠዋል (ያዕ 1:5)። ሰሎሞንም ለምኖ ተቀብሏል (1ነገ 3:5-9፤ 12፤ 4:29)።

**እግዚአብሔርን መፍራት የሌለበት ሕይወት የሰንፍና ኑሮ ነው።** ሰነፍ ሰው ኃጢአትን አቅልሎ የሚመለከት (14:9)፤ የእግዚአብሔርን ምክር የማይሰማ (12:15፤ 15:5)፤ በራሱ (በእውቀት፤ ችሎታ፤ ሀብት) የሚታመን (28:26)፤ የራሱን ሕልም የሚከተል (17:24፤ 18:4)፤ እግዚአብሔርን የሚወቅስ (19:3)፤ ኑሮን ያለ እግዚአብሔር ለመኖር የሚጥር ሰው ነው።

***መማር ያላቆመ*** ሰው ጥበበኛ ነው። ጥበበኛ ሰው ለመማር ይፈልጋል (12:1)፤ ያደምጣል (12:15፤ 21:11፤ 24:6)፤ ምክር ይጠይቃል (13:14፤ 19:20፤ 25:11)፤ ምክርንና ተግሳጽን በደስታ ይቀበላል (10:8፤ 23:12፤ 25:12)፤ የእግዚአብሔርን ምክር በመስማት ጥበብን ይጨምራል (1:5)።



# ምዕራፍ 21:-
# መጽሐፈ መክብብ

**ጸሐፊ:-** በኢየሩሳሌም የነገሠ የሰባኪው የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነው (1:1)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 935 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** የጉባዔ ስብከት የሚል ትርጉም ይዟል።[54] መክብብ ማለት ሰባኪ፤ አስተማሪ፤ በሰባኪው ዙሪያ የሚከቡ ሰሚዎች ወይም የጉባኤ ስብከት ማለት ነው። መደምደሚያ፤ መጨረሻ እንደ ማለትም ይሆናል።

**ዋና ሰዎች:-** ሰባኪው ሰሎሞን

**ዋና ሀሳብ:-** ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ከንቱ፤ የከንቱ ከንቱ መሆኑን ማሳየት ነው። ምድራዊ ስኬትን የሕይወት ዓላማና ግብ አድርጎ መኖር ከንቱ ነው። ሕይወት እንፋሎት፤ ጤዛ ነው፤ ያልፋል፤ ይጠፋል።

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ:-** ‹ከንቱ› 38 ጊዜ፤ ‹ሰባኪ› 7 ጊዜ፤ ‹ሁሉ ከንቱ› 6 ጊዜ፤ ‹የከንቱ ከንቱ› 3 ጊዜ፤ ‹ከፀሐይ በታች› 29 ጊዜ። ‹ጊዜ/ዘመን አለው› 39 ጊዜ፤

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች:-**

- ‹ሰባኪው:- ከንቱ፤ ከንቱ፤ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል› (1:2)።
- ‹የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንስማ፤ ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና፤ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትእዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፤ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፤ ወደ ፍርድ ያመጣዋልና› (12:13-14)።

---

[54] Gk *ecclesiastes*- "assembly" derived from ekkle„sia. "assembly, church." "The Hb- Qoheleth,- "one who convenes and speaks at an assembly." or "an ecclesiastic" or "preacher."

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** በ4 በመክፈል እንመለከተዋለን።

1. ዋናው ርዕስ (1፡1-3)
2. ሁሉ ከንቱ (1፡4-6፡12)
3. በከንቱነት ውስጥ ያለ ጥበብ (7፡1-12፡8)
4. ማጠቃለያ፡- ኑሮ ከፀሐይ በላይ (12፡9-14)

**1. ዋናው ርዕስ።** መጽሐፉ ‹ከንተ ከንቱ ከንቱ› በማለት ይጀምራል። ይህን እንደ ዋና ርዕስ በመውሰድ በቀሪዎቹ ክፍሎች ከተለያዩ የሕይወት ዘርፎች አንጻር ከንቱነቱን እያረጋገጠ ይሄዳል።

**2. ሁሉ ከንቱ።** ለሰው ከፀሐይ በታች ምን ትርፍ አለው? ብሎ በመጠየቅ የሁሉን ከንቱነት ያሳያል። **ኑሮ ከፀሐይ በታች** እንደ አዙሪት ቀለበት ነው፤ ዘላቂ ትርፍ የሌለው ድካም ብቻ ነው (1፡4-11)። ሰው የሚሠራው ሁሉ ከንቱ ነው (1፡14)፤ ጥበብን ፈልግ ግን እርሱም ከንቱ ነው (1፡17)፤ ደስታን ፈልግ እርሱም ቢሆን ከንቱ ነው (2፡11)፤ እወቀትም ከንቱ ነው (2፡17፤21፤23፤26)፤ ህብትም ከንቱ ነው (5፡8-6፡12)፤ ሁሉም ወደ አፈር ይሄዳል (3፡20፤ መጨረሻው ሞት ነው (2፡12-23)፤ ሁሉም ሰው ይሞታል (8፡9-9፡3)።

**3. በከንቱነት ውስጥ ያለ ጥበብ።** ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት የለም ብሎ የሚያስብ በዚህኛው ዓለም ለመደሰት የሚችለውን ሁሉ ይሞክራል (9፡1-10)። ሞት ሰውን ሁሉ እኩል ያደረገዋልና (8፡10-9፡6)፤ ስለዚህ ‹ብላ ጠጣ› ነው (2፡24፡ 3፡13፤22፤ 5፡18-19፤ 8፡15፤ 9፡7-9፤ 11፡9)። ሆኖም ፍርድ መምጣቱ አይቀርም (3፡17)። ሰው ዘላለማዊ ፍጡር ነው (3፡9-11)፤ ስለተሰጠው ስጦታ ሁሉ በእግዚአብሔር ይጠየቃል (3፡12-22)። ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት ይገባል (5፡1-9)።

**4. ኑሮ ከፀሐይ በላይ።** ሰው ምንም ያህል በተድላ ቢኖር፤ ከሞት አያመልጥም። ሰው ያለውን ሁሉ ሞት ስለሚነጥቀውና ራቁቱን ስለሚያስቀረው ሕይወት ትርጉም የለሽ ነው (2፡17)። የሀብት ብዛት ለሰው ጭንቀት ይጨምርበታል (5፡11-12)፤ ሲሞት ደግሞ ከሀብቱ ምንም ይዞ አይሄድም (5፡15)። ስለዚህ ከፀሐይ በታች ለሕይወት ትክክለኛ ትርጉም አይገኝም። ጥበበኛ ሰው ግን በወጣትነት ዘመኑ አምላኩን ያስባል (12፡1)። የከንቱነት መድኃኒቱ እግዚአብሔርን መፍራት ነው (12፡9-12)። **ስለዚህ ከፀሐይ በላይ ሙሉ ተስፋ አለ።**



**ክርስቶስ በመጽሐፈ መክብብ፡-**
ሰውን ከከንቱነት የሚታደግ፤ ትርጉም ያለውና የተትረፈረፈ ሕይወት የሚሰጥ ክርስቶስ ነው (ዮሐ 10፡10፤ 7፡37-38)።

**ዋና ትምህርት፡-**
**የሕይወት ሁለት መልኮች፡-** ከፀሐይ በታችና ከፀሐይ በላይ የሕይወት ሁለት መልኮች ናቸው። ሰው ኑሮን በራሱ ጥረት ብቻ ለመኖር ሲሞክር መጨረሻው የሰው ጥበብ ብቻ ይሆናል። ሕይወት ‹የመወለድ-ማደግ-መሞት› አዙሪት ሰንሰለት ብቻ ከሆነ አሰልቺ ነው። መኖር ለመደሰት፤ ለመዝናናት፤ ለዝና፤ ሀብት ለመከማቸት ብቻ ከሆነ ከንቱ፤ የከንቱ ከንቱ ኑሮ ነው። በአንድ ወቅት ያጓጓ ይሰለቻል፤ ያበበው ይጠወልጋል፤ ይደርቃል። ሰው ራሱን ለጥቶ የኖረለት ነገር ሁሉ እውነተኛና ዘላቂ ደስታን አያመጣም፤ መጨረሻው **ከፀሐይ በታች** የሆነ ከንቱ ኑሮ ነው። ኑሮ ትርጉም የሚኖረው ከእግዚአብሔር ጋር ሲኖር ነው። ይህ **ከፀሐይ በላይ** ነው።

**የኑሮ ዋና ግብ እግዚአብሔርን መፍራት፤ እርሱን ብቻ ማምለክና ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ነው።** ሰው ሁሉ የመኖሩ ዋና ግብ ምን እንደሆነ ይጠይቃል። ይህ የሕይወት ዋና ጥያቄ ነው። ‹ትውልድ ይሄዳል፤ ትውልድ ይመጣል› (1፡4) ግቡ ምንድን ነው? ሰዎች የሕይወትን ዋና ግብ ለማወቅ ብዙ ጥረዋል። የሕይወትን ዋና ግብ ለፈላስፋው ፕላቶ ‹እውቀት› ነው፤ ለአሪስቶትል ‹የተመጣጠነ ኑሮ› ነው፤ ለኢፒኩረስ ‹ተድላ› ነው።[55] የእነዚህ አይታ ጊዜያዊና ከፀሐይ በታች ነው።

ሰው የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዲያደርግ ነው። የመኖር ዋና ግብ እግዚአብሔርን በመፍራትና ቃሉን በመጠበቅ እርሱን ማምለክ ነው (12፡13)[56]። ስለዚህ አስተውል፡- አንተ ያለህ ነፍስ የራስህ ሳይሆን የተሰጠህ ነው። ሰጪው ነፍስህን ይፈልጋታል። መጽሐፍ ‹አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፤ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ›

---

[55] chief good in life, a *summum bonum*. *Plato* said it was knowledge. *Aristotle* suggested a well-balanced life, the golden mean between the two extremes. *Epicurus* and others believed that pleasure was the answer. http://home.hkstar.com/~johnfok1/OldTestamentSurvey/

[56] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፡- ‹እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትእዛዙንም ጠብቅ፤ ይህ የሰው ሁለንተናዊ ተግባሩ ነውና› ይላል።

(12፡7) ይላልና። ስለዚህ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር ክቡር ነው፤ ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው።

እንግዲህ ኑሮ ያለ እግዚአብሔር ከንቱ መሆኑን ፈትነህ ለማየት አትጣር፤ የጥበበኛውን ምክር ስማ! ጌታ ኢየሱስ ‹ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጕድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?› ብሏል (ማቴ 16፡26)።

**ለሁሉም ጊዜ** አለው። እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው (3፡11)። ከሰማይ በታች ለሁሉ የተመደበለት ጊዜ አለው (3፡1-8)። ለመወለድ፤ ለመሞት፤ ለመትከል፤ ለማልቀስ፤ **ለመሳቅ ጊዜ** አለው። እኛ የእነዚህን የብዙዎቹን ነገሮች ጊዜ መቆጣጠር አንችልም፤ ጊዜን ግን በአግባቡ መጠቀም እንችላለን። እኛ ጊዜን የሚቆጣጠረውን የእግዚአብሔርን አሠራር ተረድተን ከእርሱ ጋር በመተባበር (አብረን) መሥራት ጥበብ ነው።



# ምዕራፍ 22፡-
# መኃልየ መኃልይ

**ጸሐፊው፡-** ሰሎሞን (1፡1)። የሰሎሞን ስም በ1፡5፤ 3፡7፤9፤11፤ 8፡11-12 ተጠቅሶአል። አንድ ሺህ አምስት መኃልይ እንደጻፈ በ1ነገ 4፡32 እናነባለን።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 965 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** መኃልየ መኃልይ[57] ማለት ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር (1፡1) ማለት ነው።

**ዋና ሰዎች፡-** ሰሎሞን፤ የሱላማጢስ ሴት፤ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት።

**ዋና ሀሳብ፡-** የፍቅር መዝሙር ነው። በምሳሌያዊ አቀራረብ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር ያሳያል። ለመጋባት ያሰቡ ወንድና ሴት ከመጋባታቸው በፊትና ከተጋቡም በኋላ ስለሚኖራቸው ፍቅር። መጽሐፈ መክብብ በሰው አእምሮ (ወይም ኅሊና) ላይ ስለ ጥበብ የሚያተኩረውን ያህል መኃልየ መኃልይ ደግሞ በሰው ስሜት ላይ ስለ ፍቅር ያተኩራል።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ፍቅር 26 ጊዜ

**ቁልፍ ጥቅስ /ጥቅሶች፡-**

- ‹ውዴ የእኔ ነው፥ እኔም የእርሱ ነኝ› (2፡16፤ 6፡3)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን በ2 በመክፈል ማየት ይቻላል።

1. **የፍቅር ጅማሬና ሕብረት** (1-3)
2. **በፍቅር መኖር** (4-8)

[57] ኃለየ ማለት ዘመረ፤ ማኅልይ (ወይም ማህሌት) ዝማሬ ነው። መኃልየ መኃልይ ማለት ከሁሉ የሚበልጥ መዝሙር ወይም ምርጥ ዝማሬ ማለት ነው።

አስቀድመን ስለ መጽሐፉ መልእክት ምንነት ላይ የሚቀርቡ አስተያየቶችን እንመስከታለን። መጽሐፉ፡-

1. **ምሳሌያዊ (አሊጎሪካል) አነጋገር ይከተላል።** እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር ለማስተማር በምሳሌዊ አቀራረብ የተጻፈ ነው። ይህም ሰሎሞን እንደ ክርስቶስ፣ ሱላማጢስ ሴት ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን ናት የሚል ነው።

2. **ቀጥተኛ ትርጉም አለው።** መንፈሳዊ ትርጉም ሳይኖረው ከጋብቻ በፊትና በጋብቻ ውስጥ የሚኖረውን የወንድና የሴትን ፍቅር የሚሳይ ነው።[58]

3. **ቀጥተኛና ምሳሌያዊ ትርጉም አለው።** በጋብቻ ውስጥ በወንድና ሴት መካከል የሚኖረውን ፍቅር በምሳሌነት በማሳየት በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል፣ በአዲስ ኪዳንም ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የገለጸውን ፍቅር ያሳያል (ኤፌ 5፡22-27)። ስለሆነም ስለ ሴቲቱ ‹ነውርም የለብሽም› (4፡7) የሚለው ስለ ቤተ ክርስቲያን ‹…ያለ ነውር ትሆን ዘንድ› (ኤፌ 5፡27) ከሚለው ጋር ይመሳሰላል።

**የመጽሐፉን አከፋፈል።**

1. **የፍቅር ጅማሬና አንድነት።** ሰሎሞን የበግ ጠባቂዋን ልጅ ከወደዳት በኋላ በሁለቱ መካከል የሚደረግ ንግግር ነው። ራሱን ‹በሳሮን ጽጌ ረዳ፣ የቈለም አበባ› መስሎ ሲናገር የሚወዳት ሴት ደግሞ ‹በሾህ መካከል እንዳለ የሱፍ አበባ› በመመሰል ያደንቃታል (2፡1-2)። ጊዜው ምቹ ነው፣ ‹የዜማ ጊዜ ደረሰ› (2፡12)። አዝመራው መልካም ሆኗል ግን  የቀበሮዎች ጉዳይ ያሳስባል። ስለዚህ ‹የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች፣ ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዱችሁ ያዙልን› (2፡15)።

2. **በፍቅር መኖር።** በጋብቻ ግንኙነት ባል ሚስቱን በመውደድ (4፡7)፣ ‹እኔ የውዴ ነኝ፣ ውዴም የእኔ ነው› (6፡3) በሚል የእርስ በርስ ታማኝነት ይኖራሉ። በፍቅር ውስጥ ችግር ቢመጣ በጋራ

[58] በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ይህን መጽሐፍ ከ30 ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ሰዎች እንዳያነቡት አይሁድ ይከለክላሉ። The old rabbinical law stated that no Jew was to read the Song of Solomon until he was at least thirty years old. Such a precept is indicative of the puzzlement that the Song of Solomon has presented to many minds.



በማቃለል (5፡2-7፡10) ሕብረቱን በማጠናከር ፍቅራቸው ያድጋል (8፡5-7)።

**ክርስቶስ በመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ፡-**

በሰሎሞንና በሱላማጢስቱ ሴት መካከል የተነገረው የፍቅር ሁኔታ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ መሆኗን ያመለክታል (2ቆሮ 11፡2፣ ኤፌ 5፡23-25፣ ራእ 19፡7-9፣ 21፡9)።

**ዋና ትምህርት፡-**

**የጋብቻ ክቡርነትና ሞቅ ያለ አንድነት፡-** የፍቅር ሕብረት የሚኖረው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በጋብቻ ውስጥ በሆነ ግንኙነት ነው። አንዱ ለሌላው በተለጠ አኗኗር ሞቅ ባለ ፍቅር መኖር ይገባል።

**ጥቃቅኑን ቀበሮዎች መያዝ፡-** በጥሩ አንድነት ውስጥ ጥቃቅን የሚባሉ ችግሮች ሕብረትን ሊያበላሹና ትልቅ ጥፋት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ከማጥፋታቸው በፊት መወገድ አለባቸው። በባለትዳሮች መካከል ሊወገዱ የሚገባቸው ጥቃቅን ቀበሮዎች ለምሳሌ ወሬ፣ ሐሜት፣ ቁጣ ሊሆኑ ይችላሉ።

# ክፍል አራት
# የነቢያት መጻሕፍት

## ነቢይ

ነቢይ[59]- እግዚአብሔር የገለጠለትን ወይም ያዘዘውን መልእክት ለሰው በንግግር፤ በጽሑፍ፤ በምሳሌ ወይም በሌላ መንገድ የሚስተላልፍ ሰው ነው (ዘጸ 7:1-2)። ነቢያት ጉበኛ እና ባለ ራእይ በመባልም ይጠራሉ። ባለ ራእይ ሲባል ነቢዩ ከመንፈስ ቅዱስ መገለጥ (ወይም መረዳት) መቀበሉን ሲያመለክት (1ዜና 29:29፤ 2ሳሙ 24:11) ጉበኛ ደግሞ እንደ ከተማ ቅጥር ጠባቂ ወይም እንደ ሕዝብ እረኛ በሀገርና በሕዝቡ ላይ እየመጣ ያለውን አደጋ በመንፈስ በመረዳት ማስታወቅንና ማስጠንቀቅን ያሳያል (ሕዝ 3:17)።

እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆነውን እያንዳንዱን ሁኔታ ያውቀዋል። የሰው ታሪክ በልዑል እግዚአብሔር እጅ ነው። በሰማይና በምድር የሚሆነው ነገር ሁሉ ሁሉን በሚችል አምላክ ሥር ይተዳደራል፤ በእርሱ ፈቃድ ውስጥ ይከናወናል። ይህ ፈቃዱ የትዕዛዝ ፈቃድና የመፍቀድ ፈቃድ[60] ሊባል ይችላል።

በዚህ በክፍል አራት የምንመለከታቸው የነቢያት መጻሕፍት በ16 ጸሐፊዎች የተጻፉ 17 መጻሕፍት ናቸው። እነዚህ 16 ነቢያት ‹መጽሐፍ የጻፉ ነቢያት› በመባል ሊጠሩ ይችላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየስማቸው የሚጠራ መጽሐፍ የሌላቸው ነቢያት እንዳሉም ይታወቃልና። እነዚህን ደግሞ ‹የንግግር ነቢያት› እንበላቸው። ‹የንግግር ነቢያት› ማርያም (ዘጸ 15:20)፤ ዲቦራ (መሳ 4:4)፤ ጋድ (1ሳሙ 22:5)፤ አኪያ (1ነገ 11:29)፤ ኢዩ (1ነገ 16:7)፤ ኤልያስ (1ነገ 18:36)፤ ኤልሳዕ (2ነገ 9:1)፤ ሚክያስ (1ነገ 22:8)፤ ኢዶ (2ዜና 12:15)፤ ሸማያ (2ዜና 12:15)፤ አዛርያስ (2ዜና 15:1)፤ አናኒ (2ዜና 16:7)፤ የሕዚኤል (2ዜና 20:14)፤ አልዓዛር (2ዜና 20:37)፤ ያዲድ (2ዜና 28:9)፤ ሕልዳና (2ዜና 34:22)፤ ናታን (2ዜና 29:25) ናቸው።

[59] Hb. "*nibba*" - to summon, announce and call.

[60] የትዕዛዝ ፈቃድ (directive will) እንዲሆን የሚያዘው ሲሆን የመፍቀድ ፈቃድ (permissive will) ደግሞ አውቆ እንዲሆን የሚተወው ነው።



## የነቢያት መልእክት ይዘት

እውነተኛ ነቢያት የእግዚአብሔር ‹አፍ› በመሆናቸው በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው (እርሱ እንደሰጣቸው) ይተነብያሉ (ዘጸ 4:16-17፤ 7:1-2፤ 1ሳሙ 10:6፤ 2ጴጥ 1:21)። ስለሆነም የተሰጣቸውን መልእክት ሲያስተላልፉ ‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል› ይላሉ። ነቢያት ከእግዚአብሔር መልእክት የሚቀበሉት በራእይ፤ በሕልም ወይም ድምጽን በመስማት ነው (ዘኍ 12:5-8)።

ነቢያት የሚያስተላልፉት መልእክት የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሰጣቸው ሆኖ ይዘቱ የማስተማር (የእግዚአብሔርን እውነት መግለጽ)፤ የማጽናናት (እግዚአብሔርን በመታመን የሚጓዙትን ሰዎች ማበረታትና የምሕረት ቃል መናገር)፤ የማስጠንቀቅ (በኃጢአት የሚኖሩትን መገሰጽና በንስሐ እንዲመለሱ መምከር)፤ የመተንበይ (ወደፊት ሊሆን ያለውን ማሳወቅ) ይዘት ይኖረዋል።

## የነቢያት መልእክት ከጊዜ አኳያ

ከጊዜ አንጻር የነቢያትን መልእክት ላሉበት ዘመን የሚሆንና ስለ ወደፊቱ ዘመን የሚነገር በማለት በሁለት መክፈል ይችላል[61]። ላሉበት ዘመን የሚሆነውን መልእክት እንደገና የአሁንና የአሁን-ሩቅ እንበለው።

የነቢያት መልእክት ከጊዜ አኳያ




የአሁን ዘመን የምንለው አሁን ሕዝቡ ያለበትን ሁኔታ የሚገልጽና በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሊሆን ስላለውም ነገር የሚናገር ነው።

ስለ ወደፊቱ ዘመን የሚነገረው ደግሞ የሩቅና የሩቅ-ሩቅ ማለትም በብሉይ ኪዳን ዘመን በሩቁ ስለ ክርስቶስ መወለድና (ኢሳ 53)፤ በሩቅ-ሩቅ ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት (ኢሳ 11)) የተነገሩ ትንቢቶችን ያመለክታል። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ አንድ የትንቢት መልእክት ከጊዜ አንጻር በተለያየ ጊዜ የሚፈጸሙ መልእክቶችን ሊይዝል ይችላል ማለት ነው። ይህን ሁኔታ ሥዕሉ በጥቂቱ ያስረዳል።[62]

[61] Forthtelling (forth-telling)- **insight** into the will of God: **exhortative**, challenging men to obey. foretelling (fore-telling) - **foresight** into the plan of God: **predictive**, either encouraging the righteous in view of God's promises or warning in view of coming judgment.

[62] Jensen

# ክፍል 4.1
# ታላላቅ ነቢያት

የብሉይ ኪዳን ነቢያት መጻሕፍት በስፋታቸው (በምዕራፎቻቸው ብዛት) ታላላቅ ነቢያትና ደቂቅ ነቢያት በሚል በሁለት ይከፈላሉ። ይህ አከፋፈል የመልእክቱን ይዘት ሳይሆን ርዝመቱን ተከትሎ መጻሕፍቱን ለማጥናት እንዲያመች ታስቦ የተደረገ አመዳደብ ነው። ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክት ትንሽና ትልቅ የለውም። ታላላቅ ነቢያት የሚባሉት ኢሳይይስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ናቸው። ሰቆቃወ ኤርምያስ መጽሐፍ በታላላቅ ነቢያት ውስጥ የተመደበው ኤርምያስ እንደጻፈው ስለሚታመን ነው። የታላላቅ ነቢያት ዋና መልእክት፡-

- ኢሳይያስ- የእግዚአብሔር ማዳን
- ኤርምያስ- የእግዚአብሔር ፍርድ
- ሰቆቃው- በኢየሩሳሌምና በቤተ መቅደሱ መፍረስ ዋይታ
- ሕዝቅኤል- የእግዚአብሔር ልዕልናና ክብር
- ዳንኤል- የእግዚአብሔር መንግሥት

ኢሳይያስ ከምርኮ ዘመን በፊት የነበረ ሲሆን ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤልና ዳንኤል በምርኮ ዘመን የነበሩ ነቢያት ናቸው። ኤርምያስ ከምርኮው በፊት ጀምሮ በምርኮ ዘመን የቀጠለ ነቢይ ነው። የሕዝቅኤልና የዳንኤል አገልግሎት በባቢሎን ምድር ነበር። የታላላቅ ነቢያት አገልግሎት ዘመንና ትኩረት በሠንጠረዥ 24 በአጭሩ ቀርቦአል።

ሠንጠረዥ 24[63]

**ታላላቅ ነቢያት የአገልግሎት ዘመንና ትኩረት**

| ነቢይ | ለእይሁድ | ትኩረት | ጊዜው/ ነገሥታት | ዘመን |
|---|---|---|---|---|
| ኢሳይያስ | ለአይሁድ በይሁዳ 2ነገ 15-21፣ 2ዜና 26-30 | ይሁዳና ኢየሩሳሌም (1:1፡ 2:1) | የይሁዳ ነገሥታት (ዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አሀዝ፣ ሕዝቅያስ) | 740-680 ዓ.ዓ. |
| ኤርምያስ | ለአይሁድ በይሁዳና በምርኮ 2ነገ 22-25 | ይሁዳና አሕዛብ 1:5፤9-10፤ 2:1-2 | የይሁዳ ነገሥታት (ኢዮስያስ፣ ኢዮአክስ፣ ኢዮአቂም፣ ሰደቂያስ) | 627-585 ዓ.ዓ. |
| ሕዝቅኤል | ለአይሁድ በምርኮ ዳን 1-6 | ለእስራኤል በሙሉ (2:3-6፤፤ 3:4-10፤17) | ሰደቂያስ (ይሁዳ)፣ ናቡከደነፆር (ባቢሎን) | 592-570 ዓ.ዓ. |
| ዳንኤል | ለአይሁድ በምርኮና ለአሕዛብ ነገሥታት ዳን 1-6 | ለእስራኤልና አሕዛብ (2:36፤ 9) | ጀሆአኪም፣ ጀሆአቺን (ይሁዳ)፣ ናቡከደነፆር (ባቢሎን) | 605-536 ዓ.ዓ. |

[63] ራየሪ ገጽ 1117



## ምዕራፍ 23፡-
# ትንቢተ ኢሳይያስ

**ጸሐፊው፡-** የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ነው (1:1፤ 2:1፤ 7:3፤ 13:1፤ 20:1)። ከምርኮ በፊት በይሁዳ ያገለገለ ነቢይ ነበር። ከምዕ 1-39 ባለውና ከምዕ 40-66 ባለው መካከል የአጻጻፍ ስልት ልዩነት በማየት መጽሐፉ በኢሳይያስና በሌላ (ሁለተኛ) ኢሳይያስ እንደተጻፈ የሚያስቡ አሉ። ሆኖም በሁለቱም ክፍሎች ያለው የተጻፈው በአንድ ኢሳይያስ ነው። ጌታ ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር ያነበበው (ሉቃ 4:18-19) በኢሳ 61:1-2 የተጻፈውን ነበር።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 740-680 ዓ.ዓ.።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** ትንቢቱን በተናገረውና መጽሐፉን በጻፈው በነቢዩ ኢሳይያስ ነው።

**ዋና ሰዎች፡-** ኢሳይያስ[64]። የኢሳይያስ ሚስት ነቢይት ነበረች (8:3)። ያሱብ[65] (ቅሬታዎች ይመለሳሉ) (7:3)፤ ምርኮ ፈጠነ፤ ብዝበዛ ቸኩለ (8:4) የተባሉ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት። ለአገልግሎት ከልጁ ጋር የተላከበት ጊዜ ነበር (7:3)።

**ዋና ሀሳብ፡-** እግዚአብሔር አዳኝ (ታዳጊ) ነው። እግዚአብሔር ራሱ መከራ በሚቀበለው አገልጋይ (የኢየሱስ ክርስቶስ) በኩል ደህንነት ያመጣል። የመጽሐፉ የመጀመሪያ 39 ምዕራፎች በአመዛኙ ስለ ደህንነት አስፈላጊነት የሚናገሩትን (እንደ ብሉይ ኪዳን)፣ መከራ ስለሚቀበለው አገልጋይ (መሢሕ) መምጣትና በእርሱ በኩል ስለሚገኘው መዳን የሚናገሩትን 27 ምዕራፎች (እንደ አዲስ ኪዳን) በመውሰድና 66 ምዕራፎች ሰላሉት ‹ትንሹ መጽሐፍ ቅዱስ› በመባል ይታወቃል። መጽሐፉ 66 ጊዜ ያህል በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶአል።

[64] ይህን ነቢይ በ2ነገ 21:16 እና ዕብ 11:37 ከተጻፈው ጋር በማዛመድ ምናሴ የተባለው ንጉሥ በመጋዝ ሰንጥቆ እንደገደለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይናገራል።
[65] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፡- የኢሳይያስ ልጆች ስም በቅደም ተከተል ሾአር ያሹብ እና ማኸር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ ነው።

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ፡-** ‹የእስራኤል ቅዱስ› የሚለው ሐረግ 26 ጊዜ ይገኛል። ይህ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለውን የቃል ኪዳን ግንኙነት ያመለክታል። እንዲሁም ደህንነት 26 ጊዜ፣ ‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ› 21 ጊዜ፣ ‹እግዚአብሔር ንጉሣችን› 4 ጊዜ ይገኛሉ።

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፣ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች› (7፡14)።
- ‹ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል› (9፡6-7)።
- ‹የእስራኤል ቅዱስ፤ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ፤ በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል፤ እናንተም እንቢ አላችሁ› (30፡15)።
- ‹በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዘበዝን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፤ እንዲሁ አፉን አልከፈተም› (53፡4-7)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉ በአብዛኛው ስለ መፍረስ (ፍርድ)ና መታደስ (ምሕረት) ስለሚናገር በሁለት ዋና ክፍሎች መከፈል ይቻላል።

1. የፍርድ መልእክት (1-39)



2. የምሕረት መልእክት (40-66)

1. **የፍርድ መልእክት።** በይሁዳ ላይ እየቀረበ ስላለው ፍርድ ይናገራል። በይሁዳ ስለነበረው እውነተኛ ጽድቅ የሌለበት ውጫዊ ሃይማኖተኛነት በመናገር ጀምሮ ከቅጣት ማምለጫው መንገድ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ መመለስ መሆኑን በመግለጽ ያስጠነቅቃል። ይሁዳን በወይን አትክልት ምሳሌ በመግለጽ ገበሬው የሚገባትን ሁሉ አድርጎላት ጽድቅን ሲጠብቅ ያፈራችው ግን ክፋት፣ ስካር፣ ፍትህ ማጉደል ነበር። በዚህ መካከል በሩቁ እግዚአብሔር ያዘጋጀውንም ማዳን ማለትም ስለሚመጣው ‹አማኑኤል› ከምዕ 7-12 እናነባለን። ‹ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ› (9፡6) ነው። (ድንቅ- አምሳያ የሌለው፣ ልዩ፣ መካር- እውነተኛውንና ትክክለኛውን ምክር የሚሰጥ፣ ኃያል አምላክ- እርሱ መለኮት ነው፣ የዘላለም አባት- ዘመን የማይወስነው፣ አባታችን የሰላም አለቃ- ግዛቱ የሰላምና የጽድቅ የሆነ ነው)።

የእስራኤላውያን አጠቃላይ ሁኔታ ማስመሰል ስለነበር እግዚአብሔር ‹ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፣ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፣ በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈሩኛልና› (29፡13) ይላል። ይሁዳ በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ በአሦር ይደገፍ ነበር። ይህ ከሞት ጋር ቃል ኪዳን እንደማድረግ ነው (28፡15)፤ ሆኖም ‹የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ (እግዚአብሔርን) የሚያምን አያፍርም› (28፡16)። ከምዕ 13-35 ስለኃጢአታቸው በእስራኤል ላይ ብቻ ሳይሆን በአሕዛብ መንግሥታትም ላይ እግዚአብሔር እንደሚፈርድ ይናገራል። ከምዕ 36-39 ባለው ክፍል የሚናገረው ስለ ንጉሡ ሕዝቅያስ ነው (እንዲሁም 2ነገ 18-20ና 2ዜና 29-32)። በዚያን ዘመን የአሦር ንጉሥ የነበረው ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን ለመውረር በመጣ ጊዜ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ‹ደብዳቤውን ...ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው› (37፡14)። እግዚአብሔርም ታደገው።

2. **የምሕረት መልእክት።** ምዕ 40-48 ከባቢሎን አማልክት ይልቅ የእግዚአብሔርን ታላቅነት አጉልቶ ያሳያል። እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ ቂሮስን ለእስራኤል ያለውን ፈቃዱን ለማስፈጸም እንደሚጠቀምበት በምዕ 45 ይገልጻል። በኢሳ ምዕ 42-53 **እስራኤል** እንዲሁም **መሲሁ** ባሪያ (አገልጋይ) ተብለዋል። እስራኤል የእግዚአብሔር መልእክተኛ በመሆን ለአሕዛብ ብርሃን

እንድትሆን አገልግሎት (ጥሪ) ተሰጥቷት ነበር፤ አልተወጣችውም (41:8፤ 42:19፤ 43:10፡ 44:1፤2፤21፤ 45:4፤ 48:20)። እግዚአብሔር ይህን ለእስራኤል የተሰጠውን አገልግሎት እንዲፈጸም መሲሁን ላከ (49:5-7፤ 50:10፤ 52:13፡53:11)።

ከምዕ 49-57 ስለሚመጣው እግዚአብሔር ልጅ (መሲህ) አገልግሎት ያስረዳል። በተለይ ምዕ 53 የዚህን አገልጋይ ሥቃይና ክብር ይገልጻል። ይህ መከራ የሚቀበለው አገልጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ምንም እንኳን እኛ ሁላችን ወደ ገዛ መንገዳችን ብናዘነብል እርሱ ግን የሁላችንን በደል ተሸከመ (53:6)። ምዕ 58-66 እግዚአብሔር ለጽዮን ስለሚያመጣው ምሕረትና ፍርድ ሲናገር ‹ብርሃንሽ መጥቶአልና፤ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፤ አብሪ። እነሆ፤ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል፤ ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል› (60:1) ይላል። መጽሐፉ የሚጨርሰው እግዚአብሔር ስለሚያመጣው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፤ እንዲሁም ስለ መጨረሻው ፍርድ በመናገር ነው (66:22-24)።

**ክርስቶስ በትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ፡-**
ኢሳይያስ ስለሚመጣው መሲሕ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ብዙ ስለሚናገር በአንዳንዶች ዘንድ ‹ወንጌላዊው ነቢይ› የሚል ቅጽል ስያሜ ይሰጠዋል። በትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ከተነገሩት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ከድንግል ስለ መወለዱ (7:14፤ 9:6፤ 11:1)
- ከዳዊት ዘር ስለመሆኑ (11:1፤10)
- አገልጋይ አዳኝ ስለመሆኑ (49:1)
- ለአሕዛብ ብርሃን እንደሚሆን (42:6፤ 49:6)
- ስለ እኛ ኃጢአት መከራ እንደሚቀበል፤ እንደሚሞት (53)

**ዋና ትምህርት፡-**
**‹ኑና እንዋቀስ›**። እስራኤላውያን የመሥዋዕት እጥረት አልነበረባቸውም፤ በዓላትን ያደርጋሉ፤ ጸሎቱም አልተጓደለም (1:11-17)። ነገር ግን የሚናገሩትን በተግባር አይኖሩትም፤ ማስመሰልና ውጫዊ ሃይማኖተኛነት የሞላባቸው ሆነው ነበር።



ይህን ሁኔታቸውን ጌታ በማር 7:6-7 ጠቅሶታል። እስራኤላውያን በኃጢአታቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ› (ኢሳ 1:10) ሆነው ነበር። ኃጢአት ቢዘገይም መቀጣቱ አይቀርም። በንስሐ ወደ እርሱ በመቅረብ ምሕረት ይቀበሉ ዘንድ የምሕረት አምላክ እግዚአብሔር ለንስሐ ጊዜ ሰጣቸው፤ ‹ኑ› ብሎ ጠራቸው። **‹ኑና እንዋቀስ›** (1:18) ከቅጣት በፊት የተነገረ የእግዚአብሔር የምሕረት ጥሪ ነው። ዛሬም ባሕርይው አልተለወጠም፤ ጥሪውም ለሁላችን ያስተጋባል።

**የእግዚአብሔር አገልጋይ፡፡** እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን የላከው ሀሳቡን እንዲያገለግል ነው (42:1፤ ማር 10:45)። አገልጋይ የላከውን (የጌታውን) ፈቃድ የሚፈጽም ታማኝ ‹ባሪያ› ነው። እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚጠራቸውን ሰዎች ‹ባሪያዬ› ይላቸዋል። አብርሃም (ዘፍ 26:24)፤ ሙሴ (ዘጸ 14:31)፤ ኢያሱ (ዘጸ 33:11)፤ ካሌብ (ዘኁ 14:24)፤ ሳሙኤል (1ሳሙ 3:9)፤ ዳዊት (1ሳሙ 29:3)፤ ኤልያስ (2ነገ 9:36)፤ ኢሳይያስ (ኢሳ 20:3) ባሪያ ተብለዋል። የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ሰው ነቢይ፤ ንጉሥ፤ መሪ ቢሆን የተሰጠውን ያንን ኃላፊነት የእግዚአብሔር አገልጋይ (ባሪያ) በመሆን የሚወጣ ማለት ነው።

**የእግዚአብሔር ታላቅነትና ቅድስና፡፡** የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር ከአሕዛብ አማልክት ሁሉ በቅድስናው የተለየ ነው። ኢሳይያስ በአምልኮ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ሲመለከት የተደነቀው በቅድስናው ነበር (6:1-8)። እውነተኛ አምላክ እርሱ ብቻ ነው። ሌሎች ጣዖቶች የሰው እጅ ሥራዎች ናቸው (1:4፤ 17:7፤ 37:23፤ 45:11፤ 55:5፤ 60:14)። ሰው ሠርቶ የሚያመልካቸው፤ ሰው የቀደሳቸው፤ በሰው ‹ቅዱሳን› የተባሉ ናቸው። ይህ ቅድስና ከምድር ወደ ምድር፤ ከሰው ወደ ጣዖት የተላለፈ ነው። ስለዚህ ምድራዊ ነው፤ አጋንንታዊ ነው። እግዚአብሔር ግን በራሱ ቅዱስ ነው። እርሱ በቅድስናው ሰውን ይቀድሳል (ዘሌ 19:2)። ይህ ከሰማይ ወደ ምድር የሚመጣ ቅድስና ነው። ለኢሳይያስ የእግዚአብሔር ቅድስና የራሱን ኃጢአተኛነት ስላሳሳበት ‹ጠፋቻለሁና ወዮልኝ› አለ (6:5)። እግዚአብሔር ከንፈሩን በእሳት አነጻለት።

# ምዕራፍ 24፡-
# ትንቢተ ኤርምያስ

**ጸሐፊው፡-** የካህኑ የኬልቅያስ ልጅ ኤርምያስ ነው (1፡1፤ 2ዜና 35፡25)። ኤርምያስ የነቢይነት አገልግሎቱን የጀመረው በወጣትነት ዕድሜው ነበር(1፡16)። በሕዝቡ ላይ ሊደርስ ያለውን ቅጣት በማሰብ ስለሚያለቅስ (9፡1፤ 13፡17) ‹አልቃሻው ነቢይ› በመባል ይታወቃል። ኢየሩሳሌም በ586 ዓ.ዓ. ስትፈረስ አይቷል። የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም የኤርምያስን የመጀመሪያ ጽሐፍ በቢላዋ እየቆራረጠ በእሳት ስላቃጠለው በእሳት በተቃጠለው ብራና ላይ የነበረውን እንዲጽፍ ኤርምያስ ለባሮክ ነገረው (36፡20-26)።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 627-585 ዓ.ዓ.።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በጸሐፊው በነቢዩ ኤርምያስ ነው። ከኢሳይያስ ከ100 ዓመታት ያህል በኋላ የነበረና ለ40 ዓመታት ያህል በታማኝነት እግዚአብሔርን ያገለገለ ነቢይ ነበር።

**ዋና ሰዎች፡-** ኤርምያስ።

**ዋና ሀሳብ፡-** ቃል ኪዳኗን ያልጠበቀችው እስራኤል በንስሐ ባትመለስ እንደምትቀጣና ከምድሯ እንደምትነቀል፤ ብትመለስ ግን የመታደስ ተስፋ እንዳላት ማስገንዘብ ነው።

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ፡-** ‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል› የሚለው 139 ጊዜ፤ ‹የሠራዊት ጌታ› 72 ጊዜ፤ ‹ባቢሎን› 164 ጊዜ።

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹ነገር ግን ቃሌን ስሙ፤ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፤ መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ ብዬ በዚህ ነገር አዘዝኋቸው። ነገር ግን በክፉ ልባቸው አሳብና እልከኝነት ሄዱ ወደ ፊትም ሳይሆን ወደ ኋላቸው ሄዱ እንጂ አልሰሙም ጆሮአቸውንም አላዘነበሉም› (7፡23-24)።



- ‹የሕዝቤንም ሴት ልጅ ስብራት በጥቂቱ ይፈውሳሉ፤ ሰላም ሳይሆን። ሰላም ሰላም ይላሉ› (8፡11)።
- ‹ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም› (29፡11)።
- ‹እነሆ፤ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም፤ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፤ እኔም ቸል አልኋቸው፤ ይላል እግዚአብሔር። ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። እያንዳንዱ ለው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን። እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፤ ይላል እግዚአብሔር። በደላቸውን እምራቸዋለሁና፤ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና› (31፡31-34)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** በይሁዳና በአሕዛብ ላይ ከተነገሩት ፍርዶች አንጻር በ2 በመክፈል እንመለከተዋለን።

1. በይሁዳ ላይ የሚመጣው ፍርድ (1-45)
2. በአሕዛብ መንግሥታት ላይ የሚመጣው ፍርድ (46-52)

**1. በይሁዳ ላይ የሚመጣው ፍርድ።** ኤርምያስ ለአገልግሎት ሲጠራ እግዚአብሔር ባሳየው ራእይ ‹...የሚፈላ አፍላል አያለሁ፤ ፊቱም ከሰሜን ወገን ነው አልሁ። እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ። ከሰሜን ወገን ክፉ ነገር በምድሪቱ በተቀመጡ ሁሉ ላይ ይገለጣል› (1፡13-14) እንዳለው ይህ አፍላል ቀስ እያለ ፈልቶ በይሁዳ ላይ ፈሰሰ። እግዚአብሔር እንዲመለሱ ብዙ ጊዜ ተናገረ (3፡12)፤ ሕዝቡ ግን አልሰማም። የቤተ መቅደሱ አምልኮ

ሥርዓት አልተጓደለም (7:3-11) ግን ‹የሰማይ ንግሥት›[66] (7:18) ጣዖትን በቤተ መቅደስ ውስጥ እስከመከተል ድረስ በኃጢአት ውስጥ ተዘፈቁ። በይሁዳ ላይ የሚመጣውን መከራ በማመልከት ሚስት እንዳያገባና ልጆቹም እንዳይኖሩት ታዟል (16:1-4)። የሰባ ዓመት ምርኮ እንደሚኖር ተናገረ (ኤር 25:1-14)።

ይሁዳ በባቢሎን እጅ እንደምትወድቅ በአንገቱ ቀንበር አስገብቶ በምሳሌነት ሁሉ አሳይቷል (27:1-12)። ይህ ሁኔታ ኤርምያስን ‹ሀገሩን ከዳተኛ› የሚያሰኘው ነው። ካህናትና ነቢያት ምክር ጠይቀውት ከመልእክቱ ‹ጥንካሬ› የተነሣ ይጣሉት ነበር (11:18-23፤ 12:6፤ 18:8፤ 20:1-3፤ 26:1-24፤ 37:11-38:28)። ወደ እስር ቤትም ጥለውታል። ባቢሎን ኢየሩሳሌምን በማረከች ጊዜ ኤርምያስ ወደ ባቢሎን ለመሄድ ወይም እዚያው ለመቅረት ምርጫ ሲሰጠው እዚያው መሆንን መረጠ (40:4-6)። በኋላ እስራኤላውያን የይሁዳ አስተዳዳሪ እንዲሆን ባቢሎናውያን የተሾመውን ጎዶልያስ ገድለው (41:2) ኤርምያስን ወደ ግብጽ ወሰዱት። ኤርምያስ በዚያም በነቢይነት አገልግሎቱ ቀጠለ (43-44)።

**2. በአሕዛብ መንግሥታት ላይ የሚመጣው ፍርድ።** ስለ ዘጠኝ የአሕዛብ መንግሥታት የተነገሩ ትንቢቶች ከምዕ 46-52 ይገኛሉ። ይህም የእስራኤል ብቻ ሳይሆን የሁሉም አገሮች መዳረሻ በእግዚአብሔር እጅ መሆኑን ያሳያል። ይሁዳን የማረኩ አገሮች እነርሱ ደግሞ በተራቸው እንደሚቀጡ ሲናገር ‹…እንተንም ያስደድሁባቸውን አሕዛብን ሁሉ ፈጽሜ አጠፋለሁና› (46:28) ይላል። መሣሪያው (ማለትም በአንድ ዘመን እግዚአብሔር ሀሳቡን ለመፈጸም የተጠቀመበት ወገን) ራሱ ደግሞ በተራው በቅን ይፈረድበታል፤ ስለ ኃጢአቱ ይቀጣል። ይህ የእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ ነው።

[66] የሰማይ ንግሥት 44:18- የኢሽታር መጠሪያ ነበር። የባቢሎን የመባዛት ጣዖት ነበረች። በኢዮስያስ እስኪተወገድ ድረስ (2ነገ 22) እስራኤላውያን በተለይም ሴቶች ያመልኩአት ነበር። ይህን ካቋረጡ ከ35 ዓመታት ያህል በኋላ እንደገና ይጸጹቱና ወደ አምልኮ ይመለሱ ነበር።



**ክርስቶስ በትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ፡-**
ትንቢተ ኤርምያስ ስለ ክርስቶስ ከሚያመለክታቸው ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ሕያው የውኃ ምንጭ (2:13)- ዮሐ 4:14
- የሚጠብቅ እረኛ (23:4)
- የሚነሣው የዳዊት ቅርንጫፍ (23:5)
- የጽድቅ ንጉሥ (23:6)
- ከዳዊት ዘር የሚመጣ ንጉሥ (33:17)

ኤርምያስ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት በስፋት የተናገረና የጻፈ ነቢይ ነው። ሠንጠረዥ 25 ጥቂቶቹን ያሳየናል።

ሠንጠረዥ 25
የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጹ ክፍሎች በትንቢተ ኤርምያስ

| ክፍሉ | የእግዚአብሔር ባሕርይ |
|---|---|
| 2:13 | ሕያው የውኃ ምንጭ |
| 3:12 | መሐሪ |
| 4:28 | ሀሳቡን አይለውጥም |
| 7:16፤ 11:14 | ጸሎትን የማይሰማበት ጊዜ አለ |
| 8:7 | ይፈርዳል |
| 9:23-24 | ምሕረት፤ ፍርድ፤ ጽድቅ |
| 10:10 | ሕያው አምላክ የዘላለም ንጉሥ ነው |
| 10:12-16 | ፈጣሪ |
| 10:13 | የፈጠረውን የሚጠብቅ/የሚደግፍ |
| 11:20 | ሃሳብንና ልብን ይመረምራል/ ይፈትናል |
| 12:1 | ጻድቅ ነው |
| 13:16 | ክብር የሚገባው ነው |
| 18:6 | እንደ ሸክላ ሠሪ ነው፤ አፍርሶ የሚሠራ |
| 20:11 | አስፈሪና ታላቅ ነው |
| 20:12 | ጻድቃንን ይመረምራል |
| 21:8 | ምርጫን ይሰጣል |
| 23:23-24 | ሁሉም ቦታ ይገኛል |
| 23:29 | ቃሉ ሥልጣን አለው |
| 27:5 | ምድርን ለወደደው ይሰጣል |
| 29:11-13 | ለእኛ የሚያስበው ሀሳብ የመልካም ሀሳብ ነው |
| 31:3 | በዘላለም ፍቅር ይወዳል |
| 32:17፤27 | የሚሳነው ነገር የለም |
| 32:18 | ታላቅ ነው |
| 32:19 | በምክሩ ድንቅ ነው |
| 33:11 | መልካም ነው |
| 34:13 | ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል |

**ዋና ትምህርት፡-**
**የሰሚዎች እድናቆትና ‹ስኬታማነት› ለአገልግሎት ፍሬያማነት ዋናው መለኪያ አይደለም።** ኤርምያስ የነበረበት ጊዜ ‹ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፤ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፤ ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ› (5:31)

የተባለበት ዘመን ነው፡፡ እውነተኛ ትንቢት የሚናገረው ኤርምያስ ደግሞ በካህናትና በነቢያት የተጠላ፤ የጻፈው የተቀደደበት፤ በእግር ብረት የታሰረ ሰው ነው፡፡ ኤርምያስ ሚስት ሳያገባና በገዛ ሕዝቡ መካከል ‹የብቸኝነት ኑሮ› የኖረ ነቢይ ነበር፡፡ ይህም ሁሉ ቢሆን ከማህጸን ሳይሠራ የተለየበትን ዓላማ ጸንቶ የፈጸመ ደፋር ነቢይ ነበር፡፡

**ነቢይ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መልእክት የሚያስተላልፍ፤ ሕዝቡንም በመውደድ የሚጸልይ ነው፡፡** ኤርምያስ የጸሎት ሰው ነበር፡፡ የሚያገለግለውን ሕዝብ ይወድ ነበር፡፡ በአንድ መልኩ ቧንቧ ሰውኃ እንደሆነ ነቢይም ለተቀበለው መልእክት መሆን ሲኖርበት በሌላ መልኩ ደግሞ ነቢይ ለሚያገለግለው ሕዝብ ፍቅር ያለውና የሚጸለይም ሲሆን እንደሚገባ የነቢዩ ኤርምያስ ሕይወት ይመሰክራል (14:7፤20)፡፡ ኤርምያስ ሕዝቡን ከመወደዱ የተነሳ ስለ ሕዝቡ ያለቅስ ነበር (8:21-9:1)፡፡ የእግዚአብሔር ሀዘን የገባው ሰው ነበር፡፡ መጸለዩን አቁም እስከተባለበት ጊዜ ድረስ ይጸልይ ነበር (11:14)፡፡ ነቢይ ‹የተሰጠኝን ተናግሬአለሁ፤ የተቀረው የሕዝቡ ጉዳይ ነው› የሚልና በግድ የለሽነት የሚመላለስ ሰው ሳይሆን የሚያገለግለውን ሕዝብ በመውደድ አገልግሎቱን የሚፈጽም መሆን አለበት፡፡

**እግዚአብሔር ጸሎት የማይሰማበት ጊዜ፡፡** እግዚአብሔር ኤርምያስን ‹ለዚህ ሕዝብ ስለ መልካም አትጸልይላቸው› (ኤር 14:11)፤ እንዲሁም ‹ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ፤ …አልሰማቸውምና ስለ እነርሱም ጩኸትና ልመና አታድርግ› (11:14) አለው፡፡ በሌላም ቦታ ሌሎችን አማልክት በማምለክ እግዚአብሔርን ስላስቆጡ ‹ልመናና ጸሎት አታድርግ፤ አትማልድላቸው› (7:16) ‹ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም፤ ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አያዘነብልም› (15:1) አለ፡፡ ሙሴ ስለ ሕዝቡ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ‹እንደ ቃልህ ይቅር አልሁ› (ዘኍ 14:20፤ ዘጸ 32:11-) አለው፡፡ ‹ሳሙኤልም ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ሰማው› (ሳሙ 7:9)፡፡ አሁን ግን ጸሎታቸውን አልሰማም ይላል፡፡ ‹በተናገርኋቸው ጊዜ አልሰሙምና፤ በጠራኋቸውም ጊዜ አልመለሱልኝምና› (ኤር 35:17)፡፡ ስለዚህ ጸሎትን እንዳይሰማ የሚከለክል ሁኔታ አለ (ሕዝ 20:3)፡፡



## ምዕራፍ 25፡-

# ሰቆቃወ ኤርምያስ

**ጸሐፊው፡-** ነቢዩ ኤርምያስ ነው፡፡ ‹አልቃሻው ነቢይ› የተባለውና ኢየሩሳሌም ስትማረክ ያየ ሰው ነው (1:13-15፤ 2:6፤9፤ 4:1-12፤ ኤር 14:17-22)፡፡

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 586/5 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** ሰቆቃወ[67] ማለት ለቅሶ ወይም ዋይታ ማለት ነው፡፡

**ዋና ሀሳብ፡-** በኃጢአት ምክንያት በኢየሩሳሌም ላይ በመጣው መከራና መፍረስ የሚያተኩር ዋይታ ወይም ሀዘን ነው፡፡ (ጌታ ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም እንዳለቀሰላት (ሉቃ 13:34-35፤ 18:41-44))፡፡ በኢየሩሳሌም የሆነው ሁሉ እግዚአብሔር እንደተናገረው መሆኑን፤ ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ ያልጠፋትም ከምሕረቱ የተነሣ እንደሆነ ያሳይና በንስሐ የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲሰምኑ ይመክራል፡፡

***ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ፡-*** መጽሐፉ ከሌሎች መጻሕፍት የተለየ አቀራረብ ይከተላል፡፡ የግጥም መልክ አለው፡፡ ከ5ቱ ምዕራፎች ውስጥ 4ቱ እያንዳንዳቸው 22 ቁጥሮች ሲኖራቸው ምዕ 3 ደግሞ 66 ቁጥሮች አሉት፡፡ ከምዕ 5 በስተቀር ሌሎቹ በ22ቱ የዕብራይስጥ ፊደላት ቅደም ተከተል ተጽፈዋል፡፡ በምዕ 3 የዕብራይስጡ ፊደላት የሚገኙት በየ3 ቁጥር ነው፡፡

[67] በግዕዝ፡ አሰቆቀወ - አለቀሰ ሲሆን ሰቆቃወ - ለቅሶ፤ ዋይታ፤ ሙሾ ማለት ነው፡፡ ሰቆቃወ ኤርምያስ ማለት የኤርምያስ ለቅሶ (ዋይታ) ነው፡፡ Gk. *Threnoi*- "lamentations." to cry aloud"}.

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፣ ርኅራኄው አያልቅምና። ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፣ ታማኝነትህ ብዙ ነው› (3:22-23)።
- ‹ጌታ ለዘላለም አይጥልምና፣ ቢያሳዝንም እንደ ምሕረቱ ብዛት ይራራልና፣ የሰውን ልጆች ከልቡ አያስጨንቅም፣ አያሳዝንምም› (3:31-33)።
- ‹አቤቱ፣ ወደ አንተ መልስን እኛም እንመለሳለን፣ ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ› (5:21)።

***የመጽሐፉ አከፋፈል:-*** *መጽሐፉን በምዕራፎቹ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።*

- *ዋይታ:- ኃጢአት በኢየሩሳሌም ላይ ስላስከተለው መራራ ነገር (ምዕ 1)*
- *ዋይታ:- በሕዝቡ ላይ ስለተገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣ (ምዕ 2)*
- *ዋይታ:- ጸሐፊው የግል ስሜቱን በመግለጽ (ምዕ 3)*
- *ዋይታ:- በኃጢአት ምክንያት የተሸነፈችዋ ኢየሩሳሌም (ምዕ 4)*
- *ዋይታ:- የእግዚአብሔርን ምሕረት በመለመን (ምዕ 5)*

በኢየሩሳሌም ላይ ያልታሰበ ነገረ ሆኗል (4:12)፣ እግዚአብሔር የሚጠብቃት ከተማ በጠላት እጅ ወደቀች፣ ይህንም የእግዚአብሔር እጅ አደረገው (1:5፣12-15፣17፣ 2:1-7፣17፣21-22፣ 4:11፣16)። ኢየሩሳሌም መቼም ቢሆን በጠላት እጅ አትወድቅም ብለው አይሁድ ቢያስቡም እርሱ ሆነ (ኤር 7:4-15)። ይህም ስለ ኃጢአት የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ፍርድ ያሳያል።

**ክርስቶስ በሰቆቃወ ኤርምያስ መጽሐፍ:-**
ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ ኤርምያስ አለቀሰ (3:48-49)፣ ክርስቶስ የመጐብኘትዋን ዘመን ላላወቀችውና የጭንቀቷ ቀን ስለቀረበው ለኢየሩሳሌም አለቀሰ (ማቴ 23:37-38፣ ሉቃ 19:41-44)።



**ዋና ትምህርት:-**
**በኃጢአት ምክንያት የማይታሰበው ይደርሳል።** በኢየሩሳሌም በር ጠላትና አስጨናቂ እንደሚገባ ሕዝቡ አላመኑም ነበር (4:12)። ኢየሩሳሌም አብርሃም ልጁን ይስሐቅን መሥዋዕት ለማድረግ ያቀረበበት ስፍራ፣ የንጉሥ ዳዊት ከተማ፣ ሰሎሞን ያሠራው ቤተ መቅደስ የሚገኝበት፣ በዚያ ቦታ የሚጸለየውን ጸሎት እግዚአብሔር ለመስማት ያለበት ስፍራ፣ ቤተ መቅደሱ ከ300 ዓመት በላይ በክብር የቆየበትና መሥዋዕት የሚቀርብበት ቦታ በጠላት እጅ ይወድቃል! ቤተ መቅደሱም ይፈርሳል! ብሎ ማንም አላሰበም። ግን ሆነ (1:10)። ያውም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሆነ (1:17)። ኢየሩሳሌም ለሰቀስች የሚያጽናናትም አልነበረም፣ ሁሉም እግዚአብሔር እንደተናገረው ሆነ (2:17)። በኃጢአት ለሚቀጥል ሰው እግዚአብሔር እንደ ጠላት ሆኖ ይነሳበታል (2:5-6) ጉስቁልናም አይቀሬ ነው። በዚህም ውስጥ የእግዚአብሔር ታማኝነት ብዙ ነው። ሁልጊዜም መሐሪው እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ነው። ‹አቤቱ፣ ወደ አንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን፣ ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ› (5:21)።

# ምዕራፍ 26፡-

# ትንቢተ ሕዝቅኤል

**ጸሐፊው፡-** የቡዝ ልጅ ካህኑ ሕዝቅኤል ነው፡፡ ጥሪ የደረሰው ከምርኮኞች መካከል በከሰዳውያን አገር (በባቢሎን) ሆኖ ነበር (1፡1-3)፡፡ ተማርከው ወደ ባቢሎን ስተወሰዱት በመካከላቸው ሆኖ የተናገረው ትንቢት ነው፡፡ ኤርምያስ በይሁዳ ሆኖ ሲያገለግል ሕዝቅኤል በባቢሎን ነበር፡፡ እንደ ኤርምያስ ሁሉ ሕዝቅኤልም ካህን ነበር፡፡

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 592-570 ዓ.ዓ.፡፡

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በጸሐፊው በሕዝቅኤል ነው፡፡

**ዋና ሰዎች፡-** ሕዝቅኤል[68]፡፡

**ዋና ሀሳብ፡-** በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ፍርድና ከዚያ በኋላ ስለሚኖረው የመታደስ ተስፋና አዲስ ኪዳን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ክብር ይህን ይፈጽማል፡፡

**ተደጋጋሚ ቃል/ ሐረግ፡-** ‹እኔ አምላክ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ› ወይም ‹እኔ አምላክ እንደሆንሁ ያውቃሉ› 72 ጊዜ፤ ‹የእግዚአብሔር ቃል መጣ› 60 ጊዜ፤ ‹ቅዱስ› 47 ጊዜ፤ የእግዚአብሔር ክብር 10 ጊዜ፤ ‹ጠላት ሆኘባቸዋለሁ› 100 ጊዜ፡፡ መንፈስ ቅዱስ 14 ጊዜ ተጠቅሶአል (ሰምሳሌ 2፡2፤ 3፡12፤14፤24፤ 8፡3፤ 11፡1-2፤5፤ 24(2)፤ 36፡27፤ 37፡1፤14፤ 39፡29፤ 43፡5)፤ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ሲጠራው 93 ጊዜ ያህል ‹የሰው ልጅ› ብሎታል፡፡

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፤ ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፤ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም፤ የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፤ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል... በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን?› (18፡20-23)፡፡

[68] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሕዝቅኤል የተገደለው በፈረስ ተጎትቶ ወይም አንገቱ ተቆርጦ እንደነበር ከማቴ 23፡29-31፤ ሉቃ 11፡47-47፤ ሐዋ 7፡52 ጋር በማዛመድ ይገልጻል፡፡



- ‹ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አላገኘሁም› (22፡30)፡፡
- ‹እርሱም እንዲህ አለኝ፡፡ በእነዚህ አጥንቶች ላይ ትንቢት ተናገር እንዲህም በላቸው፡፡ እናንተ የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል፡፡ እነሆ፥ ትንፋሽን አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ› (37፡4-5)፡፡

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉ እንደ ትንቢተ ዳንኤልና የዮሐንስ ራእይ በርካታ ምሳሌያዊና ሰዕላዊ (አፖካሊፕቲክ[69] የሆኑ) አገላለጾች ያሉት በመሆኑ በቀላሉ ለመረዳትና ለመተረጎም ያስቸግራል፡፡ ሆኖም መጽሐፉን በአራት በመክፈል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

1. የእግዚአብሔር ክብር (1-3)
2. በኢየሩሳሌም ላይ የተነገሩ ትንቢቶች (4-24)
3. በአሕዛብ ላይ ፍርድ (25-32)
4. በሕዝቡ ላይ የሚመጣ በረከት ወይም ተሐድሶ (33-48)

**1. የእግዚአብሔር ክብር፡፡** መጽሐፉ ብዙ ሥዕላዊ አገላለጾች (ትንቢታዊ ራዕዮች) አሉት፡፡ ሕዝቅኤል ሰማይ ተከፍቶ አይቶአል፤ የእግዚአብሔር ክብር ተገልጦ በራእይ ተመልክቶአል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ክብር በመጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ ተገልጾአል፡፡ ናቡከደነጾር ለሁለተኛ ጊዜ (በ597 ዓ.ዓ) ይሁዳን ሲማርክ ሕዝቅኤል ወደ ባቢሎን ታስሮ ተወሰደ (1፡1-2፤ 33፡21)፡፡ ዕድሜው 25 ዓመት ያህል እንደነበረ ይገመታል፡፡ በባቢሎን ቴልአቢብ በተባለ ሰፈር የራሱ መኖሪያ ነበረው (3፡15፤ 3፡24)፡፡ በቤቱም ስብሰባ ይደረግ ነበር (8፡1፤ 14፡1፤ 20፡1)፡፡ ሕዝቅኤል የሚያስጠነቅቅ ጉበኛ (ጠባቂ) እንዲሆን ተጠራ (3፡16-

[69] አፖካሊፕቲክ "The word apocalypse is a Greek word meaning "revelation." Therefore. apocalyptic literature is a special kind of writing that ...reveal certain mysteries about heaven and earth, humankind and God, angels and demons, the life of the world today, and the world to come". **Nelson's Illustrated Bible Dictionary**, (1986). Thomas Nelson Publishers.

27)። ኢየሩሳሌም በባቢሎን ስትከበብ በእግዚአብሔር ዲዳ የተደረገ ይህ ነቢይ (3:26-27) መናገር የጀመረው በባቢሎን ከተማረከች ከሁለት ዓመታት ያህል በኋላ ነው (24:27)።

**2. በኢየሩሳሌም ላይ የተነገሩ ትንቢቶች።** ሕዝቅኤል በራእይ ወደ ኢየሩሳሌም ተወሰደ (8:3)። በቤተ መቅደሱ ውስጥ ጣዖት አምልኮ (8:5፤10)፤ ጸሐይ አምልኮ (8:16) ተመለከተ። ሕዝቅኤል ለእስራኤል ቤት ‹ምልክት› ነበር (12:6)። በምልክት ብዙ አስተምሮአል። ለምሳሌ በግራ ጎኑ ተኛ ከዚያ በቀኝ ጎኑ ተኛ (4:4-)። ለብዙዎች መሳለቂያ ሆኖአል። የእግዚአብሔር ክብር ከኢየሩሳሌም ተወሰደ፤ ፍርድ መምጣቱ እርግጠኛ ነው። በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ ይፈርሳል። በኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጻል። ይህ በጸሎታቸው የሚታወቁትና እግዚአብሔር ጸሎታቸውን የሰማላቸው ኖህ፤ ዳንኤልና ኢዮብ (14፤14፤20) እንኳ ቢጸልዩም ይህ የማይቀር በእግዚአብሔር የተወሰነ ነገር ነው።

**3. በአሕዛብ ላይ ፍርድ።** ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር የተከበበችበት ቀን የተመዘገበ ነው (24:2)። ሕዝቅኤል ያገባ ሰው ነበር (24:25-28)። ሚስቱ እንደምትሞት ጠዋት ተናግሮት ማታውኑ ሞተች (24:15-18)። ምንም እንኳ ኢየሩሳሌም በኃጢአቷ ምክንያት ብትፈርስም በዙሪያዋ የነበሩ አገሮች ደግሞ ስትከበብ ባለማገዛቸው፤ በእርሷ ላይ በደረሰው ፍርድ ደስ በመሰኘታቸውና በበደላቸው እያንዳንዳቸው በተራቸው መቀጣታቸው አይቀርም።

**4. በሕዝቡ ላይ የሚመጣ በረከት ወይም ተሐድሶ።** ከኢየሩሳሌም መማረክና መፍረስ በኋላ (33) እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደገና ሕይወትን እንደሚሰጣት በደረቁ አጥንቶች (37) ምሳሌ ተናገረ። የደረቁ አጥንቶች ራእይ እስራኤል በምርኮው ዘመን የነበራትን ኑሮ የሚገልጽ ምሳሌ ነው። ለሞቱ ነገሮች ሕይወት የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። ለምርኮኞች ነጻነት ሰጥቶ ወደ ምድራቸው የሚመልስ እርሱ ነው። ‹ሕዝቤ ሆይ፤ መቃብራችሁን በከፈትሁ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኋችሁ ጊዜ፤ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ፥ በገዛ ምድራችሁም አኖራችኋለሁ› (37:13-14) አለ። እንዲሁም ከምርኮው ዘመን በኋላ ሰሎሞን ካሠራው ቤተ መቅደስ የሚበልጥ ቤተ መቅደስ እንደሚሠራ የእግዚአብሔርም ክብር ወደዚህ ቤተ መቅደስ እንደሚመለስ ተናገረ (40-48)።



**ክርስቶስ በትንቢተ ሕዝቅኤል መጽሐፍ።**
እስራኤል ኃላፊነታቸውን የተወጡ እረኞች (ሕዝ 34:11-31) ባይኖሯትም መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ (ዮሐ 10) ይመጣል። እርሱ የሚገዛ ንጉሥ (21:26-27)፤ የዳዊት ዘር (37:24-25) ነው።

**ዋና ትምህርት፦**
**የእግዚአብሔር ክብር።** ይሁዳ የእግዚአብሔርን ምክርና ማስጠንቀቂያ ባለመስማቷ የእግዚአብሔር ክብር ደረጃ በደረጃ ከቅድስተ ቅዱሳን ተነስቶ ወደ አደባባዩ ሄደ (10:4)፤ ቤተ መቅደሱንም ትቶ ወደ ምሥራቁ በር ሄደ (10:18-19)፤ ከዚያም ኢየሩሳሌምን ትቶ ሄደ (11:22)። የተስፋው ዘመን ሲሞላ የእግዚአብሔር ክብር ወደ አዲሱ ቤተ መቅደስ ተመለሰ (43:1-5)። ክብር የእግዚአብሔር በአንድ ቦታ በሙላት መገኘት ነው (ዘጸ 16:10፤ ኢሳ6:3)። እርሱ እንደ ቃሉ በሚመለክበት፤ ነውር የሌለበት መሥዋዕት በሚቀርብበት በዚያ ይገኛል (ዘሌ 9:6፤22)። እግዚአብሔር ከጣዖታት ጋር በደባልነት አይገኝም እንዲህ ሲሆን በሕዝቅኤል ዘመን በኢየሩሳሌም እንደሆነው ‹ክብር› ይሰቃል። ይህም ‹ኢካቦድ› ያባላል (1ሳሙ 4:21)። የእግዚአብሔር ክብር ሲለቅ ለሕዝቡ ውርደት ይከተላል።

**ቁም፤ ስማ፤ ብላ፤ ሂድ።** እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የአገልግሎት ትእዛዝ የሰጠው ‹በግርህ ቁም› (2:1)፤ ‹የምነግርህን ስማ› (2:8)፤ ‹ይህን መጽሐፍ ብላ› (3:1)፤ ‹ተነሥተህ ወደ እስራኤል ቤት ሂድ ቃሌንም ተናገራቸው› (3:4) በማለት ነው። እግዚአብሔር አገልጋዮቹን የሚጠራበት መንገድ ልዩ ልዩ ነው። አብርሃምን በመናገር (ዘፍ 12)፤ ዮሴፍን በሕልም (ዘፍ 37)፤ ሙሴን በሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ በድምጽ (ዘጸ 3)፤ አሮንን በወንድሙ በሙሴ በኩል (ዘጸ 4)፤ ኢያሱን በሙሴ በኩል (ዘጸ 17)፤ ጌዴዎንን በመልአኩ በኩል (መሳ 6)፤ ሳሙኤልን በድምጽ (1ሳሙ 3)፤ ዳዊትን በሳሙኤል በኩል (1ሳሙ 16)፤ ኢሳይያስን በድምጽ (ኢሳ 6:6-9)፤ ኤርምያስን በድምጽ (ኤር 1)፤ ሕዝቅኤልን በድምጽ (2:1-3) ነበር። የነቢዩ አገልግሎት ‹ሰዎች ቢሰሙ ወይም ባይሰሙ› (2:5) ከእግዚአብሔር ትክክለኛውን መልእክት በመቀበል፤ ቃሉን በማጥናት (በመብላት) መልእክቱን ማድረስ ነው። የመልእክቱ ምንጭ ሳኪው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ‹የመጽሐፍ ጥቅልል› መብላት ቃሉን በቃል ከማወቅ በተጨማሪ መልእክቱን ልብ ማለት፤ ማገናዘብ፤ ማስተዋል ነው። የሚሄድ መልእክተኛ ‹ቃሱን የበላ› መሆን አለበት።

# ምዕራፍ 27:-
# ትንቢተ ዳንኤል

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ ዳንኤል ነው (12:4፤ ማቴ 24:15፤ ማር 13:14)::

**የተጻፈበት ጊዜ:-** በ537 ዓ.ዓ.:: መጽሐፉ ከ605-536 ዓ.ዓ. ያለውን ጊዜ ይሸፍናል። መጽሐፉ የተጻፈው በአረማይስጥና በዕብራይስጥ ነው። በዕብራይስጥ የተጻፈው 1-2:3 እና 8-12 ሲሆን በአረማይስጥ የተጻፈው 2:4-7 ያለው ነው::

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በጸሐፊው በዳንኤል ነው::

**ዋና ሰዎች:-** ዳንኤል፤ አናንያ (ሲድራቅ)፤ ሚሳኤል (ሚሳቅ)፤ አዛርያ (አብድናጎ)፤ ናቡከደነፆር፤ ብልጣሶር፤ ዳሪዮስ፤ ቂሮስ::

**ዋና ሀሳብ:-** እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ጌታ፤ የነገሥታት ንጉሥ መሆኑን ማሳየትና ለእስራኤልም በቅርብና በሩቅ ዘመን ያለውን ዓላማ መግለጽ::

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ:-** ‹ፍቺ (ሕልምን መፍታት) 30 ጊዜ፤

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**
- ‹ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ፤ እንዳይረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ ለመነ› (1:8)::
- ‹ዳንኤልም ተናገረ እንዲህም አለ። ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፤ ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል፤ ነገሥታትን ያፈልሳል፥ ነገሥታትንም ያስነሣል፤ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል። የጠለቀውንና የተሠወረውን ይገልጣል፤ በጨለማ ያለውን ያውቃል፥ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው› (2:20-22)::
- ‹ልዑሉም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሠለጥን፥ ለሚወድደውም እንዲሰጠው እስክታውቅ ድረስ ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ፥ መኖሪያህም ከምድር አራዊት ጋር ይሆናል፥ እንደ በሬም ሣር ትበላ ዘንድ ትገደዳለህ፥ በሰማይም ጠል ትረሰርሳለህ፥ ሰባት ዘመናትም ያልፉብሃል› (4:25-26)



- ‹አቤቱ ስማ፤ አቤቱ፤ ይቅር በል፤ አቤቱ፤ አድምጥና አድርግ፤ አምላኬ ሆይ፥ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና ስለ ራስህ አትዘግይ› (9:19)::
- ‹...ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም (11:33)::
- ‹አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ፤ አንተም ታርፋለህ፥ በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ› (12:13)::

**የመጽሐፉ እከፋፈል:-** መጽሐፉን በሦስት በመክፈል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

1. የዳንኤል ታሪክ (1)
2. ለአሕዛብ መንግሥታት እግዚአብሔር ያለው እቅድ (2-7)
3. ስለ እስራኤልና ስለወደፊቱ ዘመን የተነገረ ትንቢት (8-12)

1\. **የዳንኤል ታሪክ።** ብላቴናው ዳንኤል ከይሁዳ በምርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰደ፤ በንጉሡ መብልና መጠጥ ላለመርከስ ወሰነ፤ እግዚአብሔርም ሞገስ ሰጠው። ዳንኤል በጽድቅ ኑሮውና በጸሎቱ (ሕዝ 14፤14፤20)፤ በጥበቡ (ሕዝ 28:3) ይታወቃል:: በእግዚአብሔር የተወደደ ሰው ነበር (9:23፤ 10:11፤19):: ዳንኤል በመጀመሪያው የናቡከደነጾር ምርኮ በ605 ዓ.ዓ. ወደ ባቢሎን ከተወሰዱት ሰዎች መካከል ሲሆን በዚህ ጊዜ ዕድሜው ከ13-15 ዓመት እንደሚሆን ይገመታል (1:4):: በ70 የምርኮ ዓመታት በባቢሎን ኖሯል (1:1፤6 እና 10:1፤ እንዲሁም 9:2 እና ኤር 25:11-12፤ 29:10):: ዳንኤል ከ590-530 ዓ.ዓ. በነገሥታቱ በናቡከደነፆር (ምዕ 1-4)፤ ብልጣሶር (ምዕ 5፤ 7ና 8)፤ ዳሪዮስ (ምዕ 6ና 9) እና ቂሮስ (ምዕ 10-12) ዘመን ከፍተኛ የመንግሥት ሠራተኛ ነበር።

2\. **ለአሕዛብ መንግሥታት እግዚአብሔር ያለው እቅድ።** ከምዕ 2 እስከ 7 ያለው ክፍል የተጻፈው በአረማይስጥ ቋንቋ ነበር። በምዕ 2ና በምዕ 7 ወደፊት ስለሚመጡት አራት መንግሥታት ዳንኤል ያየው ራእይ ይገኛል። በእግዚአብሔር በማመናቸውና ለጣዖት አንሰግድም በማለታቸው ምክንያት ሲድራቅ፤ ሚሳቅና አብድናጎ በሚነድ እሳት ውስጥ ተጣሉ (3)፤ ዳንኤልም በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ተጣለ (6):: ዳንኤል ወደ አንበሳ ጉድጓድ የተጣለው ከ538-536 ዓ.ዓ ባለው ጊዜ ዕድሜው ከ80 ዓመት በላይ ከሆነ በኋላ እንደነበረ ይለላል። ናቡከደነፆር በትዕቢቱ ምክንያት በእግዚአብሔር ቅጣት እንደ እንስሳ ሆኖ ሣር

# ክፍል 4.2
# ደቂቅ ነቢያት።

ደቂቅ ነቢያት ተብለው የሚታወቁት ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ የነበሩት ነቢያት ‹አሥራ ሁለቱ› በመባልም ይጠራሉ።

ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ደቂቅ ነቢያት ያገለገሉበትን ዘመን በተመለከተ ከምርኮ በፊት፤ በምርኮ ዘመንና ከምርኮ በኋላ በማለት በሦስት እንደሚመደቡ ተመልክተናል። ከምርኮ በፊት ያገለገሉት ሆሴዕ፤ አሞጽ፤ ሚክያስ፤ ኢዩኤል፤ ዮናስ፤ ናሆም፤ ዕንባቆምና ሶፎንያስ ሲሆኑ በምርኮ ጊዜ አብድዩ፤ ከምርኮ በኋላ ደግሞ ሐጌ፤ ዘካርያስና ሚልክያስ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ሦስቱ ማለትም ሆሴዕ፤ አሞጽና ዮናስ የሰሜን እስራኤል (ሰማርያ) ነቢያት ናቸው። በተለይ ዮናስ ከእስራኤል ውጭ ወደ ነነዌ (አሦር) ተልኮ የሰበከ ነቢይ ነው።

የደቂቅ ነቢያት የመልእክት ይዘት እንደ ታላላቅ ነቢያት ሁሉ ስለ ኃጢአት መገሰጽ፤ ለንስሐ መጥራት፤ ስለ ፍርድ ማስጠንቀቅና የእግዚአብሔርን ምሕረት ማወጅ ነበር።

የደቂቅ ነቢያትን መጻሕፍት ዳሰሳ በሚከተሰው ቅደም ተከተል እንመለከታለን።

1. ሆሴዕ፦ የተከፈቱ የእግዚአብሔር የፍቅር እጆች፤
2. አሞጽ፦ እግዚአብሔርን መፈለግ፤
3. ሚክያስ፦ እግዚአብሔር ይመጣል!
4. ኢዩኤል፦ የጌታ ቀን ቀርቦአል፤
5. አብድዩ፦ ‹የሚረግሙህን ረግማለሁ›፤
6. ዮናስ፦ የእግዚአብሔር ፍቅር፤ ርኅራኄና ምሕረት፤
7. ናሆም፦ እግዚአብሔር መልካም ነው፤
8. ዕንባቆም፦ እስከ መቼ?
9. ሶፎንያስ፦ ወዮ ለእናንተ!
10. ሐጌ፦ የመሥራት ጊዜ ነውና ተነሥታችሁ ሥሩ፤
11. ዘካርያስ፦ በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፤
12. ሚልክያስ፦ እግዚአብሔር አይለወጥም።



# ምዕራፍ 28፡-
# ትንቢተ ሆሴዕ

**ጸሐፊው፦** የብኤሪ ልጅ ሆሴዕ (1፡1)፤ ሆሴዕ የጎሜር ባል ነው (1፡3)።

**የተጻፈበት ጊዜ፦** 710 ዓ.ዓ። የሆሴዕ አገልግሎት በይሁዳ 4 ነገሥታት በዖዝያን፤ ኢዮአታም፤ አካዝና ሕዝቅያስ ዘመን እና በእስራኤል አንድ ንጉሥ ኢዮርብዓም ዘመን ነበረ (1፡3)። ሆሴዕ በሰማርያ በሚያገለግልበት ዘመን ኢሳይያስና ሚኪያስ የይሁዳ ነቢያት ነበሩ።

**የመጽሐፉ ስያሜ፦** በጸሐፊው በነቢዩ ሆሴዕ።

**ዋና ሰዎች፦** ሆሴዕ

**ዋና ሀሳብ፦** የእግዚአብሔር ፍቅር። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያሰውን ቃል ኪዳንና ታጋሽ ፍቅሩን ያሳያል። ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ ቃል ኪዳን ያልጠበቅችውን እስራኤልን ወደ ራሱ ይጠራል።

**ተደጋጋሚ ቃል፦** ጋለሞታ (ግልሙትና) 19 ጊዜ፤ ‹ኤፍሬም› 37 ጊዜ (የሰሜኑ እስራኤል ሌላ መጠሪያ)።

**ቁልፍ ጥቅሶች፦**

- ‹ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ አጠላሃለሁ፤ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ። እንደ ብዛታቸው መጠን ኃጢአት ሠሩብኝ፤ እኔም ክብራቸውን ወደ ነውር እለውጣለሁ› (4፡6-7)።
- ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ እርሱ ሰብሮናልና፤ እርሱም ይፈውሰናል፤ እርሱ መትቶናል፤ እርሱም ይጠግነናል (6፡1)።
- ‹ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፤ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወድዳለሁና› (6፡6)።

- እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና፤ በመካከልህም ቅዱሱ ነኝና የቁጣዬን መቅሠፍት አላደርግም፤ ...› (11፡9)።
- ‹የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው፤ ጻድቃንም ይሄዱበታል፤ ተላላፊዎች ግን ይወድቁበታል› (14፡9)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** መጽሐፉን በሁለት በመክፈል እንመለከተዋለን።

1. የሆሴዕ ጋብቻ (1-3)
2. በእስራኤል ላይ ሊመጣ ያለው ፍርድና እንዲመለሱ የተደረገ ጥሪ (4-14)

**1. የሆሴዕ ጋብቻ።** እስራኤል ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግልሙትና በማድረጓ ሆሴዕ ጋለሞታ እንዲያገባ በእግዚአብሔር ታዘዘ። ሆሴዕ ሦስቱን ልጆቹን በዚያን ዘመን እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያለውን ሀሳብ በሚገልጽ ስያሜ፡- ኢዝራኤል (ማለት እግዚአብሔር ይበትናል)፤ ሎሩሃማ (አልምርም)፤ ሎዓሚ (ሕዝቤ አይደላችሁም) (1፡6-9) ብሎ እንዲጠራቸው እግዚአብሔር አዘዘው። ሚስቱ ሆሴዕን ትታ ወደቀደመ ኑሮዋ ተመለሰች። ታማኝ ያለሆነች ሚስትና ይቅር የሚል ባልን ያሳያል።

**2. በእስራኤል ላይ ሊመጣ ያለው ፍርድና እንዲመለሱ የተደረገ ጥሪ።** የእስራኤል ኃጢአት በምዕ 4-5 ተገልጾአል። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን እውቀት ጥለዋል። እውቀት ከማጣትም የተነሣ ጠፍተዋል። የእግዚአብሔርን እውቀት በጣዖት አምልኮ ተክተዋል። መሠዊያ አበዙ፤ ሐውልቶች ሠሩ፤ ስለዚህም ‹ልባቸው ተከፈለ› (10፡1)። ድብልቅ ሕይወት ነበራቸው። እግዚአብሔርንና ጣዖትን ያመልኩ ነበር። ከዚህም የተነሣ ጥፋት ሆነ። ሆሴዕ ሚስቱን እንዲፈልግ ታዘዘ። እንዲሁ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይፈልጋል፤ በንስሐ እንዲመለሱም ይጠራቸዋል፤ ተስፋም ይሰጣቸዋል (ምዕ 14)። ታማኝ ያልሆነ ሕዝብና ተመለሱ የሚል ይቅር ባይ አምላክን እንመለከታለን።

**ክርስቶስ በትንቢተ ሆሴዕ መጽሐፍ።**
ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፡- ‹ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት› (11፡1 እና ማቴ 2፡15)።

ኢየሱስ በትንሣኤው የሞትን መውጊያ የሚሰብር (13፡14 እና 1ቆሮ 15፡55)።



**ዋና ትምህርት፡-**
**የእግዚአብሔር አስደናቂ ፍቅር።** እስራኤል ለእግዚአብሔር ካህን እንድትሆን ተጠርታ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔርን እውቀት ጠላች። እውቀትን መጥላት ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ጽድቅ አለመፈለግ ነው። የእግዚአብሔርን እውቀት መፈለግ ከአመጽ መንገድ በንስሐ መመለስን ይጨምራል (2፡20፤ 4፡1፤6፡5፡15፤ 6፡1-3፤6፤ 10፡12፤ 13፡4፤14)። ሆሴዕ ያልታመነችና ከእርሱ ተለይታ የሄደችውን ሚስቱን ወደ ገባያ ሄዶ እንደገና ገዝቶ የራሱ እንዳደረጋት እንዲሁ በኃጢአት ያሉ ‹ጊዜ ሳያልፍባቸው› በንስሐ ቢመለሱ እግዚአብሔር እንደገና የራሱ ያደርጋቸዋል። ይህም የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። **እግዚአብሔር ኃጢአተኛን ሰው ይወዳል ኃጢአትን ይጠላል።**

**የመዝራትና የማጨድ ሕግ።** በእስራኤላውያን ጓዳና ኑሮ ይሆን የነበረውን ሲናገር ‹ነፋስን ዘርተዋል፤ ዐውሎ ነፋስንም ያጭዳሉ፤ አገዳ የለውም፤ ከፍሬውም ዱቄት አይገኝም፤ ቢገኝም እንግዶች ይበሉታል› (8፡7) ይላል። እንዲሁም ‹ለእናንተ በጽድቅ ዝሩ፤ እንደ ምሕረቱም መጠን እጨዱ፤ ጥጋታችሁንም አረሱ። ክፋትን አርሳችኋል፤ ኃጢአትንም አጭዳችኋል፤ የሐሰትንም ፍሬ በልታችኋል ...› (10፡12-13)። በተፈጥሮው ዓለም ሰው የዘራውን ዓይነት ምርት እንደሚያገኝ ሁሉ በመንፈሳዊውም ዓለም ‹ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል› (ገላ 6፡7-8)።

# ምዕራፍ 29:-
# ትንቢተ አሞጽ

**ጸሐፊው:-** ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ የነበረ የቴቁሔው ነቢዩ አሞጽ (1፡1፤ 7፡14-15)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 755 ዓ.ዓ.። (በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን፤ በእስራኤል ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን፤ የምድር መናወጥ ከሆነበቱ ከሁለት ዓመት በፊት 1፡1)።

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በጸሐፊው ነቢዩ አሞጽ። ከደበቡ (ይሁዳ) ወደ ሰሜኑ (ሰማርያ) የተላከ ነቢይ።

**ዋና ሰዎች:-** አሞጽ

**ዋና ሀሳብ:-** የንስሐ ጥሪ ነው። ሕዝቡ ከክፉ መንገዳቸውና ከጣዖት አምልኮ እንዲመለሱ ጥሪ ያደርጋል። አግዚአብሔር በአምቢተኞች ላይ ሊፈርድ ይመጣል። ቅዱስ አግዚአብሔር ክፋትን ይጠላል፤ በአመጽ የሚሄደውም ሳይቀጣ አይቀርም።

**ተደጋጋሚ ቃል/ሐረግ:-** ‹ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት› 7 ጊዜ፤ ‹ጽድቅ› 3 ጊዜ፤ ‹ቅሬታ› 3 ጊዜ፤ ‹ይህን ቃል ስሙ› 3 ጊዜ።

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- እስራኤልም ሆይ፤ እንደዚህ ስለማደርግብህ አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ› (4፡12)።
- ‹አግዚአብሔርም ለእስራኤል ቤት እንዲህ ይላልና። እኔን ፈልጉ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ› (5፡4)።
- ‹እነሆ፤ በምድር ላይ ራብን የምሰድድበት ዘመን ይመጣል፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም› (8፡11)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** በ3 በመክፈል እንመለከታለን።

1. በአሕዛብ አገሮች ላይ የሚመጣ ፍርድ (1-2)



2. የእስራኤል ኃጢአትና የሚመጣው ፍርድ (3-9፡10)
3. የእስራኤል መመለስ ተስፋ (9፡11-15)

**1. በአሕዛብ አገሮች ላይ የሚመጣ ፍርድ::** አግዚአብሔር በየትኛውም አገር ቢሆን የሚኖረውን የፍርድ መጓደል፤ ግፍና ኃጢአት አይወድም። በድሆች ላይ ስለሚፈጸመው ግፍ ይበቀላል (2፡7)። በአገሮች ላይም ይፈርዳል። እስራኤል በኃጢአት ውስጥ ነበረች (2፡6-8)፤ ነቢያት ትንቢት እንዳይናገሩ ይታዘዙ ነበር (2፡12)።

**2. የእስራኤል ኃጢአትና የሚመጣው ፍርድ::** ድሆች የበለጠ እየደኸዩ፤ ሀብታሞቹ በግፍ የበለጠ እየከበሩ ይሄዱ ነበር። በኃጢአት ድርጊታቸው የአግዚአብሔርን ቅዱስ ስም አለማክበር (2፡7)፤ ድሆችን መጨቆን (2፡7)፤ ጣዖትን ማምለክ (2፡8) ጎልተው ይታዩ ነበር። በእስራኤል ሃይማኖተኛነቱ አለ እውነተኛነትና ፍትህ ግን ተጓድሏል። ስለ ኃጢአት ለመበቀል አግዚአብሔር በሚያስፈራና በሚያገሳ አንበሳ ምሳሌ ተነግሮአል (3፡4)። የራሳቸውን ምኞት የሚፈልጉ ሀብታም የሰማርያ ሴቶች ‹በባሳን ላሞች› (4፡1) ተመስለዋል። ለድሆች ግዴለሾች ናቸው። በቤቴልና በጌልገላ ጣዖት አምልኮ አለ፤ ኃጢአት በዝቷል (4፡4፤ 5፡5)። ‹እስራኤልም ሆይ፤ እንደዚህ ስለማደርግብህ አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ› (4፡12) ተብሏል። ስለዚህ ‹ፍርድ እንደ ውኃ፤ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ› (5፡24)። ያለዚያ ቅጣት ሊመጣ ነው። ያውም ከቅጣት ሁሉ የሚከፋው ቅጣት መንፈሳዊ የሆነ የቃሉ ራብ ነው (8፡11-12)። አግዚአብሔር ሀሳቡን ለሕዝቡ መናገር ሲያቆም የጨለማ ዘመን ይሆናል። ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ቅሬታ ማስቀረት ይችላል (አሞ 5፡15)።

**3. የእስራኤል መመለስ ተስፋ::** ከፍርድ በኋላ ለእስራኤል ተስፋ አላት (9፡11-15)። ይህ ተስፋ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚመጣውን መታደስ ሲገልጽ ‹በዚያ ቀን የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ፤ የተናደውንም ቅጥርዋን አጠግናለሁ፤ የፈረሰውንም አድሳለሁ፤ እንደ ቀደመውም ዘመን እሠራታለሁ› (9፡11) ይላል።

**ክርስቶስ በትንቢተ አሞጽ መጽሐፍ።**
የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን የሚያነሣ ክርስቶስ (9:11-16) በእርሱ የሚገኘው ደህንነት አሕዛብን ሁሉ የሚጨምር ነው (ሐዋ 15:16)።

**ዋና ትምህርት፡-**
**የእግዚአብሔር ቸርነት በመከራ ዘመን ቅሬታን መጠበቁ።** እግዚአብሔር የርስቱን ቅሬታ ያስቀራል (ሚክ 7:18፤ ሕዝ 6:8)። እግዚአብሔር ከኖኅ ዘመን ጀምሮ በመስኮታዊ አሠራሩ በመከራ፤ በቅጣትና በምርኮም ዘመን ጥቂቶችን ያስቀራል፤ ይጠብቃል። በኤልያስ ዘመን ለበዓል ያልተንበረከኩ 7000 ሰዎችን ለራሱ አስቀርቷል። ከባቢሎን ምርኮ በኋላም እግዚአብሔር የጠበቃቸው 50000 ያህል ‹ቅሬታዎች› ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ቅሬታ መኖሩ ከእግዚአብሔር ሞገስ ማግኘትንና በሙሉ አለመጥፋትን ያሳያል (ዕዝ 9:8፤14)። ይህም ኢሳይያስ ‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ፤ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር› (ኢሳ 1:9) እንዳለው ነው።



## ምዕራፍ 30፡-
# ትንቢተ ሚክያስ

**ጸሐፊው፡-** ሞሬታዊው ነቢዩ ሚክያስ (1:1፤ 3:12፤ ኤር 26:18)።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 760 ዓ.ዓ። በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታምና በአካዝ በሕዝቅያስም ዘመን የነበረ ነቢይ (1:1)።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በጸሐፊው ነቢዩ ሚክያስ።

**ዋና ሰዎች፡-** ሚክያስ

**ዋና ሀሳብ፡-** በሰማርያና በይሁዳ ላይ የሚመጣው ፍርድ በቅርብ መሆኑን መግለጽ፤ ስለ መታደስም ተስፋ መስጠት።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ‹ስሙ› 9 ጊዜ፤ (እግዚአብሔርን እንዲሰሙ/እንዲያደምጡ ምክር)።
**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹ሰው ሆይ፤ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፤ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፤ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?› (6:8)።
- ‹እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እመለከታለሁ፤ የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ፤ አምላኬም ይሰማኛል። ጠላቴ ሆይ፤ ብወድቅ እነሣለሁና፤ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ› (7:7-8)።
- ‹የእግዚአብሔር ድምፅ ከተማይቱን ይጠራታል፤ ስምህን መፍራት ጥበብ ነው፤ የመቅሠፍትን በትር፤ እርሱንም ያዘጋጀ ማን እንደ ሆነ ስሙ› (8:9)።
- ‹...በደልን ይቅር የሚል፤ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? ምሕረትን ይወድዳልና ቍጣውን ለዘላለም አይጠብቅም። ተመልሶ ይምረናል፤ ክፋታችንንም ይጠቀጥቃል፥ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል› (7:18-19)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** ከዋናው ሀሳብ አንጻር በሦስት በመክፍል መመልከት ይቻላል።

1. አግዚአብሔር በፍርድ ይመጣል 1-2
2. እግዚአብሔር በሰላም ይመጣል ማዳን 3-5
3. አግዚአብሔር በምሕረት ይመጣል የበረከት ተስፋ 6-7

**1. እግዚአብሔር በፍርድ ይመጣል።** አግዚአብሔር ከስፍራው ወጥቶ ስለ ኃጢአት በሰማርያ ላይ ለመፍረድ ይመጣል (1፡3-5)። ሀብታሞች የድሆችን ርስት ይነጥቁ ነበር (2፡2)። ሕዝቡ በኃጢአት ይኖሩ ነበር፤ ነቢያትን ሳይቀር ትንቢት አትናገሩ ይሏቸው ነበር (2፡1-6)። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊመሰክርባቸው (1፡2) ይወርዳል።

**2. እግዚአብሔር በሰላም ይመጣል።** በዘመኑ የነበሩት መሪዎችና ነቢያት ሕዝብን የሚያስቱ ነበሩ (3፡5-)። በቅድስት ከተማ በመኖራቸውና ቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሌም በመኖሩ ብቻ ከቅጣት የሚያመልጡ ይመስላቸው ነበር። ‹አለቆችዋ በጉቦ ይፈርዳሉ፤ ካህናቶችዋም በዋጋ ያስተምራሉ፤ ነቢያቶችዋም በገንዘብ ያምዋርታሉ፤ ከዚህም ጋር እግዚአብሔር በመካከላችን አይደለምን? ክፉ ነገር ምንም አይመጣብንም እያሉ በእግዚአብሔር ይታመናሉ› (3፡11)። ስእነርሱ በቅጣት ይመጣል። ሆኖም በቤተልሔም የሚወለደው የእስራኤል ገዥ (ክርስቶስ) እረፍትን ያመጣል (5፡2-5)።

**3. እግዚአብሔር በምሕረት ይመጣል።** ‹እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ክርክር አለውና፤ ከእስራኤልም ጋር ይፋረዳል› (6፡1-2)። አግዚአብሔር የሚፈልገውን ነግሯቸዋል ይህም ወደ እርሱ በመመለስ ፍርድን ማድረግ፤ ምሕረትን መውደድና ከእርሱ ጋር በትሕትና መሄድን ነው (6፡8)። ለድሆች ማዘንና ፍትሕን መጠበቅ የእውነተኛ አምልኮ ክፍል ነው። እግዚአብሔር የሚለምኑትን ሰዎች ጩኸት ይሰማል፤ ከጨለማ አውጥቶ ወደ ብርሃን ያመጣል (7፡7-9)።

**ክርስቶስ በትንቢተ ሚክያስ መጽሐፍ።**
ክርስቶስ በቤተልሔም ኤፍራታ የሚወጣው ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ ገዥ ነው (5፡2 እና ማቴ 2፡5-6)።



**ዋና ትምህርት፡-**
የእግዚአብሔር ‹እምሳያ የለሽነት›። ነቢዩ በአድናቆት አግዚአብሔርን ‹እንዳንተ ያለ ማን ነው?› (7፡18) ይላል። አግዚአብሔር ለኃጢአት ብድራትን የሚሰጥ፤ ሕዝቡን ተመልሶ ይቅር የሚል፤ ተስፋን የሚያድስ፤ ቅሬታዎችን የማይረሳ ነው። እርሱ ከሰው ጋር ሕብረት ማድረግ ይወዳል። ስለሆነም ይህ አምሳያ የለሽ (ልዩ) አምላክ ከሰው ‹ፍርድ፤ ምሕረት፤ ትሕትናን› ይወዳል (6፡8)[71]። የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት አስደናቂ መስኮታዊ ባሕርይ ነው።

**እግዚአብሔር የሚወደውን ‹ዋና ነገር› ማወቅና ማድረግ።**
አግዚአብሔር ለእርሱ ከሚቀርብለት መሥዋዕት ይልቅ እርሱን መታዘዝን (1ሳሙ 15፡22-23)፤ ፈቃዱን ማድረግን (መዝ 40፡6-8)፤ ከትዕቢት የራቀ የተሰበረ መንፈስን (መዝ 51፡16-19)፤ ቃሉን መስማትና በመንገዱ መሄድን (ኤር 7፡21-23) ይወዳል። እግዚአብሔር ከጽድቅ ሕይወት ያልፈለቀ ውጫዊ ሃይማኖተኛነትንና አስመሳይነትን ይጠላል። መሐሪ አግዚአብሔር ይቅር ባይነትን፤ ከእርሱ ጋር በትሕትና መራመድን ይወዳል (ሚክ 6፡6-8፤ ማቴ 9፡13)። ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር ‹እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፤ ከአዝሙድና ከእንስላል ከከሙንም አሥራት ስለምታወጡ፤ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም፤ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ፤ ወዮላችሁ፤ ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር› (ማቴ 23፡23) አለ። ከሁሉ የገቢ ዓይነት አሥራት መክፈል ጥሩ ነው፤ ሆኖም እግዚአብሔር የሚፈልገው ‹ዋና ነገር› ከአሥራት ወይም ከመሥዋዕት በላይ የሆነ የተለወጠ ሕይወትን ነው። ይህን ተረድቶ ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያስገኛል።

[71] "There are 613 commandments in the Pentateuch, they were reduced to 11 in Psalm 15, reduced further to three here (Micah 6:8), then to one in Matthew 22:35-40. God wants our hearts; He desires relationship with us." http://truthsaves.org/outlines/oldtestament.shtml)

## ምዕራፍ 31፡-

# ትንቢተ ኢዩኤል

**ጸሐፊው፡-** የባቱኤል ልጅ ነቢዩ ኢዩኤል (1፡1)

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 835 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በጸሐፊው ነቢዩ ኢዩኤል።

**ዋና ሰዎች፡-** ኢዩኤል

**ዋና ሀሳብ፡-** አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን በቅርብ ስለሆነ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ መምከር። መጽሐፉ 28 ጊዜ ያህል በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶአል።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ‹የእግዚአብሔር ቀን› 6 ጊዜ።

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹አሁንስ፤ ይላል እግዚአብሔር፤ በፍጹም ልባችሁ፤ በጾምም፤ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፤ ከቁጣው የዘገየ፤ ምሕረቱም የበዛ፤ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ› (2፡12-13)።
- ‹ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፤ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፤› (2፡28-29)።
- ‹የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ፥ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣል። እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፥ የምስራች የሚሰበካላቸው ይገኛሉ› (2፡31-32)።



**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** ከዋናው ሀሳብ አንጻር በሁለት መክፈል ይቻላል።

1. በቅርብ ያለው የእግዚአብሔር ቀን (1፡1-2፡17)
2. የወደፊቱ የእግዚአብሔር ቀን (2፡18-3፡21)

**1. በቅርብ ያለው የእግዚአብሔር ቀን።** በይሁዳ ላይ የእግዚአብሔር ቀን (ቅጣት) እንደ አንበጣ ወረራ ሳይታሰብ ይመጣባታል። ለሰው ሁሉ የሀዘንና የለቅሶ ጊዜ ይሆናል። ስለዚህ በንስሐ ተመለሱ።

**2. የወደፊቱ የእግዚአብሔር ቀን።** ከይሁዳ መወረር በኋላ በሚመጣው የእግዚአብሔር ቀን መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ ተስፋ አለ (2፡29)። ይህም በባለ ሃምሳ ቀን እንደተፈጸመ ጴጥሮስ ተናገረ (ሐዋ 2፡17-21)። ወደፊት በሚመጣው የእግዚአብሔር ቀን የመባረክ ተስፋ አለ። ‹የስደድሁባችሁ ታላቁ ሠራዊቴ አንበጣና ደጎብያ ኩብኩባና ተምች የበሉባቸውን ዓመታት እመልስላችኋለሁ› (2፡25) ይላል። የወደፊቱ የእግዚአብሔር ቀን የታሪክ ማብቂያ ይሆናል።

**ክርስቶስ በትንቢተ ኢዩኤል መጽሐፍ።**
ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን የሚያፈስ ጌታ ነው (2፡28 እና ዮሐ 16፡7-15፤ ሐዋ 2፡16-21፤33)።

**ዋና ትምህርት፡-**
**እግዚአብሔር በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሱን ያፈሳል።** ከባቢሎን ምርኮ በኋላ እስራኤላውን የበረከት ጊዜ ይኖራቸዋል። ከዚያም (በሩቁ ጊዜ/ በአዲስ ኪዳን) እግዚአብሔር ልዩ የሆነን ስጦታ ከሰማይ ይልካል ይህም መንፈሱን ማፍሰስ ነው (2፡28-29)። በአዲስ ኪዳን በባለ ሀምሳ ቀን ይህ የመጨረሻው ዘመን ተስፋ መፈጸሙን ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢዩ 2፡28-29ን በመጥቀስ ተናገረ (ሐዋ 2፡17-21)። ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ ጋር እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያስተውቅባቸው መንገዶች ትንቢት መናገር፤ ሕልምን ማለም፤ ራእይ ማየት በባለሃምሳ ቀንና ከዚያም በኋላ እንደሆነው (ሐዋ 2፡2-4፤33፤39፤ ሐዋ 9፡10፤ 10፡44-47፤ 11፡15-18፡ 15፡7-8፤ 16፡9፤ 21፡9) አብረው ይገለጣሉ። ሕልምና ራእይ ነቢያት ከእግዚአብሔር መልእክት የሚቀበሉባቸው መንገዶች ነበሩ (ዘኁ 12፡6)።

መንፈስ ቅዱስን ‹ማፍሰስ› እግዚአብሔር የሚያደርገው መለኮታዊ ሥራ ነው። የሚፈሰውም በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ነው። በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ የወረደው በጥቂት ነገሥታት፣ መሳፍንትና ሽማግሌዎች ላይ ብቻ ነበር (ዘኍ 11:29)። የተስፋው ቃል ግን ለሰው ሁሉ (ለአይሁድና ለአሕዛብ) ነው። በጾታ ወይም በዕድሜ የተገደበ አይደለም፤ ለወንዶችና ለሴቶች ነው። ለወላጆች ብቻ ሳይሆን ለልጆችም ነው፤ ለሽማግሌዎች ብቻ አይደለም ለጎበዞችም ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ‹የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና› እንዳለው (ሐዋ 2:39) የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በአንድ ዘመን (ወቅት) ያላበቃ ነው። እንዲሁም በሽማግሌዎች ወይም ጎበዞች ሳያበቃ ለልጆችም በየዕድሜው ላሉት ሁሉ መሆኑ የስጦታውን ቀጣይነት ያመለክታል።



## ምዕራፍ 32:-

# ትንቢተ አብድዩ

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ አብድዩ (1:1)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 841 ወይም 586 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በነቢዩ አብድዩ። 21 ቁጥሮች ብቻ ያለው ከብሉይ ኪዳን አጭሩ መጽሐፍ ነው።

**ዋና ሰዎች:-** አብድዩ

**ዋና ሀሳብ:-** ኤዶምያስ ስለ ትዕቢቷ ትቀጣለች። ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል።

**ተደጋጋሚ ቃል:-** ኤሳው 7 ጊዜ፤ ኤዶምያስ 2 ጊዜ፤

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹የእግዚአብሔር ቀን በአሕዛብ ሁሉ ላይ ቀርቦአልና፤ አንተ እንዳደረግኸው እንዲሁ ይደረግብሃል፤ ፍዳህም በራስህ ላይ ይመለሳል› (1:15)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** የመጽሐፉ ዋና ሀሳብ በኤዶምያስ ላይ የሚመጣው ፍርድ ነው። ኤዶምያስ ታብዮ ነበር (1:3)። ይሁዳ በተቸገረ ጊዜ ኤዶምያስ ፍቅር ባለማሳየቱ፤ ከሀብቱም በመውሰዱ የማይገባ ነገር አድርጓል (1:12-14)። ኤዶም ከይሁዳ ደቡባዊ ምሥራቅ የምትገኝ አገር ነበረች። ኤዶማውያን የኤሳው ዘሮች ነበሩ (ዘፍ 25:19-34)። እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲጓዙም በእነርሱ ምድር እንዳያልፉ ከልክለዋቸው ነበር (ዘኍ 20:14-21)። ለእስራኤል ወንድማዊ ፍቅር አላሳዩም። የኤዶም ልጆች ኢየሩሳሌምን ‹እስከ መሠረትዋ ድረስ አፍርሱ፤ አፍርሱ› (መዝ 137:7) ብለው ባቢሎናውያንን አበረታተው ነበር። ስለዚህ ፍርድ ይጠብቃቸዋል። ‹ከዔሳውም ቤት ቅሬታ የለውም› (1:18) ይሁዳን ግን እግዚአብሔር ያስባል።

**ክርስቶስ በትንቢተ አብድዩ መጽሐፍ፡፡**
‹መንግሥቱም ለእግዚአብሔር ይሆናል› (1፡21) የሚለው ፍጹም አምላክ የሆነው የክርስቶስን መንግሥት ያመለክታል (ሉቃ 1፡32-33፤ 22፡0፤ ራዕ 11፡15)፡፡

**ዋና ትምህርት፡-**
**እግዚአብሔር የሰውን ሁሉ ‹ሂሳብ› በጊዜው ያወራርዳል፡፡** በአንድ ወቅት ‹ከፍ ከፍ› (1፡3) እንዳለ የመለሰውን እግዚአብሔር ‹አወርድሃለሁ› (1፡4) ይላል፡፡ ኤዶምያስ የፍርድ ቀን የሚመጣ አልመሰለውም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ጊዜን ጠብቆ ‹የኃጢአት ጽዋ ሲሞላ› ዋጋን ይከፍላል፡፡ ለሌላው እንዳደረግኸው ይደረግብሃል (ኤር 50፡29፤ ዕን 2፡8፤ ማቴ 26፡52፤ ሉቃ 6፡38፤ ያዕ 2፡13፤ ራዕ 13፡10)፡፡



## ምዕራፍ 33፡-
# ትንቢተ ዮናስ

**ጸሐፊው፡-** የአማቴ ልጅ ነቢዩ ዮናስ (1፡1)፡፡

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 760 ዓ.ዓ፡፡.

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በነቢዩ ዮናስ፡፡

**ዋና ሰዎች፡-** ዮናስ፡፡

**ዋና ሀሳብ፡-** እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ እንደሚወድ ማሳየት፡፡ የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር የአሕዛብም አምላክ ነው፡፡ ለዕብራውያን የሚራራ ለነነዌ ሰዎችም ይራራል፡፡ እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ እንዲሁ ይወዳል (ዮሐ 3፡16)፡፡ ዮናስ ወደ ነነዌ የተላከ የሰሜን እስራኤል ነቢይም ነበር (2ነገ 14፡25-27)፡፡

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ‹እግዚአብሔር ...አዘጋጀ/ አሰናዳ› 4 ጊዜ፡፡

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹እኔ ግን በምስጋና ቃል አሠዋልሃለሁ፤ የተሳልሁትንም እከፍላለሁ፡፡ ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው› (2፡10)፡፡
- ‹ወደ እግዚአብሔርም ጸለየና፤ አቤቱ፤ እለምንሃለሁ፤ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህ አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፤ ታጋሽም ምሕረትህም የበዛ፤ ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበርና ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኰብለል ፈጥኜ ነበር (4፡2)፡፡

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** ከዮናስ ዋና ድርጊቶች አንጻር በአራት መክፈል ይቻላል፡፡

1. የዮናስ መኰብለል (ምዕ 1)
2. የዮናስ ጸሎት (2)
3. የዮናስ ስብከት (3)
4. ዮናስ የተማረው (4)

1. **የዮናስ መኮብለል፡፡** ዮናስ የተላከው በጨካኝነቱ ወደሚታወቀውና እስራኤልም ትፈራው ወደነበረው ወደ አሦር ሕዝብ ነበር፡፡ በኋላም በ722 ዓ.ዓ. አሦር እስራኤልን ማርኳል፡፡ እግዚአብሔር ‹ወደ ነነዌ ሂድ› ብሎ ሲጠራው (1:2) ዮናስ ግን ከእርሱ ፊት ስመኮብለል በመርከብ ወደ ተርሴስ ሄደ (1:3-7)፡፡ በባሕር ላይ በተነሣው ታላቅ ማዕበል ምክንያት መርከበኞቹ ወደ ባሕር ጣሱት፡፡ በባሕር ውስጥም እግዚአብሔር ታላቅ ዓሣ አዘጋጀ፤ ዓሣውም ዮናስን ዋጠው፡፡

2. **የዮናስ ጸሎት፡፡** ዮናስ በትልቅ ዓሣ ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ዓሣው ዮናስን በምድር ላይ ተፋው፡፡

3. **የዮናስ ስብከት፡፡** እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ሲልከው ዮናስ ወደ ነነዌ ሄደ፡፡ በስብከቱም የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ ንስሐ ገቡ፤ እግዚአብሔርም ምሕረት አደረገላቸው፡፡

4. **ዮናስ የተማረው፡፡** እግዚአብሔር ለነነዌ ሰዎች ባደረገው ምሕረት ዮናስ ተቆጣ፡፡ የንስሐ መልእክት ቢሰብክም ለሚኖረው መልካም ውጤት የተዘጋጀ አልነበረም፡፡ ለመሞትም ፈለገ (4:3)፡፡ ዮናስ እግዚአብሔር ባበቀለለት ቅል መድረቅ ምክንያት ሲቆጣ እግዚአብሔር ደግሞ ታላቅ ባሕርይውን አስተማረው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ የሚያስብ ምሕረትን የተሞላ አምላክ ነው፡፡

**ክርስቶስ በትንቢተ ዮናስ መጽሐፍ፡፡**
ዮናስ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣ ሆድ ውስጥ መቆየቱ የክርስቶስን በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት መኖር ምሳሌ ነው (2:1 እና ማቴ 12:40፤ 16:4)፡፡

**ዋና ትምህርት፡-**
**የወንጌል አድማስ እስከ ምድር ዳርቻ ነው፡፡** እስራኤል የተጠራችው ለአሕዛብ ብርሃን እንድትሆን ነበር (ዘጸ 19:5-6)፡፡ የዮናስ ተልዕኮም ይህን እንዲፈጽም ነው፡፡ ነቢዩ ዮናስ ወደ ነነዌ ሳይሄድም የእግዚአብሔር ባሪያ ነበር (2ነገ 14:25)፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ባሪያዎቹን እንደ ፈቀደ ያስማራል፡፡ በእነርሱም ተጠቅሞ መንፈሳዊ ጉብኝት ሪቫይቫልና ተሐድሶ ያስነሣል፡፡ የስምሪት ቦታ ‹ምድብ›ና የመልእክቱ ዓይነት በላኪው በእግዚአብሔር ስለሚወሰን አገልጋይ የራሱ ምርጫ የሌለው ‹በጎ



ባሪያ› መሆን አለበት፡፡ እስራኤላዊው ዮናስ በጨካኝነቱ ወደሚታወቀውና የእስራኤል ‹ጠላት› ወደሆነው ወደ ነነዌ ሕዝብ ለመሄድ ፍርሃት እንደሚኖርበትም ይታሰባል፡፡ ሆኖም የእግዚአብሔርን የምሕረት ባሕርይ እያወቀ ምሕረቱ ለነነዌ ሰዎች እንዳይደርሳቸው መከላከል ከፍርሃት ያለፈ ‹ወገንተኝነት› ይሆናል፡፡ የወንጌል አገልጋይ ለሰው ሁሉ የሚራራ፤ በዘረኛነት አስታሳሰብ ያልታሰረ፤ ከኃጢአት በስተቀር የሚጠላው ሰው፤ ዘር ወይም አገር የሌለው መሆን ይገባዋል፡፡ የእግዚአብሔር ማዳን ለሰው ሁሉ ነው፡፡ ይህ ‹ድንበር የለሽ› አገልግሎት ነው፡፡

**እግዚአብሔር መሐሪ ነው፤ ፈቃዱም አይከለከልም፡፡** ታላቅ አምላክ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም ታላላቅ በሆኑ እንደ ነፋስ፤ ዓሣ አንባሪ እንደሚጠቀም ሁሉ በሰው እጅ እንደሚጣል ‹እጣ›፤ በበረሃ እንደምትበቅል ‹ቅል› ባሉም በታናናሽ ነገሮች ይጠቀማል፡፡ እግዚአብሔር በምድር፤ በባሕርና በነፋስ ሁሉ ላይ ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡ ከእግዚአብሔር ፊት የት ማምለጥ ይቻላል? (መዝ 139:7-10)፡፡ እዚህ ላይ የሚያስደንቀው የእግዚአብሔር አሠራር፡- በራሱ የግል ምክንያት ‹ሌላ› ሕዝብ ወይም ወገን ምሕረት እንዲያገኝ ያልፈለገውን ነቢይ ‹አባብሎና› ታድጎ የሀሳቡ አገልጋይ ማድረጉ ነው፡፡

**እግዚአብሔር ጸሎትን እንዳይሰማ የሚከለክለው ቦታ ሳይሆን ኃጢአት ነው፡፡** እግዚአብሔር በየትም አገርና ስፍራ፤ በየብስ ቢሆን በባሕር ላይ፤ በበረሃ ይሁን በዓሣ ሆድ ውስጥ ወደ እርሱ የሚደረግ ጸሎትንና ንስሐን ይቀበላል፡፡ ዮናስ በዓሣ ሆድ ውስጥ ሆኖ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማው፡፡

# ምዕራፍ 34:-
# ትንቢተ ናሆም

**ጸሐፊው:-** ኤልቆሻዊው ናሆም (1:1)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 663-612 ዓ.ዓ።

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** ከነቢዩ ናሆም።

**ዋና ሰዎች:-** ናሆም

**ዋና ሀሳብ:-** የእግዚአብሔር ታላቅነትና ፍርድ። የአመጸኛዋን ነነዌ ግፍና ኃጢአት እግዚአብሔር ይቀጣል።

**ቁልፍ ቃል:-** ነነዌ

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹እግዚአብሔር መልካም ነው፤ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው፤ በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል› (1:7)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** የመጽሐፉ ዋና ሀሳብ በነነዌ ላይ የሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ዮናስ በ760 ዓ.ዓ አካባቢ ወደ ነነዌ በመሄድ በሰበከ ጊዜ ሕዝቡ ንስሐ በመግባቱ ከቅጣት አመለጠ። ሆኖም ከ100 ዓመታት ያህል በኋላ ነነዌ በቀደመው ኃጢአት ቀጠለች። በክብር የሚራመድ እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ ንስሐ ያልተገባበትን ኃጢአት ሳይቀጣ አይቀርም። ስለሆነም ነነዌን ባድማ ያደርጋል (3:7)።

**ክርስቶስ በትንቢተ ናሆም መጽሐፍ፡፡**
የምሥራች ብሎ የሰላምን ወንጌል የሚሰብክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ናሆ 1:15 እና ሐዋ 10:36፤ ሮሜ 10:15፤ 2ጢሞ 2:19)። መልካሙ እረኛ ክርስቶስ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል (1:7 እና ዮሐ 10:27፤ 2ጢሞ 2:19)።



**ዋና ትምህርት:-**
**የእግዚአብሔር ባሕርይና ታላቅነቱ።** እግዚአብሔር ታጋሽ ነው፤ በእርሱ የሚታመኑ ከመከራ ያመልጣሉ፤ በንስሐ ባለመመለስ በእምቢተኛነት የሚቀጥሉትን ግን ይቀጣል። ይህም የእርሱን ጻድቅ ፈራጅነት ያሳያል።

- እግዚአብሔር ቀናተኛና ተበቃይ እምላክ ነው፤ (1:2)
- እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፤ ኃይሉም ታላቅ ነው (1:3)
- እግዚአብሔር በደለኛውን ንጹሕ ነህ አይልም (1:3)፤
- እግዚአብሔር ተፈጥሮን ይቆጣጠራል (ወጀብ፤ ዐውሎ ነፋስ፤ ደመና፤ ባሕር፤ ወንዞች፤ አበባ፤ ተራሮች፤ ኮረብቶች፤ **ምድርና ዓለም** (1:4-6))።
- እግዚአብሔር መልካም ነው (1:7)
- እግዚአብሔር በመከራ ቀን መሸሸጊያ ነው (1:7)፤
- እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል (1:7)።

# ምዕራፍ 35:-
# ትንቢተ ዕንባቆም

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ ዕንባቆም (1:1፤ 3:1)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 606-604 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** ከጸሐፊው ነቢዩ ዕንባቆም።

**ዋና ሰዎች:-** ዕንባቆም

**ዋና ሀሳብ:-** እግዚአብሔር የሚያደርገውን ያውቃል።

**ቁልፍ ቃል:-** ለምን? እምነት

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹...ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል› (2:4)።
- ‹ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፤ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፤ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፤ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ። ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ ነው፤ እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል› (3:17-19)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** መጽሐፉን በዕንባቆም ጥያቄዎችና ባገኘው መረዳት አንጻር በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

1. የዕንባቆም ጥያቄዎች/ የእምነት መፈተን (1)
2. የዕንባቆም መረዳት/ የእምነት ጸሎት (2-3)

1. ***የዕንባቆም ጥያቄዎች/ የእምነት መፈተን*** ። ይሁዳ በባቢሎን እንድትማረክ እግዚአብሔር ‹ለምን› ይፈቅዳል? (1:2-4) የሚለው የነቢዩ ትልቁ ጥያቄው ነበር። ስለዚህም ‹ጠያቂው ነቢይ› በመባልም ይታወቃል። ዕንባቆም ለጥያቄው መልሱን ባያውቀም ጻድቅ እግዚአብሔር ግን በሥራ ላይ ነው (1:5-11)። በተጨማሪም ቅዱስ አምላክ ይሁዳን ለመቅጣት ከእርሱዋ ይልቅ ኃጢአተኛ የሆነችውን ባቢሎንን እንዴት የቅጣት መሣሪያው



አድርጎ ይጠቀማል? በማለት ጠየቀ (1:12-2:1)። ባቢሎንን የሚጠቀመው ጻድቅ ስለሆነች ሳይሆን የቅጣት መሣሪያው አድርጎ ነው (2:6፤9፤12፤15፤19)። የእግዚአብሔርን ምክር ለሚንቁና በሚያርስባቸው ነገር ስለሚገረሙ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን እንደማስጠንቀቂያ ጠቅሶታል (ሐዋ 13:41)።

2. ***የዕንባቆም መረዳት/ የእምነት ጸሎት***። ዕንባቆም እንቆቅልሽ ለሆነበት ጥያቄው ያገኘው መልስ እግዚአብሔርን መጠባበቅ ነው (2:1)፤ ምክንያቱም በማያሪያው ያለ እግዚአብሔር በእርግጥ ይመጣልና። ስለዚህም ዕንባቆም በመዝሙር ጸሎት እግዚአብሔርን ስለ እርሱነቱ (3:1-3)፤ ስለ ኃይሉ (3:4-7)፤ ስለ አሠራሩ (3:8-16) ያመሰግናል።

**ክርስቶስ በትንቢተ ዕንባቆም መጽሐፍ።**
ሰውን በእምነት በሕይወት የሚያኖር (የሚያጸድቅ) ክርስቶስ ነው (2:4 እና ዮሐ 3:36፤ ገላ 3:11-16፤ 1ዮሐ 5:11-12)።

**ዋና ትምህርት:-**
እግዚአብሔርን ‹ለምን› ብሎ መጠየቅ ባሕርዩንና አሠራሩን አለመረዳት ነው። ብዙ ሰዎች እንደ ዕንባቆም ከባድ የሚባሉ የሕይወት ጥያቄዎች ሊኖሯቸው ይችላሉ። በጊዜ፤ በቦታና በመረዳት አቅም የተገደቡት ነቢያትም ቢሆኑ ስለ እግዚአብሔር አሠራር እርሱ የገለጠላቸውን ብቻ እንጂ ሁሉን አያውቁም። ለዘላለም በማያሪያው ያለ እግዚአብሔር እርሱ መልስን ይዞ ይመጣልና (3:3፤13)። ለጥያቄ ሁሉ ትልቁ መልስ በእግዚአብሔር ማንነት ላይ በመታመን በእርሱ ደስ በመሰኘት መጠበቅ ነው። በእግዚአብሔር ማንነት ላይ መታመን በቅድስናውና በጽድቅ አሠራሩ ላይ መደገፍ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ አመጸ የለም። ጥያቄ ለሚሆንብን ነገር መልሱ ቶሎ ላይመጣ ይችላል፤ ግን መምጣቱ አይቀርም። ጻድቅ ሰው ከሌላው የሚለየው ‹እምነት› ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን በትዕግሥት መጠባበቅ (2:3)። ስለዚህ በአስቸጋሪ ጊዜ ጻድቅ ሰው በእግዚአብሔር ታምኖ በትዕግሥት ይጠብቃል።

## ምዕራፍ 36:-

# ትንቢተ ሶፎንያስ

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ ሶፎንያስ። የሶፎንያስ ቅድመ አያት ንጉሡ ሕዝቅያስ ነበር (1:1)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 625 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በጸሐፊው በነቢዩ ሶፎንያስ።

**ዋና ሰዎች:-** ሶፎንያስ

**ዋና ሀሳብ:-** ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ቀን (የፍርድ ቀን) ማወጅ። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ በጽድቅ ላይ እንደሚቆጣ ማስገንዘብና በንስሐ የሚመለሰውን እንደሚባርክ መናገር ነው።

**ተደጋጋሚ ቃል:-** ‹የእግዚአብሔር ቀን› 10 ጊዜ፤

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና፤ እግዚአብሔር መሥዋዕትን አዘጋጅቶአልና፤ የጠራቸውንም ቀድሶአልና በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ዝም በሉ› (1:7)።
- ‹እናንተ ፍርዱን የጠበቃችሁ የምድር ትሑታን ሁሉ፤ እግዚአብሔርን ፈልጉ፤ ጽድቅንም ፈልጉ፤ ትሕትናንም ፈልጉ፤ ምናልባት በእግዚአብሔር ቍጣ ቀን ትሰወሩ ይሆናል› (2:3)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** መጽሐፉ ስለ አንድ ዋና ሀሳብ ማለትም ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ቀን ይናገራል። በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት የበኣል ተከታዮችና ካህናቱ፤ ለሰማይ ሠራዊት የሚሰግዱ ነበሩ። ሚልኮም ለሚባል ጣዖትና ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ነበር (1:4-5)። ይህ ‹ድብልቅ ሕይወት› (ወይም ቅይጥ አምልኮ) ነው። እግዚአብሔር ይህን ለማጥራት ‹በዚያም ዘመን ኢየሩሳሌምን በመብራት እመረምራለሁ› (1:12) ይላል። ይህ የፍርድ ቀን ነው (1:1-3-9)። ፍርዱም ይሁዳንና (1:4-2:3)፤ ኢየሩሳሌምን (3:1-7) ጨምሮ በምድር ሁሉ ላይ ይሆናል። ከቁጣው ቀን ማምለጫው መንገድ የእግዚአብሔርን ጽድቅና ትሕትናን መፈለግ ነው (2:3)።



**ክርስቶስ በትንቢተ ሶፎንያስ መጽሐፍ።**
ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ የእስራኤል ንጉሥ ነው (3:3፤15 እና ዮሐ 1:49፤ 12:15፤ 19:19)።

**ዋና ትምህርት:-**
የእግዚአብሔር ቀን። የእግዚአብሔር ቀን ‹የመዓት ቀን የመከራና የጭንቀት ቀን፤ የመፍረስና የመጥፋት ቀን፤ የጨለማና የጭጋግ ቀን፤ የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን› ነው (1:14-15)፡ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቀን የሚያመለክተው በአንድ በኩል በቅርብ ጊዜ የሚሆነው የእስራኤል በባቢሎን መማረክን ነበር። ይህ እግዚአብሔር ይሁዳን (እስራኤልን) የሚፈርድበት ጊዜ (ኢሳ 13:6፤9፤ ኢዩ 1:15፤ 2:1-2፤11፤31፤ 3:14፤ አሞ 5:18፤20፤ አብድ 15፤ ሶፎ 1:7፤14)። ይህ ቀን ‹ቅርብ› ነው፤ አመጣጡ በፍጥነት ነው (ኢሳ 13:6፤ ሕዝ 30:3፡ ኢዩ 2:1፤ 3:13፤ ሶፎ 1:7)። ከዚህ ቀን በኂላ በረከት አለ። ይህን አይሁድ ሲገልጹት በቀን ውስጥ ከጨለማ በኂላ ብርሃን እንዳለ እንዲሁ የጌታ ቀን ‹ፍርድና በረከት› አለው ይላሉ። በሩቁ ዘመን ደግሞ በዘመን መጨረሻ የሚገለጠውን ፍርድ ያመለክታል (ኢዩ 2:30፤ 3:18)።

‹የእግዚአብሔር ቀን› በአዲስ ኪዳንም ተገልጾ እናገኘዋለን። (1ቆሮ 1:8፤ 5:5፤ 2ቆሮ 1:14፤ ፊል 1:6፤10፤ 2:16፤ 1ተሰ 5:2፤ 2ተሰ 2:2፤ 2ጴጥ 3:10፤12፤ ራእ 16:14)። የሚያመለክተውም የፍርድና የቁጣ ቀን መሆኑን ነው። እንደ ሌባ ባልታሰበ ሰዓት የሚመጣውን ይህን ቀን ነቅቶ መጠበቅ ይገባል። ይህም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ ነው (2ተሰ 2:2)። ያ ቀን በብዙዎች ላይ እንደ ወጥመድ ይመጣባቸዋል። ሆኖም ከዚህ የቁጣ ቀን ማምለጥ ይቻላል። ማምለጫውም መንገድ ወደ ኢየሱስ መቅረብ ነው (ሉቃ 21፡ 34-36፤ 1ተሰ 1:9-10)።

## ምዕራፍ 37:-

# ትንቢተ ሐጌ

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ ሐጌ (1:1)::

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 520 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በነቢዩ ሐጌ። ትንቢተ ሐጌ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁለተኛው አጭር መጽሐፍ ነው::

**ዋና ሰዎች:-** ዘሩባቤል፤ ኢያሱ

**ዋና** ሀሳብ:- ከምርኮ የተመለሱት ቅሬታዎች ጊዜው ስለሆነ ቤተ መቅደሱን በርትተው እንዲሠሩና እንዲጨርሱ ማበረታታት::

**ተደጋጋሚ ቃል:-** ‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል› 19 ጊዜ፤ ‹ቤት› 9 ጊዜ (የቤተ መቅደሱን እንደገና መሠራት ሲያመለክት):: ‹አናውጣለሁ› 3 ጊዜ::

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:: ልባችሁን በመንገዳችሁ ላይ አድርጉ:: ወደ ተራራው ውጡ፤ እንጨትንም አምጡ፤ ቤቱንም ሥሩ፤ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል፥ እኔም እመሰገናለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር:: እናንተ ብዙ ነገርን ተስፋ አደረጋችሁ፥ እነሆም፤ ጥቂት ሆነ፤ ወደ ቤትም ባገባችሁት ጊዜ እፍ አልሁበት:: ይህ ስለ ምንድር ነው? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: እናንተ ሁሉ ወደ እየቤታችሁ እየሮጣችሁ የእኔ ቤት ፈርሶ ስለ ተቀመጠ ነው› (1:7-9)::
- ‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና:: ገና አንድ ጊዜ በቅርብ ዘመን እኔ ሰማያትንና ምድርን ባሕርንና የብስንም አናውጣለሁ፤ አሕዛብን ሁሉ አናውጣለሁ፥ በአሕዛብ ሁሉ የተመረጠውም ዕቃ ይመጣል፤ ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ በዚህም ስፍራ ሰላምን እሰጣለሁ፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር› (2:6-9)::



**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** መጽሐፉን ከቤተ መቅደሱ መሠራት አንጻር ማየት ይቻላል:: በፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ፈቃድ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱት አይሁድ መካከል ዘሩባቤል (ዕዝ 1:2-4፤ ኢሳ 44:28)፤ ታላቁ ካህን ኢያሱ እንዲሁም ነቢያቱ ሐጌና ዘካርያስ ነበሩ:: እንደተመለሱ የቤተ መቅደሱ ግንባታ ተጀመረ:: በተቃዋሚዎች ለ16 ዓመታት ያህል ተቋረጠ:: የቤተ መቅደሱ መሠራት እግዚአብሔር በመካካላቸው የመኖሩ ምልክት ነው:: የሕዝቡ ትኩረት ግን በየራሱ ኑሮና ቤቱን በማሳመር ላይ ሆኖ ነበር:: ሆኖም እንደ ጥረታቸው ብዛት አልበለጸጉም፤ እግዚአብሔር ሥራቸውን አልባረከላቸውምና:: እግዚአብሔር የይሁዳ አለቃ ወደነበረው ዘሩባቤልና ሊቀ ካህን ወደነበረው ኢያሱ ተነስተው ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ነቢዩን ሐጌን በመላክ (ዕዝ 5:1-2፤ ሐጌ 1:1) ...ለመሥራት ጊዜው አሁን ነው ይላቸዋል:: እንዲሁም በኑሮአቸውም እንዲቀደሱ ይመክራቸዋል (2:10-19):: የእግዚአብሔርን መቅደስ በመሥራታቸው በረከት እንደሚሆንላቸውም ያስታውቃቸዋል (2:18-19):: ይህም ልባቸውን በመንገዳቸው ላይ ማድረግ ነው (1:7)::

**ክርስቶስ በትንቢተ ሐጌ መጽሐፍ::**

ክርስቶስ ሰላምን የሚሰጥ የሰላም አለቃ ነው (2:8 እና ዮሐ 14:27፤ ኤፌ 2:14)::

ክርስቶስ የመንግሥታትን መንግሥት የሚገለብጥና በሁሉም ላይ የሚገዛ ንጉሥ ነው (2:22 እና ራእ 11:15)::

**ዋና ትምህርት:-**

የእግዚአብሔርን ሥራ ተግቶ መሥራት:: ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ ረስተው ቤቶቻቸውን ይሠሩ ጀመር:: ለእነርሱ ቤቶቻቸውን መሥራት ጊዜው እንደሆነ ሲመስላቸው የፈረሰውን የእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ግን ‹ዘመኑ አልደረሰም› (1:2) ይሉ ነበር:: በምርኮ በነበሩባቸው ዓመታት ለረጅም ዘመን ያለ ቤተ መቅደስ የኖሩ ሰዎች በመሆናቸው ያለ ቤተ መቅደስ መኖሩን ‹ለምደውታል›:: ሆኖም ጥረታቸው አልተባረከላቸውም:: ‹ብዙ ዘራችሁ፤ ጥቂትም

አገባችሁ፤ በላችሁ፤ ነገር ግን አልጠገባችሁም፤ ጠጣችሁ፤ ነገር ግን አልረካችሁም፤ ለበሳችሁ፤ ነገር ግን አልሞቃችሁም፤ ደመወዙን የተቀበለ ሰው በቀዳዳ ከረጢት ያደርገው ዘንድ ደመወዙን ተቀበለ› (1፡6) አላቸው። የዚህም ምክንያት ‹እናንተ ሁሉ ወደ እየቤታችሁ እየሮጣችሁ የእኔ ቤት ፈርሶ ስለ ተቀመጠ ነው› (1፡9) በማለት እግዚአብሔር ይናገራቸዋል። እውነተኛ በረከት ያለው ቅድሚያ ለሚሰጠው ለእግዚአብሔር ነገር ቅድሚያ በመስጠት ነው (ማቴ 6፡33)። ለግል ጉዳይ ቅድሚያ በመስጠት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምክንያት ማብዛትና መስላቸት እውነተኛውን የበረከት ምንጭ መዘንጋት ነው።



# ምዕራፍ 38፡-
# ትንቢተ ዘካርያስ

**ጸሐፊው፡-** የአዶ ልጅ፤ የበራክዩ ልጅ ነቢዩ ዘካርያስ ነው (1፡1)። አዶ ከዘሩባቤልና ከኢያሱ ጋር ከምርኮ ከተመለሱት ካህናት መካከል አንዱ ነበር (ነህ 12፡4)።

**የተጻፈበት ጊዜ፡-** 520-518 ዓ.ዓ። ነቢዩ ሐጌና ነቢዩ ዘካርያስ በአንድ ዘመን የነበሩ ነቢያት ናቸው (ዕዝ 6፡14)።

**የመጽሐፉ ስያሜ፡-** በጸሐፊው ነቢዩ ዘካርያስ። በአዲስ ኪዳን 41 ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል።

**ዋና ሰዎች፡-** ዘሩባቤል፤ ኢያሱ

**ዋና ሀሳብ፡-** ከምርኮ የተመለሱት በእግዚአብሔር ታምነው የቤተ መቅደሱን ሥራ እንዲፈጽሙ ማበረታትና በመሢሑ መምጣት የእስራኤል መታደስ እንደሚሆን ማስገንዘብ።

**ተደጋጋሚ ቃል፡-** ‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር›[72] 53 ጊዜ፤ ‹የእግዚአብሔር ቃል› 13 ጊዜ፤

**ቁልፍ ጥቅሶች፡-**

- ‹ለዘሩባቤል የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር› (4፡6)።

---

[72] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ‹እግዚአብሔር ጸባኦት› ይላል። Hb. tsaˆbaˆ. tsebaˆaˆh (tsaw-baw', tseb-aw-aw') a mass of persons especially regularly organized for war. በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በብዛት ‹የሠራዊት ጌታ› ተብሎ የተጠራው ከምርኮ በኋላ በነበሩት በሦስቱ ነቢያት ነው። ይህ ጊዜ እስራኤላውያን ገና ከምርኮ የተመለሱበት ዘመን ነበር። የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እየሠሩ፤ ለራሳቸውም ገና መኖሪያ ቤት እየሠሩ ነበር። የጦር ሠራዊት አልነበራቸውም። ሰባው የምርኮ ዓመታት ሲያልቅ እንደተናገረው ከምርኮ እንዲመለሱ ያደረገ እግዚአብሔር እርሱ ይጠብቃቸዋል፤ እርሱ ይዋጋላቸዋል። እግዚአብሔር የእስራኤል ‹ጸባዖት› ነው።

- ‹አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤ እነሆ፤ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፤ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል› (9፡9)።

**የመጽሐፉ አከፋፈል፡-** *መጽሐፉን* በ3 በመክፈል እንመለከታለን፡፡

1. ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቤት እንዲሠራ የተደረገ ጥሪ (1-6)
2. ስለ ጾምና በዓላት (7-8)
3. ስለወደፊቱ ዘመን የተነገረ መልእክት (9-14)

**1. ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቤት እንዲሠራ የተደረገ ጥሪ፡፡** ዘካርያስ ስለ ቤተ መቅደሱ፤ ስለ ዘሩባቤል፤ ስለ ኢያሱና በአጠቃላይ ስለ እስራኤል የሚናገሩ ስምንት ራእዮች ተሰጠው (1፡7-7፡14)፡፡ ቤተ መቅደሱን እንደገና የመሥራት ጉዳይ እንደ ተራራ አዳጋች ተግባር ሆኖባቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ይህን መሥራት የሚችሉት ተራራውን ደልዳላ ሜዳ በሚያደርገው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሆነ ያስገነዝባቸዋል (4፡6-9)፡፡ በታላቁ ካህን ምሳሌነት ሰይጣን በእስራኤል ሕዝብ ላይ ባነሣው ክስ እግዚአብሔር ተዋጋላቸው (6፡9-15)፡፡

**2. ስለ በዓላትና ጾም፡፡** የመጾም ዓላማ ለራስ ጥቅም ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማክበር መሆን አለበት (7፡5-6)፡፡ በዚህ ዘመን ግን ጾም ራስን በማስጨነቅ (በማዋረድ) የእግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግና ከእርሱ ጋር የመገናኘት መንገድ መሆኑ ቀርቶ ውጫዊ ሥርዓት ብቻ ሆኖ ነበር፡፡ እውነተኛ ጾም ድሃ አደጉን ማሰብ፤ ምሕረትን ማድረግ በእውነት መፍረድን ይጨምራል፡፡ ሕዝቡም እግዚአብሔር ሲናገር ልባቸውን ‹እንደ አልማዝ› አጠንክረው ነበር (7፡12)፡፡ እግዚአብሔርም ‹እኔ በጠራሁ ጊዜ እነርሱ እንዳልሰሙኝ፤ እንዲሁ እነርሱ በሚጠሩበት ጊዜ እኔ አልሰማም› አላቸው (7፡13)፡፡

**3. ስለ ወደፊቱ ዘመን የተነገረ ሽክም፡፡** እግዚአብሔር በእስራኤል ጠላቶች ላይ ፍርድ እንደሚፈርድ ይገልጻል (9)፡፡ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት (9-11)ና ሁለተኛ መምጣት (12-14) ይናገራል፡፡



ከነቢያት መጻሕፍት ከኢሳይያስ ቀጥሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ትንቢት የተናገረ ነቢይ ዘካርያስ ነው፡፡ ነቢዩ ዘካርያስ ስለ ክርስቶስ ሁለቱ መምጣቶች ትንቢት ተናግሯል፡፡ ሠንጠረዥ 26 ትንቢቱንና በእውን የተፈጸመውን ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 26
ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢትና የተፈጸመው

| ትንቢቱ | የተፈጸመው |
| --- | --- |
| ባሪያዬ 3፡8 | ማር 10፡45 |
| ንጉሥ-ካህን 6፡13 | ዕብ 6፡20-7፡1 |
| ትሑት ንጉሥ 9፡9-10 | ማቴ 21፡4-5፤ ዮሐ 12፡14-16 |
| በሰላሳ ብር አልፎ የሚሰጥ 11፡12-13 | ማቴ 27፡9 |
| ጎድኑን የተወጋ 12፡10 | ዮሐ 19፡37 |
| ከኃጢአትና ከርኩሰት የሚያነጻ ምንጭ 13፡1 | ራእ 1፡5 |
| የተመታ እረኛ 13፡7-9 | ማቴ 26፡31፤ ማር 14፡27 |
| ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር የሚመጣ 14፡5፤9 | ዮሐ 10፡16፤ ራእ 11፡15፤ 21፡27 |

**ዋና ትምህርት፡-**

**በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እግዚአብሔርን ማገልገል፡፡** የይሁዳ አለቃ ዘሩባቤል ለ16 ዓመት ያህል የተቋረጠውን የቤተ መቅደስ ሥራ የማስቀጠልና የማስጨረስ ከባድ ኃላፊነት አለበት፡፡ ቢሆንም ሥራውን ለመሥራት እግዚአብሔር በዘሩባቤልም ሆነ በሌላ ሰው ወይም መንግሥት አይደገፍም፡፡ ስለዚህ ‹በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም› (4፡6) በማለት ሲያስተውለው ስለተገባ ነገር ይነግረዋል፡፡ ኃይልና ብርታት ማናቸውንም ዓይነት የሰው ጉልበት፤ እውቀት፤ ሀብት፤ ሥልጣን ወዘተ ያመለክታል፡፡ ‹ሰማይንና ምድርን በማናወጥ› (ሐጌ 2፡7) ሥራውን የሚሠራ እግዚአብሔር በሰው ኃይል፤ ብርታት፤ ሀብት፤ ሥልጣን አይደገፍም፡፡ የእግዚአብሔር ሥራ በሰው ጥበብና ችሎታ አይሠራም፡፡ ወንጌልን መስበክ (1ቆሮ 2፡4-5፤ 1ጴጥ 1፡12)፤ የጠላትን ምሽግ የሚያፈርስ መንፈሳዊ ውጊያ ማድረግ የሚቻለው (2ቆሮ 10፡4-5) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡ ሌሎች በኃይላቸውና በሠራዊታቸው ይታመናሉ፤ ለእግዚአብሔር ሰው ግን ትምክህቱ አምላኩ በእግዚአብሔር ነው (መዝ 20፡7)፡፡

## ምዕራፍ 39:-

# ትንቢተ ሚልክያስ

**ጸሐፊው:-** ነቢዩ ሚልክያስ ነው (1:1)።

**የተጻፈበት ጊዜ:-** 450-400 ዓ.ዓ.

**የመጽሐፉ ስያሜ:-** በጸሐፊው በነቢዩ ሚልክያስ።

**ዋና ሰዎች:-** ሚልክያስ፤ ካህናት

**ዋና ሀሳብ:-** በንስሐ መመለስና እግዚአብሔርን እንደ ቃሉና በእውነት ማምለክ። ቤተ መቅደሱ ከተሠራና ከሐጌና ዘካርያስ አገልግሎት ከ100 ዓመት በኋላ ሕዝቡ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ተዳክሞ ነበር። የነበራቸው ቅንዓት ቀዝቅዟል። ወደ መንፈሳዊ ግድየለሽነትና የኃጢአት ኑሮ የተመለሰውን ይህን ሕዝብ መንገዱን እንዲያስተካክልና ከእግዚአብሔር ጋር በንስሐ እንዲታረቅ መምከር።

**ተደጋጋሚ ቃል:-** ‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር› 24 ጊዜ፤ ‹ትላላችሁ› 11 ጊዜ፤ ርጉም (የተረገመ) 7 ጊዜ።

**ቁልፍ ጥቅሶች:-**

- ‹እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችኋል። እናንተም። ያታከትነው በምንድር ነው? ብላችኋል። ክፉን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ መልካም ነው፤ እርሱም በእነርሱ ደስ ይሰዋል፤ ወይስ:- የፍርድ እምላክ ወዴት አለ? በማለታችሁ ነው (2:16)።
- ‹እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፤ እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፤ ስለዚህ የጠፋችሁ አይደላችሁም› (3:6)።
- ‹የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ፤ እግዚአብሔርም አደመጠ፤ ሰማም፤ እግዚእብሔርንም ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ። እኔ በምሠራበት ቀን እነርሱ የእኔ ገንዘብ ይሆናሉ፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ሰውም የሚያገለግለውን ልጁን እንደሚምር፤ እንዲሁ እምራቸዋለሁ› (3:16-17)።



**የመጽሐፉ አከፋፈል:-** በሦስት በመክፈል እንደሚከተሰው ማየት ይቻላል።

1. የእስራኤል በእግዚአብሔር መወደድ (1:1-5)።
2. የእስራኤል በኃጢአት መርከስ (1:6-3:15)
3. ለእስራኤል የተሰጠ ተስፋ (3:16-4:6)

**1. የእስራኤል በእግዚአብሔር መወደድ።** በኃጢአታቸው ምክንያት እስራኤላውያን ሰምርኮ አልፈው በመሰጠታቸው በእግዚአብሔር የተወደዱ አልመሰላቸውም ነበር። የእግዚአብሔር መውደዱ የተገለጸው እንደ አባት መቅጣቱና ቅሬታዎቹ ወደ ምድራቸው እንዲመለሱ ማድረጉ ነው።

**2. የእስራኤል በኃጢአት መርከስ።** ሕዝቡ እግዚአብሔር ለሚናገራቸው ቃል በክርክር ይመልሱለት ነበር። ካህናት የመሥዋዕት ሥርዓት አያከብሩም (1:6)፤ የቀዘቀዘ መንፈሳዊ ሕይወት ነበራቸው። የተናቀውን፤ በሰው የማይፈለገውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድረገው ያቀርቡ ነበር። ካህናቱ ሕጉን አያውቁም ለሕዝቡም አያስተምሩም። ሕዝቡም ‹የእንግዳ አምላክ ልጆችን› ያገቡ ነበር (211)። እግዚእብሔር ቅን ፈራጅ መሆኑንም ረስተው ነበር። ሕዝቡ አሥራቱን ወደ እግዚአብሔር ቤት አያመጣም (3:7-12)። ከዚህም የተነሳ ምንም ጥረት ቢያደርጉ በኑሮአቸው የተባረኩ አልነበሩም። እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ የእነርሱን ተለዋዋጭነትና አለመታመን በመግለጽ ‹እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም› (3:6) በማለት ከእርሱ ማንነት የተነሣ በመመለስ ተስፋ እንዳላቸው ያረጋግጥላቸዋል።

**3. ለእስራኤል የተሰጠ ተስፋ።** በየትኛውም ዘመን እግዚአብሔር እርሱን የሚፈሩትን እንደሚያውቃቸውና መታሰብም እንደሚሆንላቸው ይገልጽላቸዋል (3:16-18)። ለእነርሱ የጽድቅ ፀሐይ ይወጣልና።

**ክርስቶስ በትንቢተ ሚልክያስ መጽሐፍ፡፡**

ክርስቶስ መንገድን በፊቱ የሚያስተካክል መልእክተኛ የሚልክ ጌታ ነው (3፡1 እና ማቴ 11፡10)፡፡ ‹ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው› አይለወጥም (3፡6 እና ዕብ 11፡8)፡፡

**ዋና ትምህርት፡-**
**የቀዘቀዘ ሕይወት ተሚጋች ነው፡፡** በሚልክያስ ዘመን የካህናቱና የሕዝቡ አምልኮ የቀዝቀዘና ውጫዊ የሆነውን ሥርዓት መፈጸም ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር፡፡ በመሥዋዕት አቀራረብ፤ በጋብቻቸውና በገንዘባቸው ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩም፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት የለም፡፡ አገልጋዮችም እግዚአብሔርን ማገልገል እንደ ከንቱ ነገር ይመስላቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ያሉበትን ሁኔታ ሲያስረዳቸው ይከራከሩ ነበር፡፡ በውጫዊ ሥርዓት ላይ ብቻ ያተኮረ በሰው ለመታየትና ለመሞገስ የሚደረግ አምልኮ በእግዚአብሔር የተናቀ ነው፡፡ የአንድ ሰው የክርስትና ሕይወት አደጋ ላይ የሚወድቀው እንደዚህ ለብ ሲል ነው፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ግን ሁልጊዜ በትጋትና በቅንነት ያገለግሉታል፡፡ እነርሱንም እግዚአብሔር አይረሳም፤ በመታሰቢያ መጽሐፍ ይጻፋሉ (2፡17)፤ የሚታሰቡበት ጊዜም አለ፡፡



# ማጠቃለያ

ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እቅድና የማዳን ሥራ የሚገልጥ ‹እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም› (ሚል 3፡6) ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ወይም ምሳሌ ነው፡፡ ከአዲስ ኪዳን ጋር በተገናኘ መልኩ የብሉይ ኪዳንን መልእክት በ6 ዋና ርዕሶች እንደሚከተለው ለማጠቃለል እንሞክራለን፡፡

**1. ከሴቲቱ ዘር የሚወለደው የሰይጣንን ራስ ይቀጠቅጣል፡፡**
ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ከሴቲቱ የሚወለደው የእባቡን (ሰይጣንን) ራስ እንደሚቀጠቅጥ ቃል ገባ (ዘፍ 3፡15)፡፡ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ለሰው የተሰጠ የመጀመሪያው የደህንት ተስፋ ነው፡፡ ከዚያም በአብርሃም ዘር የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩና (ዘፍ 22፡18) አሕዛብ ሁሉ የሚታዘዙለት ገዥ በአብርሃም፤ ይስሐቅ፤ ያዕቆብ በኩል እንደሚመጣ ተናገረ (ዘፍ 49፡10)፡፡ ይህም ከዳዊት ቤት የሆነ (2ሳሙ 7፡12-15) በቤተልሔም የሚወለደው ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ ህፃን ነው (ሚክ 5፡2)፡፡ እርሱም በመስቀል ሞቱ የዲያብሎስን ሥልጣን የገፈፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዕብ 2፡14-15፤ ቆላ 2፡15)፡፡

**2. እግዚእብሔር ከሕዝቡ ጋር ይሆናል፡፡**
እግዚአብሔር አብርሃምን ‹ከአንተ ጋርም እሆናለሁ› (ዘፍ 26፡3) በማለት የገባውን ቃል ጠብቋል፡፡ እስራኤለውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ካወጣቸው በኋላ በምድረ በዳ በማደሪያው ድንኳን ‹በእስራኤልም ልጆች መካከል እኖራለሁ› (ዘጸ 29፡45) አለ፡፡ እርሱ መንፈሱን በሕዝቡ ውስጥ ያሳድራል (ሕዝ 37፡14)፡፡ ከሕዝቡ ጋር የሚኖረው ከድንግል የሚወለደው አማኑኤል ነው (ኢሳ 7፡14)፡፡ የአማኑኤል ትርጓሜ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው፡፡ የአማኑኤል ስሙ ኢየሱስ ነው (ማቴ 1፡21-23)፡፡

**3. እስራኤል ለምድር ብርሃን እንድትሆን ተመረጠች።**

ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት፣ የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ እንዲሆኑ እግዚአብሔር እስራኤልን መረጠ (ዘጸ 19:3-6)። የተመረጡት የእግዚአብሔርን መልካምነት ለምድር ሁሉ እንዲያውጁ ነበር። ሆኖም አልታዘዙም። እግዚአብሔርን በመፍራት ተቀድሰው እንዲኖሩ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ባለመጠበቃቸው ለሁለት ተከፈሉ። የሰሜኑ እስራኤል ለአሦር፣ የደቡቡ ይሁዳ ለባቢሎን ምርኮ አልፈው ተሰጡ። በምርኮ ሳሉ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን አሰበ፣ መቃብራቸውን ከፍቶ ከመቃብራቸው አወጣቸው፣ ቅሬታዎችን ወደ እስራኤል ምድር አገባቸው (ሕዝ 37:12)። እግዚአብሔር ለአሕዛብ ብርሃን እንድትሆን ከተጠራት (ኢሳ 49:5-6) ከእስራኤል ነቢያትን ወደ አሕዛብ እየላከ የንስሐ ስብከት እንዲሰብኩም አደረገ። ሆኖም በአጠቃላይ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር አልተጣበቁም። ጌታም ሲናገር ‹እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፣ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት። አብዝቼ ብጠራቸው አጥብቀው ከፊቴ ራቁ› (ሆሴ 11:1) አለ። ልጁ እስራኤል ባለመታዘዙ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያደርገውን አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከ (ማቴ 2:15)።

**4. እግዚአብሔር ሕግን ሰጠ።**

እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ሕግን ሰጠ። የሕግ መጀመሪያው ‹ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ› የሚለው ነው (ዘጸ 20:3)። የሕግ ማጠቃለያም ‹አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ› እና ‹ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ› የሚሉት ናቸው (ዘሌ 19:18፤ዘዳ 6:5፤ ማር 12:33)። እነዚህ በእግዚአብሔር የተሰጡ ትእዛዛት የእርሱን የጽድቅ ባሕርይ ይገልጻሉ። ሌሎች ሕጎችም ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ እንዲቻል የመቅረቢያውን መንገድ ያመለክታሉ፣ ሕዝቡም በተቀደሰውና ንጹህ ባልሆነው መካከል የሚለዩበትን መንገድ ያሳያሉ። ይህም ሆኖ ሕግ የተሰጣቸው እስራኤላውያን ሕግን አልጠበቁም። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግንና ነቢያትን ሊፈጽም መጣ (ማቴ 5:17)። ሕግ በአምነት ወደሚያጸድቀው ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚት ነው (ገላ 3:24)። ጽድቅ የሚገኘው በሥራ ሳይሆን በአምነት ነውና።



**5. እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ነው።**

እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤል የገባው ኪዳን ሕዝቡ የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ እንዲሆንለት ነው ‹ዘጸ 19:6)። እነርሱ ግን ከእግዚአብሔር ጋር በቅድስና መራመድ አቃታቸው። በተደጋጋሚ ባለመታዘዝ ወደቁ፣ ከአሕዛብ ጋር ተደባለቁ፣ ጣዖታትንም ተከተሉ፣ ክህነታቸውንም አልፈጸሙም፣ በኪዳን አልጸኑም። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሌላ የሚሻል ኪዳን አዘጋጀ። እግዚአብሔር ከእስራኤል ቤት ጋር የገባው ይህ የሚሻል ቃል ኪዳን እርሱ ሕጉን በልቡናቸው የሚያኖርበት፣ በልባቸውም የሚጽፍበት ‹አዲስ ቃል ኪዳን› ነው (ኤር 31:33-34፤ ዕብ 8:6-10)። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ተፈጸመ። ለኃጢአት ይቅርታ በፈሰሰው ደሙ አዲሱ ኪዳን ታተመ (ማቴ 26:28)። ‹ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል› (ዕብ 7:22)።

**6. የጌታ ቀን ይመጣል።**

የጌታ ቀን እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ሀሳቡን የሚገልጽበት ቀን (ሰዓት/ ጊዜ) ነው። በብሉይ ኪዳን ስለ ጌታ ቀን የተነገረው በአንድ በኩል በእስራኤላውያን ላይ ስለሚመጣው ቅጣትና ምርኮ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከዚያ በኋላ በሩቁ ዘመን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ስለሚፈሰው መንፈስ ቅዱስ መውረድ ያመለክታል (ኢዩ 2:28-32)። ይህንም ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ በባለ ሃምሳ ቀን አፈሰሰው (ሐዋ 2:33)። ከዚያም እልፎ ብሉይ ኪዳን በመጨረሻ ዘመን በጌታ ቀን ስለሚሆኑ ዋና ጉዳዮች ያስረዳል። አስፈሪ የፍርድና የቁጣ ቀን ይመጣል፣ እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ይሠራል (ኢሳ 66:22)፣ የሙታንም ትንሣኤ ይሆናል። ‹በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፣ እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፣ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጕስቍልና› ይሄዳሉ (ዳን 12:1-2)። የሙታንና የሕያዋን ጌታ ከሙታን በኩር የሆነው ኢየሱስ ነው (ሮሜ 14:9)።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ እርሱን እናውቀው ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠን መመሪያ ነው። የቀደመውን ክብር የሚገልጸው ብሉይ ኪዳን የሚያስደንቅ የእግዚአብሔር መገለጥ የያዘ መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔርን ለማወቅ በሩ ቃሉን ማወቅ ነው። ቃሉ ወደ እግዚአብሔር ስለሚያደርሰው አንድና ብቸኛ

መንገድ ይናገራል። መንገዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አንባቢ ሆይ በዚህ መንገድ ብትሄድ ወደ ዘላለም እረፍት ትደርሳለህ።

ብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት፣ በአዲስ ኪዳን የታየው ክብር ከመምጣቱ በፊት የተገለጠውን የቀደመ ክብር የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ በመልኩ እንደ ምሳሌው የፈጠረው ሰው በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ የደህንነትን መንገድ በማዘጋጀት፣ ቃል ኪዳን በመግባት፣ ሕግን በመስጠት፣ ለራሱ ሕዝብን በመምረጥ፣ በመምራትና በመጠበቅ ባደረገው ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ባሕርይ፣ አቅድና አሠራር ከብሉይ ኪዳን በጥልቀት እንረዳለን።

ይህ የዳሰሳ መጽሐፍ በእያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ አጠር ያለ ማብራሪያ ያቀርባል። የተለየ ትኩረትም፦

- ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የተገለጸበትን መንገድ በማመልከትና
- የየመጽሐፉን ዋና ትምህርት በማሳየት ላይ ያደርጋል።

የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እግዚአብሔር ያዘጋጀውንና በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የሚጀምረውን አዲስ ኪዳን በእምነት በሩቁ ተመለከቱ። እኛ በአሁኑ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ደግሞ ከ2000 ዓመታት በፊት አዳኛችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅና የማዳን ሥራ እያሰብንና ደስ እየተሰኘን ለእርሱ ክብርና ምስጋና እናቀርብለታለን።

እንግዲህ የቀደመውን ኪዳን የሰጠን የክብር ጌታ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ከፊተኛው በሚሻል ተስፋ አዲስ ኪዳን ሰጠን። ክብር ለእርሱ ይሁን። አሜን።



# ዋቢ መጻሕፍት Bibliography

## Books and publications


በላይ መኮንን (ሊቀ ኅሩያን) 2002 ዓ.ም.፤ ሕያው ልሳን፦ግዕዝ-አምርኛ መዝገበ ቃላት የተሻሻለው ሁለተኛ እትም፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ

ተም ዶውሴይ (ዶ/ር) (1989)፤ የተማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ አትላስ፤ ኤስ አይ ኤም ኢትዮጵያ አሳታሚ፤

ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1993 ዓ.ም.) መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲሱ መደበኛ ትርጉም

የብሉይ ኪዳን መክፈቻ (1997 ዓ.ም.)፤ ኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1972 ዓ.ም.)፤ የመጽሐፍ ቅዱ መዝገበ ቃላት፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ

-------------------- (1980 ዓ.ም.)፤ መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲስ አበባ፤

Bickel, Bruce and Stan Jantz (2006). Bible Answers to Life's Big Questions. Harvest House Publishers, Eugene, Oregon

English Standard Version Study Bible.

Gurdem, Wayne (1994). Systematic Theology, Inter-Varsity Press, Leicester.

Jensen's Bible Study Charts, Moody Press, 1981 Edition

Larkin, Clarence (1918). Dispensational Truth or God's Plan and Purposes in the Ages, Rev Clarence Larkin Publishers, Glenside, Pa.

Life Application Bible, King James Version

Milne, Bruce (1982). Know The Truth: A handbook of Christian belief, Inter-varsity press.

Nelson's Illustrated Bible Dictionary. (1986), Thomas Nelson Publishers.

Nelson's Student Bible Handbook (2007). Thomas Nelson Inc., Nashville.

Ramm, Bernard, (1956), Protestant Biblical Interpretation, Boston: W.A. Wilde company.

Ryrie Study Bible: New International Bible (1986). Moody Press, Chicago.

Towns, Elmer L. (2003), Bible Answers for almost all your questions, Thomas Nelson Publishers, Nashvile

Walvoord, John F., Roy B. Zuck (1985), The Bible Knowledge Commentary: Old Testament, Victor Books.

Wilson, D.N. (2009), Old Testament Survey, Feedbooks.

## Electronically Retrieved.

http://www.clclutheran.org/

http://www.free-bible-study-lessons.com/

http://www.gotquestions.org/

http://home.hkstar.com/~johnfok1/Old Testament Survey

http://www.tenbasicsteps.org/

ብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት፣ በአዲስ ኪዳን የታየው ክብር ከመምጣቱ በፊት የተገለጠውን የቀደመ ክብር የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ በመልኩ እንደ ምሳሌው የፈጠረው ሰው በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ የደህንነትን መንገድ በማዘጋጀት፣ ቃል ኪዳን በመግባት፣ ሕግን በመስጠት፣ ለራሱ ሕዝብን በመምረጥ፣ በመምራትና በመጠበቅ ባደረገው ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ባሕርይ፣ እቅድና አሠራር ከብሉይ ኪዳን በጥልቀት እንረዳለን።

ይህ የዳሰሳ መጽሐፍ በእያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ አጠር ያለ ማብራሪያ ያቀርባል። የተለየ ትኩረትም፦
•ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የተገለጸበትን መንገድ በማመልከትና
•የየመጽሐፉን ዋና ትምህርት በማሳየት ላይ ያደርጋል።

በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እግዚአብሔር ያዘጋጀውንና በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የሚጀምረውን አዲስ ኪዳን በእምነት በሩቁ ተመለከቱ። እኛ በአሁኑ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ደግሞ ከ2000 ዓመታት በፊት አዳኛችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅና የማዳን ሥራ እያሰብንና ደስ እየተሰኘን ለእርሱ ክብርና ምስጋና እናቀርብለታለን። ክብር ለእርሱ ይሁን።




Designed & Printed by Andne Printers

**ዋጋ 25 ብር**